የወንጀል ሕግ ሞጁል
የወንጀል ሕግ የቅድመ ሥራ ሥልጠና ሞጁል

የሥልጠና ሞጁሉ ዓላማ

የሥልጠናው አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

1. ወንጀልን የሚመለከቱ የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች እንዲለዩ ማድረግ፤
2. የወንጀል ፍትህ ሥርአት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በማስከበርና የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ በኩል ስላለው ሚና እንዲረዱ ማድረግ፤
3. የወንጀል ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸምና የትርጉም ችግሮችን እንዲለዩ፣ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል ወጥ፣ ተገማችና ተመራጭ የሆነ ትርጉም ተግባራዊ የማድረግ ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
4. በዘመናችን የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውጤታማነትን የሚፈታተኑ ለየት ያለ ባህሪ ያላቸውን ወንጀሎች እና ወንጀሎችን አስመልክቶ ሊሰጥ ስለሚገባው ትኩረት እንዲገነዘቡ ማስቻል፤

ናቸው።

የወንጀል ሕግ የቅድመ ሥራ ሥልጠና ሞጁል ማውጫ

ገጽ

ምዕራፍ አንድ - የወንጀል ሕግና ሕገ መንግሥቱ .....

ክፍል አንድ - የወንጀል ሕጉና የሕገ መንግሥቱ ቁርኝት .....

ክፍል ሁለት - የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የሚመራባቸው መርሆዎች .....

ንዑስ ክፍል አንድ - የህጋዊነት መርህ .....

ንዑስ ክፍል ሁለት - የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ .....

ንዑስ ክፍል ሦስት - ለአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት መከልከሉ .....

ምዕራፍ ሁለት - በወንጀል ድንጋጌዎች ዙሪያ የሚስተዋሉ የትርጉምና
የአፈጻፀም ችግሮች .....

ክፍል አንድ - በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የሚስተዋሉ የትርጉምና
የአፈጻፀም ችግሮች .....

ንዑስ ክፍል አንድ - ወንጀልን የሚያቋቁሙ ቅድመ ሁኔታዎች እና በሕግ
ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት .....

ንዑስ ክፍል ሁለት - የምክንያትና ውጤት ግንኙነት መርህ .....

ንዑስ ክፍል ሦስት - የወንጀል መፈፀም ሀሳብ .....

ንዑስ ክፍል አራት - ደጋጋሚ ወንጀለኛነት .....

ንዑስ ክፍል አምስት - ተደራራቢ ወንጀሎች እና ቅጣት.....

ንዑስ ክፍል ስድስት - በወንጀል ተካፋይነት .....

ክፍል ሁለት - በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የሚስተዋሉ የትርጉምና
የአፈጻፀም ችግሮች .....

ንዑስ ክፍል አንድ - የሰው መግደል ወንጀል .....

ንዑስ ክፍል ሁለት - በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል .....

ንዑስ ክፍል ሦስት - የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት .....

ምዕራፍ ሦስት - ልዩ ትኩረት የሚሹ አንዳንድ ወንጀሎች .....

ክፍል አንድ - በሕገ መንግሥቱና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ
የሚፈፀሙ ወንጀሎች .....

ንዑስ ክፍል አንድ - በሕገ መንግሥቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች .....

ንዑስ ክፍል ሁለት - በሕገ መንግሥት በተቋቋመው ሥርዓት ላይ
የሚፈጸሙ ወንጀሎች .....

ክፍል ሁለት - የሙስና ወንጀል .....

ክፍል ሦስት - የዘር ማጥፋት ወንጀል .....

ክፍል አራት - የአሸባሪነት ወንጀል .....

ክፍል አምስት - የሰዎች ህገወጥ ዝውውር .....

ክፍል ስድስት - የአስገድዶ መድፈር ወንጀል .....

ምዕራፍ አንድ - <u>የወንጀል ሕግና ሕገ መንግሥቱ</u>

ይህን ሥልጠና ሲያጠናቀቁ ሰልጣኞች፡-

1. በወንጀል ሕጉና በሕገ መንግሥቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ይረዳሉ፤
2. በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ ከወንጀል ሕጉ ጋር ግንኙነት ያላቸው መርሆዎች ይገነዘባሉ፤
3. ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመጠበቅ የወንጀል ሕጉ ያለውን ሚና በአግባቡ ይረዳሉ፡፡
4. የህጋዊነት መርህን ምንነት በዝርዝር ይረዳሉ፤
5. የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ሄዶ የማይሰራ መሆኑንና ከነምክንያቱ ይገነዘባሉ፤
6. የወንጀል ሕጉ ከመፅናቱ በፊት ያሉትን ጉዳዮች ለመሸፈን ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሠራባቸውን ሁኔታዎች ይረዳሉ፤

ክፍል አንድ - <u>የወንጀል ሕጉና የሕገ መንግሥቱ ቁርኝት</u>

በ1993 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው መዝገበ ቃላት “ህገ መንግስት ማለት አንድ አገር የሚተዳደርበትና ሕዝቦቿ ለሚያከናውኗቸው ተግባሮች ሁሉ መርህ የሚሆናቸው የሁሉም የበላይ የሆነ ህግ” ነው በማለት ይተረጉመዋል፡፡

የኮመን ሎው አገሮችን በተለይም የአሜሪካን የሕግ ሥርዓት የሚያንፀባርቀው በሕግ ሙያ ዙሪያ የምንጠቀምባቸውን ቃላት እና ሀረጎች ወይም ፅንሰ ሀሳቦች ለመተርጎም ብዙ ጊዜ የምንጠቀምበት ብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት (Black’s Law Dictionary) የሰጠውን ትርጓሜ ስንመለከት ደግሞ “Constitution is the fundamental and organic law of Nation or State establishing the conception, character, and organization of its government, as well as prescribing the extent of its sovereign power and the manner of its exercise” የሚል ትርጓሜ ሰጥቶት እናገኛለን፡፡ ይህን ትርጓሜ ስንመረምረው፡-

- ሕገ መንግሥት መሠረታዊ የሆነ አንዲት አገር ወይም መንግሥት የሚመራባትና የሚተዳደሩበት ህግ መሆኑን፤

- ይህ መሰረታዊ ህግ በዋነኛነት ስለ መንግሥት አወቃቀር፣ የመንግሥት አካላት አደረጃጀት፣ የመንግሥቱን ባህሪና ስለ መንግሥት ስልጣን ሊያዝ የሚገባውን ገዢ አስተሳሰብ የሚያቋቁምና የሚደነግግ የህግ ክፍል መሆኑን፣
- ከላይ ከገለፅናቸው በተጨማሪ ሕገ መንግሥት የመንግስት ስልጣን እስከምን ድረስ እንደሆነና መንግስት ስልጣኑን ሥራ ላይ ስለሚያውልበት አግባብ ወይም ስርዓት የሚደነግግ ገዢ የሆነ የህግ ክፍል እንደሆነ ይገልፃል፡፡
- እንደዚሁም ትርጓሜው ሕገ መንግስት በመንግስት ስልጣን ላይ ገደቦች የሚጥልና መንግስት ስልጣኑን እንዴትና በምን መንገድ መጠቀም እንዳለበት ገዢ የሆነ ደንቦች የሚያስቀምጥ የህግ ክፍል እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከተው ሕገ መንግሥት በዋነኛነት አንዲት አገር ወይም አንድ መንግሥት የሚተዳደርባቸው መሰረታዊ መርሆዎችና ደንቦች የሚይዝ የህግ ማዕቀፍ እንደሆነ የሚገልፅ ሲሆን የሕገ መንግሥት ፅንሰ ሀሳብን በአጠቃላይ ስንመረምር፡፡

- ሕገ መንግሥት አንዲት አገር የምትመራበትና መንግስት የሚተዳደርበት መሰረታዊ ህግ መሆኑን፣
- ህገ መንግሥት እንደየአገሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ በፅሁፉ ተጠቃልሎ በህገ መንግስትነት የታወጀ ወይም በረዥም ጊዜ ልምድና በህግ የዳበሩ አሴቶችና መርሆዎች ሊሆን እንደሚችል፣
- የተፃፈም ሆነ ያልተፃፈ ሕገ መንግሥት የመንግስትን አወቃቀር፣ የመንግስት አካላትን አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር የሚወስኑ ገዢ መርሆችንና ድንጋጌዎችን የሚያካትት መሆኑን፣ እና
- ሕገ መንግሥት የመንግስት ሉአላዊ ስልጣን ምንጭና መሰረት እንደዚሁም የመንግስት ወሰንና ገደብ የሚወስኑ መርሆችና ድንጋጌዎችን የሚይዝና መንግስት ስልጣኑን ስለሚጠቀምበት አግባብ የሚደነግግ የሕግ ክፍል እንደሆነ ፣ እንደዚሁም
- ሕገ መንግሥት በመንግስትና በዜጎች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት በተለይም መንግስት ለዜጎቹ ማክበርና ማስከበር ስላለበት ሰብዓዊ መብቶች ይዘት የአፈፃፀም ስርዓት መሰረታዊ መርሆችን የሚይዝ በፅሁፍ የታወጀ ወይም በልምድ የዳበረ የህግ ማዕቀፍ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በማናቸውም አገር የሚገኝ ሕገ መንግሥት ከሞላ ጐደል ከላይ የተገለፁትን መሰረታዊ ነጥቦች የሚያሟላ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥትም እነዚህን መሰረታዊ ሀሳቦች አካትቶ የሚይዝ በፅሁፍ የተቀረፀ ሕገ መንግሥት እንደሆነ የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ሀሳቦች ከሌሎች ህግጋተ መንግስት ጋር የሚጋራ ቢሆንም ከነዚህ መሰረተ ሐሳቦች በተጨማሪ አንድ ለየት ያለ ባህሪ አለው፡፡ ይኼውም በሕገ መንግስቱ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ጥቅማቸውን፣ መብታቸውንና ነጻነታቸውን በጋራና በተደጋጋፊነት ለማሳደግና አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመገንባት ያስችላቸው ዘንድ ያፀደቁት የቃል ኪዳን ስምምነት ሰነድ መሆኑ ነው፡፡

ሕገ - መንግስት በዜጐችና በመንግስት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚወስን ህግ ነው፡፡ ሕገ መንግስት የመንግስትን ስልጣንና የዜጐችን መብትና ነፃነት ለይቶ የሚደነግግ ሰነድ ነው፡፡ በአንቀፅ 9 (ዘጠኝ) ላይ እንደተመለከተው ህገ መንግስቱን የሚቃረን ማንኛውም ህግ ልማድ እንዲሁም መንግስታዊ ውሣኔ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የአንድ አገር ዜጐች በአንድ መንግስት ጥላ ስር ሲተዳደሩ ምን መብት ምንስ ግዴታ ይኖራቸዋል? የመንግስትስ ስልጣንና ተግባር ምንድን ነው? መንግስትስ ስልጣንና ተግባሩን የሚያከናውነው በምን አኳኋን ነው? እነዚህ አበይት ጉዳዮች በህገ መንግስቱ ተለይተው የተቀመጡ ናቸው፡፡ ህገ መንግስት በበታች ህጐች ልማዷች ወይም አሰራሮች የሚጣስ ከሆነ የዜጐች መብትና ግዴታ የመንግስት የስልጣን ገደብና የአሰራር ዋስትና አጡ ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ (1) “ህገ መንግስት የበላይ ህግ ነው” በማለት የደነገገው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሕግ እንዲያወጣ በህገ መንግስቱ ስልጣን በተሠጠው የመንግስት አካል ፀድቆ ከግንባት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለ ህግ ነው፡፡ ይህ ህግ የህጐች ሁሉ የበላይ የሆነው ህገ መንግስት መሠረት አድርጐ የተዘጋጀ ነው፡፡ የወንጀል ህጉ ዓላማና ግብ በሕገ መንግስቱ ላይ የደነገጉትን የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በማስከበር ዙሪያ ከፍተኛ ሚና አለው እያንዳንዱ ዜጋ ወይም የመንግስት አካል በህገ መንግስቱ ላይ የተጣለውን ግዴታ ካልተወጣ እና ከጣሰ የወንጀል ህጉ አስፈላጊውን ምላሽ ይሰጣል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ህገ መንግስቱ እና የወንጀል ህጉ ያላቸውን ትስስር በዝርዝር እንመልከታለን፡፡

መንግሥት የህብረተሰብን ሠላምና ፀጥታ እንዲሁም የግለሰብን መብትና ነፃነት የማስከበር ሃላፊነት አለው፡፡ ይሄንን ሃላፊነት ህገ መንግስቱ በሚፈቅደው እና በሚያዘው መሠረት ተገባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡ ከእነዚህ እርምጃዎች አንዱ የወንጀል ህግ መደንገግ እና ይህንን ህግ የተላለፉ ሰዎች ወደ ህግ ማቅረብ ይጨምራል፡፡

በእነዚህ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ንፁህ ግለሰቦች ሣይጐዱ የመንግስትና የህዝብ ጥቅም ሣይስተጓጐል ጥፋተኞች እንዲቀጡና ከጥፋታቸው እንዲማሩ ማድረግ የመንግስት ሃላፊነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእነዚህ ህገ መንግስታዊ መርሆች ዋና አላማ መንግስት ከለይ የተገለፀውን ሃላፊነት ሲወጣ ሊያልፈ የማይችለውን ገደብ ማበጀት ነው፡፡ በአጠቃላይ ህገ መንግስት በባህሪው መብቶችና ግዴታዎችን በጥቅል መልኩ የሚያስቀምጥ ሰነድ ነው፡፡ የወንጀል ህግ ደግሞ በህገ መንግስቱ ውስጥ ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶችና ነፃነቶች ተግባራዊ ማድረጊያ መንገድ ነው፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

ሕገ መንግሥቱ በተግባር እንዲተረጎም የወንጀል ሕግ ሊጫወት ስለሚችለው ሚና መርምሩ፡፡ ይህ ሁኔታ የሚገለጽባቸውን ሁኔታዎች በምሳሌነት የተወሰኑትን በማንሳት ተወያዩበት፡፡

ክፍል ሁለት - <u>የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የሚመራባቸው መርሆዎች</u>

ንዑስ ክፍል አንድ - <u>የሕጋዊነት መርህ</u>

ይህ መሰረታዊ የወንጀል ህግ መርህ በኢ.ፌዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 2 ላይ የተመለከተ ሲሆን የተለያዩ ጉዳዮችን በስሩ አካቶ ይዟል። የወንጀል ሕግ ስለ ልዩ ልዩ ወንጀሎችና ወንጀል አድራጊዎች ላይ ስለፈፀሙት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች በዝርዝር ይደነግጋል። ፍርድ ቤት ሕገወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደወንጀል ሊቆጥረው እና ቅጣት ሊወስንበት አይችልም። ፍርድ ቤቱ በሕግ ከተደነገጉት በቀር ሌሎች ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን አይችልም። እንዲሁም በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሰላል በማለት ወንጀልነቱ በግልፅ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት ፍርድ ቤት እንደወንጀል ሊቆጥር አይችልም።

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች ፍርደ ቤት ሕጉን እንዳይተረጉም አያግዱትም። የሕጉ አነጋገር አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ለማረጋገጥ እንዲቻል ሕግ አውጪው ባቀደው ትርጉምና በሕግ መንፈስ መሠረት ፍርድ ቤቱ መተርጎም አለበት።

በወንጀል ህጉ የሚያስቀጡ የተባሉ ድርጊቶች፣ ቅጣታቸው እና ሊወሰድ የታሰበው የጥንቃቄ እርምጃዎች በሙሉ በማያሻማ መልኩ በግልፅ መቀመጥ አለባቸው። ይህ የሕግ ግልፅነት ካለ ስለወንጀሎች እና ቅጣታቸው በቅድሚያ ለህብረተሰቡ ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስችላል። በተጨማሪም በዘፈቀደ የሚሰሩ ስራዎች ያስቀራዳል፤ ፍርድ ቤቶች በሕጉ ብቻ እንዲመሩ ያደርጋል። በፍትህ ስርዓት ውስጥ ያሉ ሁሉም ወገኖች ስራቸውን በአግባቡ ሕጉ ባስቀመጠው መንገድ እንዲያከናውኑ ይረዳቸዋል። በዚህ መርህ መሰረት በሕግ በግልፅ ካልተደነገገ በስተቀር ወንጀል የለም። በአንቀጽ 2(1) እንደተቀመጠው ወንጀል መሆኑ በግልፅ ካልተቀመጠ ማንኛውም ሰው ለፈፀመው ድርጊት ምንም እንኳን ድርጊቱ ግብረ-ገብነት የጐደለው ቢሆን ተጠያቂ አይደለም።

እንዲሁም በሕጉ በግልፅ የተቀመጠውን የወንጀል ድርጊት የፈፀመው ሰው የሚቀጣው ሕጉ ባስቀመጠው መሠረት ነው፤ ለተላለፈው ድርጊት የተቀመጠውን ቅጣት ብቻ ይቀጣል፡፡ እነዚህ ሁለት አባባሎች በአጭር ሲቀመጡ በሕግ በግልፅ ካልተደነገገ ወንጀል የለም፣ እንዲሁም በሕግ በግልፅ ካስቀመጠው በስተቀር ቅጣት የለም የሚሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ህግ አውጪው በአንድ አገር ውስጥ ያለ ህዝቦች የሚተዳደሩበትንና ግንኙነታቸውን የሚመሠረቱበትን ህጐች የማውጣት ስልጣን ሲኖረው ህግ ተርጓሚው አካል ወይም ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች ሕግ አውጭው በደነገጋቸው ብቻ ውሣኔ ይሰጣሉ፡፡ በዚህም መሠረት አስቀድሞ በህግ ያልተመለከተን ጥፋት ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት አንደ ሕግ መጣስ ሊቆጥረው አይቻልም፡፡ በወንጀል ህጉም ከተወሰኑት ቅጣቶች በስተቀር ሌላ ቅጣት መጣል አይቻልም፡፡

አንድ ሰው ላሣየው ባህሪ ጥፋተኛ ለማድረግ መጀመሪያ ባህሪው ያልተፈቀደ እና ወንጀል እንደሆነ ማስጠንቀቅ መሠረታዊ ስራ እንደሆነ አንቀፅ 2 ላይ የተቀመጠው ህጋዊነት መርህ ያስረዳል፡፡ ጥፋት መሆኑን ሳይነገረው ወይም ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠው ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም፡፡ ማንኛውም ህግ የተጨባጭነት ባህሪይ ሊኖረው ይገባል፤ በተለይም የወንጀል ህግ፡፡ ሰዎች ህግን ከመጣስ እንዲቆጠቡ ቢጥሱም የሚከተላቸውን ቅጣት አውቀው አንዲገቡበት የተወሰነ የታወቀና የተጨበጠ ህግ መኖር አለበት፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት - <u>የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ</u>

በሕግ በሌላ አካኋን ካልተገለፀ በስተቀር ለአንድ ወንጀል በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው የቅጣት ወለልና ጣራ ውጭ ቅጣት ሊጣል አይችልም፡፡ እንዲሁም ለአንድ የወንጀል ድርጊት ሊጣል የሚችለው ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ከተፈፀመበት ወቅት አስቀድሞ በተደነገገ የወንጀል ድንጋጌ በተመለከተው መሠረት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአገራቱ የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ የሆነው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 “ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም፡፡ እንዲሁም ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣራ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም

ሰው ላይ አይወሰንም" ይላል። ይህ ድንጋጌ ሁለት ዓይነት መሠረታዊ ውጤቶችን ያስከትላል። እነዚህም አንድ ድርጊት በሚፈፀምበት ወቅት ድርጊቱ በጊዜው የማያስቀጣ ከነበረ ይኸው አስቀድሞ የተፈፀመው ድርጊት ከጊዜ በኋላ በወጣ ሕግ ወንጀል ነው ሊባል አይችልም። በተጨማሪም ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ወንጀል ቢሆንም እንኳ ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በሚፈፀምበት ወቅት ተፈጻሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በደነገገው የቅጣት ጣራ መሠረት መሆን አለበት። ስለዚህም ከድርጊቱ በኋላ የወጣ ሕግ የቅጣት ጣራውን ከፍ ቢያደርገው ይህ ቅጣት ሕጉ ከመታወጁ በፊት ለተፈፀመ ወንጀል ተፈጻሚ መሆን የለበትም።

ስለዚህም አንድ ህግ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ማንም ሰው ህግን የጣሠ እንደሆነ የሚፈረደው በዚያው ህግ መሠረት ነው። ነገር ግን ወንጀሉ የተሠራው የቀድሞው ህግ ይሰራበት በነበረ ጊዜ እንደሆነ ፍርዱ የሚፈፀመው በቀድሞው ህግ መሠረት ነው። ስለዚህ የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራባቸው ድንጋጌች ሁለት አይነት ናቸው። አንደኛው አንድ ህግ ከመውጣቱ በፊት እንደ ወንጀል ይቆጠር ያልነበረ ድርጊት ቢፈፀም ሆኖም ግን በአዲሱ ህግ መሠረት እንደዚህ አይነት ድርጊት የሚያስቀጣ ቢሆን አድራጊው ህጉ ከመፅናቱ በፊት ለፈፀመው ተግባር በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም። ሁለተኛው አንድ የቆየ የቅጣት ህግ በአዲስ ቢተካ አዲሱ ህገ ከመውጣቱ በፊት የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች የሚዳኙት በተሻረው ህግ ድንጋጌዎች እንጂ በኋለኛው ህግ አይደለም። በማንኛውም መልኩ ህግ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች ላይ እንጂ ባለፉት ላይ ተፈፃሚነት ሃይል የለውም። ይህ መሠረታዊ ድንጋጌ ሰዎች ከአሁን በፊት የሚያውቁት ህግ ብቻ የመዳኘት መብት ይሰጣቸዋል፤ ካልተጠበቀና ካልታሰበ ቅጣት ያድናቸዋል። ህጉ ሁሌም አብሮአቸው እንዲኖር እንዲያውቁትና እንዲጠነቀቁበት ካልሆነም ደግሞ የሚደርስባቸውን የቅጣት ደረጃ ለመገመት እንዲችሉ ይረዳቸዋል።

አንድ የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመ በኋላ የሚወጡ የወንጀል ድንጋጌዎች ለዚያ ዓይነት ወንጀሎች ቀደም ሲል ተደንግጎ የነበረውን ቅጣት በተለያዩ መንገድ ሊያከብዱት ይችላሉ። ይኸውም ድርጊቱ ቀደም ሲልም ሆነ አሁን ወንጀል ቢሆንም ከድርጊቱ በኋላ የወጣው የወንጀል ድንጋጌ የቅጣቱን ከፍተኛ ጣራ በማሳደግ፣ ወይም የቅጣቱን ዝቅተኛ ወለል ከፍ በማድረግ ወይም በአማራጭ ተቀምጠው የነበሩ የቅጣት ዓይነቶችን በማጣመር የወንጀል ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ሕጉ ላይ ተመልክቶ የነበረውን ቅጣት አክብዶት ሊሆን ይችላል። ሆኖም

በየትኛውም መንገድ ቅጣቱ እንዲከብድ የተደረገበት ሁኔታ ቢኖር ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ከተቀመጠው የቅጣት መጠን ውጭ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት ሊወሰንበት አይችልም፡፡

አንድ ህግ ይህኛውን ወይም ያኛውን ሰው ለመቅጣት ብሎ የሚወጣ ከሆነ ሁሉን አቀፍ ባህሪዩን አጣ ማለት ነው፡፡ አንድ ህግ እንዲፀና ከመደረጉ በፊት የተሠራ ስራ ሲኖርና ህግን እንደመጣስ ያልተቆጠረ ሲሆን አዲስ በወጣው ህግ ሊያስቀጣ አይችልም፡፡ እንዲሁም የህግ መጣስ ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ባልተፃፈ ቅጣት ሊፈርድ አይችልም፡፡ አንድ ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ በፊት “ወንጀል ሆኖ ያስቀጣል” ተብሎ ቀደም ሲል ተደንግጐ ካልቆየና ተከሣሹም ለፍርድ የሚቀርብበት ህግ በድርጊቱ ፍፃሜ በፊት በህግ መልክ ተቀርፆ ካልቆየና ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላ አድራጊውን ለመቅጣት ሲባል ሌላ ህግ ከወጣ በህገ መንግስቱ መሠረት ተፈፃሚነት የለውም፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22 ድንጋጌ መሠረት አስቀድሞ ወንጀል መሆኑ ባልተደነገገ ድርጊት ማንኛውም ሰው ሊቀጣ አይችልም፤ እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ከነበረው የቅጣት ጣራ በላይ ሊቀጣ አይችልም፡፡ ይህ ሕገ መንግሥታዊ መርሕ በአ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5 ላይም ተካትቶ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህም አንጻር የአዲሱ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚነት ሕጉ ሥራ ላይ ከዋለበት ከግንቦት 01 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ነው ማለት ነው፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ድርጊት በአዲሱ የወንጀል ሕግ ወንጀል ነው ቢባልም በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ግን በወንጀልነት ያልተፈረጀ ድርጊት የነበረ ከሆነ ድርጊቱ የተፈፀመው ከግንቦት 01 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት ከሆነ በወንጀል ሊያስጠይቅ አይችልም፡፡ እንዲሁም ድርጊቱ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ወንጀል ስለመሆኑ የተደነገገ ቢሆንም እንኳን ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ተፈጻሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በደነገገው የቅጣት ጣራ እና የቅጣት ወለል መሰረት መሆን አለበት፡፡

አንድ ድርጊት በቀድሞው ህግ ስር ያስከትል የነበረው የቅጣት ክብደት በሌላ አዲስ ህግ የተጨመረ እንደሆነ ጥፋተኛው የሚቀጣው ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈፃሚ በነበረው ቅጣት ነው፡፡ ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈፃሚ ከነበረው ቅጣት ጣራ

በላይም አይፈፀመበትም። ይህ የወንጀል ቅጣት በተከሣሽ ላይ የከበደ ቅጣት ለማስፈረድ በየጊዜው እንደ ገበያ ዋጋ ከፍና ዝቅ የሚል አለመሆኑን ያመለክታል። ዋናው ጥያቄ አንድ ሰው ወንጀል በሚፈፅምበት ጊዜ የነበረው ህግ የሚደነገገው የቅጣት ጣሪያ የት ድረስ ነው? የሚለው እንጂ ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የወጣ (አዲስ) ህግ የሚደነገገው የቅጣት ጣሪያ የት ድረስ ነው? የሚለው አይደለም።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ማለትም አንድ የወንጀል ሕግ ከመውጣቱ በፊት ለተፈፀመ ድርጊት ተፈጻሚነት የለውም የሚለው አጠቃላይ መርሕ ቢኖርም በተለዩ በሕግ በተፈቀዱ ልዩ ሁነታዎች (exceptions) ግን የወንጀል ሕጉ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ይችላል። እነርሱም፡-

1. አዲሱ የወንጀል ሕግ ከቀድሞው ሕግ ይልቅ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቃልልለት በሚሆንበት ጊዜ ተከሳሹ ወንጀሉን በፈፀመበት ወቅት ሥራ ላይ ያልነበረ ሕግ ቢሆንም ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

2. አዲሱ የወንጀል ሕግ ከወጣ በኋላ በቀድሞው ሕግ መሰረት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰኑት የቀድሞውን ሕግ መሰረት በማድረግ ሳይሆን በአዲሱ ሕግ መሰረት ነው። ማለትም የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረነት ጊዜ ቢሆንም ውሳኔው የተሰጠው አዲሱ የወንጀል ሕግ ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰኑት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ይሆናል ማለት ነው።

3. የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ክስ የማቅረብና እና ቅጣት ቀሪ የመሆን የይርጋ ጊዜ የሚታሰበው (የሚሰላው) አዲሱ የወንጀል ሕግ በሚደነግገው መሠረት ነው።

4. በቀድሞው ሕግ መሠረት የተሰጡ ፍርዶች የሚፈፀሙት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ነው።

5. የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ለተፈፀመ ወንጀል የሚሰጥ አስቀድሞ በገደብ ወንጀለኛን መልቀቅና በአመክሮ ከእስር መፍታት ውሳኔ የሚወሰነው አዲሱ የወንጀል ሕግ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በመጠቀም ነው፡፡ እንዲሁም

6. በቀድሞው ሕግ መሠረት የተፈረደባቸው ሰዎች የወንጀል ሪከርዳቸው የሚሰረዘውና የሚሰየሙት አዲሱ የወንጀል ሕግ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በመጠቀም ነው፡፡

ንዑስ ክፍል ሦስት - <u>ለአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ</u>

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 23 ላይ “ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም” በማለት ተደንግጓል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግም እንዲሁ በተመሳሳይ አንድ ሰው በአንድ ወንጀል ሁለት ጊዜ ሊከሰስም ሆነ ሊቀጣ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡

አንድ ወንጀል ከአንድ ጊዜ በላይ እንደማያስቀጣ በሕገ መንግሥቱም ሆነ በመሠረታዊ የወንጀል ሕጉ ውስጥ እንዲደነገግ ያስፈለገበት በቂ ምክንያት አለ፡፡ በአንድ የወንጀል ሕግ ውስጥ እያንዳንዱ ወንጀል ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚያስከትል በዝርዝር የተደነገገ በመሆኑ አንዱ ለተፈፀመ ወንጀል የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሕግ አውጪው በቂ ወይም ተመጣጣኝ ነው ብሎ የገመተውን ቅጣት በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ስለዚህም አንድ ወንጀለኛ በአንድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ቅጣት ተወስኖበትና ቅጣቱንም ፈፅሞ እያለ ያንኑ ሰው ለዚያው ወንጀል መልሶ መክሰሱ ወይም መቅጣቱ በሕብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍ ያለ ቀውስን መጋበዝ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በአንድ ወንጀል ተከሰው ቅጣታቸውን የጨረሱ ወይም ተከሰው ነፃ የወጡ በዚያው ጉዳይ እንደገና ይከሰሱ ቢባል የወደፊት ኑሯቸውን ያለ ሥጋት መምራት አይችሉም፡፡ ስለሆነም መርሁን በሕገ መንግሥቱና በመሠረታዊ የወንጀል ሕጉ ላይ መደንገጉ የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ ይረዳል፡፡ ዜጎች በሕጉና በሥርዓቱ ላይ አመኔታ እንዲኖራቸውም ያደርጋል፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

(1) የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6 ሕጉ ከመፅናቱ በፊት አንድ ሰው ለፈፀመው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው ህግ ይልቅ ይሄኛው (አዲሱ ሕግ) ቅጣት የሚያቃልልለት ከሆነ በዚህ ህግ መሠረት ቅጣት ይጣልበታል ይላል። ይህ አባባል ከዋናው የወንጀል ህግ መርህ "የወንጀል ህግ ወደ ኃላ ተመልሶ አይሰራም" ከሚለው በልዩነት የተቀመጠ ነው። በዚህ መሠረት ለወንጀለኛው ይጠቅማል በማለት ቀደም ያልነበረ ቅጣት መፈፀም የህጋዊነት መርህን አይቃረንም?

(2) "አንድ ጥፋተኛ የቅጣት ውሣኔ ተበይኖበት ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ይቅርታ ከተደረገለት በኋላ በማናቸውም ጊዜ በይቅርታ የተነሣለትን ቅጣት እንዲፈፅም አይደረግም፤ ካልሆነ በአንድ ጉዳይ ድጋሜ ቅጣት እንደተፈፀመበት ይቆጠራል።" በአባባሉ ትክክለኛነት ላይ ተወያዩበት።

(3) በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 7 መሠረት አንድ የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው የቀድሞው የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ጊዜ ቢሆንም ውሳኔው የተሰጠው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰኑት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት ሳይሆን በወንጀል ሕጉ መሠረት ስለመሆኑ ይደነግጋል። በዚህም መሠረት ለምሳሌ አንድ ሰው ባለው የምግብ ድርጅት አማካኝነት የሚያቀርበው ምግብ በተደጋጋሚ ችግር የሚፈጥር ቢሆን እንደጥንቃቄ እርምጃ ምንም እንኳን ወንጀሉ የተፈፀመው በቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ቢሆንም በወንጀል ሕጉ መሠረት ምግብ ቤቱ እንዲዘጋ ሊወሰን ይችላል ማለት ነው። ይህ ወንጀሉ በተፈፀመበት ወቅት ያልነበረን ሕግ ተፈጻሚ የማድረግ ሁኔታ ያለውን አግባብነት መርምሩ።

(4) በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34(3) መሠረት የሕግ ሰውነት መብት ያለው ድርጅት መቀጣት የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞችን ቅጣት እንደማያስቀረው ይደነግጋል። ለአንድ

ጥፋት ድርጅቱ ተጠያቂ ከሆነ እንደገና በድጋሚ ድርጊቱን የፈፀመውን የድርጅቱን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በወንጀል ተጠያቂ ማድረጉ የወንጀል ሕጉ ያስቀመጠውን መርህ አይጻረርም? ዓላማውስ ምንድን ነው?

(5) ወ/ሮ አሰለፈች እና አቶ ደስታ ባልና ሚስት ሆነው ሲኖሩ በመካከላቸው በነበረው አለመግባባት መነሻ ብዙ ጊዜ ወ/ሮ አሰለፈች ባለቤታቸን እገድልሀለሁ በማለት ትዝትበት ስለነበር ሁኔታዋን በማፍራት ለፖሊስ ሪፖርት አቶ ደስታ አድርጎ ነበር። በዚህ ሁኔታ እንዳሉ አቶ ደስታ በመሰወሩ ወ/ሮ አሰለፈች ተጠርጥራ ክስ ቀርቦባት አለመግባባታቸውን ያዉቁ የነበሩ ሰዎች እንዲሁም አቶ ደስታ ለፖሊስ አመልክቶ የነበረ መሆኑ በማስረጃነት ቀርቦ ወ/ሮ አሰለፈች ተብላ የተወሰነውን ቅጣት ፈጽማ በአመክሮ ከወጣች በኋላ ባሏ በህይወት መኖሩን በማረጋገጧ ያለበት ቦታ ድረስ በመሄድ ገደለችው። የወንጀል ምርመራው ተጣርቶ ቢቀርብ ለአንድ ጥፋት አንድ ሰው ሁለት ጊዜ አይከሰስም፣ አይቀጣምም ከሚለው መርህ አኳያ እንዴት ይታያል?

ምዕራፍ ሁለት - <u>በአንዳንድ የወንጀል ድንጋጌዎች ዙሪያ የሚስተዋሉ የትርጉምና የአፈጻጸም ችግሮች</u>

ይህን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ ሰልጣኞች፡-

1. የወንጀል ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ መርሆዎች ዙሪያ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸምና የትርጉም ችግሮችን ይለያሉ፣
2. በዝርዝር ወንጀሎች ላይ ያሉ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ መሠረታዊ የአፈጻጸምና የአተረጓጎም ችግሮችን ይለያሉ፣
3. ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል ወጥ፣ ተገማችና ተመራጭ የሆነ ትርጉም ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ይኖራቸዋል፡፡

ክፍል አንድ - <u>በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የሚስተዋሉ አንዳንድ የትርጉምና የአፈጻፀም ችግሮች</u>

ንዑስ ክፍል አንድ - <u>ወንጀልን የሚያቋቋሙ ቅድመ ሁኔታዎች እና በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት</u>

በብዙ አገሮች የወንጀል ሕጎች እንደሚታወቀው ሁሉ በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረትም ለወንጀል መቋቋም መሠረት የሚሆኑት ነጥቦች (ነገሮች) ሦስት ናቸው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 ላይ እንደተደነገገው እነዚህም ነጥቦች አታድርግ የተባለውን አድርጎ መገኘት ወይም ደግሞ አድርግ የተባለውን ሳያደርጉ መቅረት (ድርጊት ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል)፣ ድርጊቱ እንደሚያስቀጣ በወንጀል ሕግ በግልጽ መደንገጉ ፈጻሚው ድርጊቱን የፈፀመው አስቦ ወይም በቸልተኝነት መሆኑ ናቸው፡፡

ድርጊት በግዙፍነት የሚታይ ሲሆን ምንም እንኳን የሀሳብ ውጤት ቢሆንም ወንጀል ለመፈፀም ማሰብ ብቻውን በድርጊት እስካልተገለፀ ድረስ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም፡፡ በድርጊት ያልተገለፀ ሀሳብ ተጠያቂነት የማያስከትልበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ሰው

ምን እንደሚያስብ ማረጋገጥ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ በድርጊትና በሀሳብ መካከል ርቀት ያለ በመሆኑ ወንጀል ለመፈፀም ያሰበ ሁሉ ሀሳቡን በድርጊት ይገልጻል ተብሎ ሊገመት ስለማይችል ቅጣት እንዲጣልበት ማድረጉ የወንጀል ሕግ ዓላማን ለማሳካት የሚያስችልም አይሆንም፡፡ ሥለዚህም አንድ ሰው ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ ቢኖረውም ይኸው ሀሳቡ በድርጊት እስካልተገለፀ ድረስ በወንጀል የሚያስጠይቅ አይሆንም፡፡

አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ለማለት ድርጊቱ ሕገ ወጥ ስለመሆኑና የሚያስቀጣ ስለመሆኑ በሕግ ተደንግጎ መገኘት አለበት፡፡ ይህ ነው ሕጋዊ ፍሬ ነገር ተብሎ ወንጀልን ከሚያቋቁሙት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንደኛው ነጥብ ሆኖ በወንጀል ሕጉ ውስጥ የተመለከተው፡፡

አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ለማለት ሦስተኛው ነጥብ ሞራላዊ ፍሬ ነገር ተሟልቶ መገኘት ያለበት ሲሆን ይህ የሀሳብ ክፍልን የሚመለከተው ሁኔታ ድርጊቱ በተፈጸመበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ከወንጀል ሕግ መርህ አኳያ ጥፋተኝነት ሳይኖር ቅጣት አይኖርም፤ ይህ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የሚገለጽ የሀሳብ ሁኔታ ደግሞ መኖሩ መረጋገጥ ያለበት ወንጀለኛው ድርጊቱን በፈፀመበት ወቅት ነው፡፡ ድርጊቱን ከመፈፀሙ በፊት ወይም ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላ የፈፀመውን ተግባር ወይም ድርጊቱ ያስገኘውን ውጤት አስመልክቶ ያለው ወይም የነበረው ሀሳብ የድርጊቱን ፈጻሚ አጥፊነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ነገሮች አይደሉም፡፡

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተለዬ በአንቀጽ 23(3) ላይ ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ ወንጀልን ለማቋቋም ሦስት መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች (ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች) በአንድነት ተሟልተው መገኘት ያለባቸው ቢሆንም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ አስቀምጧል፡፡ ሆኖም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 የተመለከቱት ነጥቦች ግምት ውስጥ ገብተው ነው፡፡ በአንቀጽ 34 መሠረት፡-

- የወንጀል ተጠያቂነቱ የሚመለከተው ማንኛውም ድርጅት ሳይሆን የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡

- የመንግስት አስተዳደር አካላት የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ቢሆኑም በወንጀል ሊጠየቁ ግን አይችሉም፡፡ ከአስተዳደር አካላት የመንግስት ተቋማት ግን በወንጀል ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡
- የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ሊጠየቅ የሚችለው በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል በግልጽ ተደንግጎ በሚገኝበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡
- የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ ቢሆኑም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ሊጣልባቸው የሚችለው ዋና ቅጣት መቀጮ ነው፡፡ በእርግጥ ተጨማሪ ቅጣቶች ሊጣሉባቸው ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ከዋና ቅጣቶች በተደራቢ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድርጅቶች እንዲዘጉ፣ እንዲታገዱ ወይም እንዲፈርሱ ሊወሰን ይችላል፡፡
- የሕግ የሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች መጠየቃቸው ድርጊቱን በቀጥታ የፈፀሙት ሰዎች ያለባቸውን የወንጀል ተጠያቂነት አያስቀርም፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በወንጀል መርህ መሠረት ጥፋተኝነት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ የሚተላለፍ፣ ወይም አንዱ ለሌላው ሰው የሚያውሰው አይደለም። የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የእራሱ የሕግ ሰውነት ያለው ሰው ነው። የተፈጥሮ ሰዎች በፈጸሙት ድርጊት ምክንያት የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት እንዲኖራቸው መደረጉ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መርህ አይጻረርም? ይህ ሌላ ሰው ለፈፀመው ድርጊት ተጠያቂ ማድረግ (vicarious liability) አይሆንም?

2. አንድ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሲቋቋም የሚቋቋምበት ዓላማ ሕጋዊ እና የተፈቀዱ መሆናቸው በሚመለከተው አካል ተረጋግጦ ነው። በመሠረቱ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በእራሱ ግዑዝ በመሆኑ የሚንቀሳቀሰው በተፈጥሮ ሰዎች አማካኝነት ቢሆንም የተቋቋመበት ዓላማ በዝርዝር የሚታወቁ በመሆናቸው ከዓላማው ውጭ የተከናወኑ ተግባሮች የወንጀል ባህርይ ካላቸው ፈጻሚዎቹ የተፈጥሮ ሰዎች ከሥልጣናቸው ውጭ የፈጸሙ (ultravires) በመሆናቸው ሊጠየቁ የሚገባቸው ፈጻሚዎቹ ማለትም የድርጅቱ መሪዎች እና ሠራተኞች ናቸው እንጅ ድርጅቱ መሆን የለበትም የሚሉ አሉ። ይህን አመለካከት እንዴት ያዩታል?

ንዑስ ክፍል ሁለት - <u>የምክንያትና ውጤት ግንኙነት መርህ</u>

የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖረው በአንድ ድርጊትና ድርጊቱን በተከተለው ውጤት መካከል የምክንያትና ውጤት ግንኙነት መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በምክንያትና በውጤት መካከል ግንኙነት አለ የሚባለው ደግሞ በነገሮች የታወቀ ወይም የተለመደ ሂደት አንድ ድርጊት ተከትሎት የመጣውን ውጤት ማስከተል የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይህ ምክንያት ውጤቱን የሚያስከትለው ሁሌ ማለት ፍፁም በሆነ ሁኔታ ላይሆን ይችላል፡፡ በአብዛኛው ድርጊቱ ተከትሎት የደረሰውን ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ግንኙነቱ ስለመኖሩ በቂ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በጥይት አንድን ሰው ጭንቅላቱን መምታት ሞትን ያስከትላል፡፡ ይህ በነገሮች የተለመደ ሂደት የሚታወቅ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሌም እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች ሞትን ያስከትላሉ ማለት አይደለም፡፡ የማያስከትሉበት አጋጣሚ ሊኖርም ይችላል፡፡ ሆኖም እንዲህ ዓይነት ልዩ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ የሚችሉ በመሆናቸው ምክንያት ብቻ በመሰል ድርጊት እና ድርጊቱን ተከትሎ በተከሰተው ሞት መካከል ግንኙነት የለም ሊባል አይችልም፡፡

የወንጀል ተጠያቂነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለመወሰን በምክንያትና በውጤት መካከል ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ቢሆንም የወንጀል ሕግ ሁሌም የሆነ ውጤት ማለትም ጉዳት ሲደርስ ብቻ ድርጊት ፈጻሚውን ለመቅጣት የምንጠቀምበት ነው ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ ድርጊቶች ውጤት ባይስከትሉም የወንጀል ተጠያቂነትን ግን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ለምሳሌ አንድ ሰው ድርድ ቤት ቀርቦ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ቢሰጥ ቃሉ ሀሰት መሆኑ በፍርድ ቤቱ ታውቆ ተቀባይነት ያላገኘና የተፈለገው ውጤት ያለተገኘ ቢሆንም ድርጊቱ በወንጀል ሊያስጠይቅ ግን ይችላል፡፡

ከምክንያትና ውጤት ግንኙነት አንጻር አንዳንድ ጊዜ ለደረሰው ጉዳት ከአንድ በላይ ምክንያቶች ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ተከሣሽ የፈፀመው ድርጊት ለውጤቱ ምክንያት ነው አይደለም የሚለውን ለመወሰን ለተከሣሹ እንግዳ የሆነውን አስቀድሞ የደረሰ፣ ተደርቦ የተፈፀመ ወይም ከተከሣሹ ድርጊት በኋላ የደረሰውን ጣልቃ ገብ ምክንያት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት ለተከሣሹ እንግዳ ከሆኑት በሦስቱ የጊዜ ደረጃ ከደረሱት ልዩ ልዩ ምክንያቶች (ማለትም አስቀድሞ የደረሰ፣ የተደራረቡ ወይም ጣልቃ የገቡ

ምክንያቶች) ውስጥ አንዱ እራሱን ችሎ ማለትም የተከሣሹ ድርጊት ምንም እገዛ ሳይደርግለት አንድን ውጤት ማስከተሉ ከተረጋገጠ በተከሣሹ ድርጊትና በውጤቱ መካከል ሊኖር ይችል የነበረውን ግንኙነት ይቋረጣል፡፡ ሆኖም የተቋረጠው ድርጊት እራሱን የቻለ ወንጀል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ለዚያ ወንጀል ተከሣሹ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ከምክንያትና ውጤት ግንኙነት አንጻር በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ያልነበረ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(3) የተካተተ ጉዳይ ያለ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ልዩ ልዩ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እራሳቸውን ችለው አንድን ውጤት ማምጣት ባይችሉም ተጣምረው አንድን ውጤት ካስገኙ ሁሉም ለውጤቱ ምክንያቶች ተብሎ ተደንግጓል፡፡ አንዳቸውም ለየብቻቸው ውጤቱን አያስከትሉም ነገር በጥምረት ውጤቱን አስከትለዋል፡፡ ስለዚህም ሕጉ በውጤቱና በእያንዳንዱ ምክንያት (ድርጊት) መካከል ግንኙነት እንዳለ አድርጎ ይቆጥረዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለውጤቱ ተጠያቂ የሚሆን አንድ ምክንያት ከሌለ (ከጠፋ) በጥምር ሁሉም ውጤቱን አስከትለዋል ብሎ ሕጉ ይወስዳል ማለት ነው፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ተከሣሽ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከመገናኛ ወደ አራት ኪሎ በሚወስደው መንገድ መኪናውን ሲያሽከረክር እንግሊዝ ኤምባሲ ፊት ለፊት አካባቢ በእግሯ ትጓዝ የነበረችን ሴት ከጎኗ በኩል ይገጫትና ትወድቃለች፡፡ በዚህም ወቅት የአስፓልቱ ጠርዝ ጭንቅላቷን ያገኛታል፡፡ ተከሣሹ ከመኪናው ወርዶ ተጎጂዋን ወደ ህክምና ለመውሰድ ወደ እርሷ በመሄድ ላይ እንዳለ ከሌላ አቅጣጫ የመጣ መኪና ሟች ላይ ይወጣባታል፡፡ ተጎጂዋ ወደ ሆስፒታል ለሕክምና የተወሰደች ቢሆንም በሆስፒታሉ የሚስተናገዱ ብዙ ሰዎች የነበሩ በመሆናቸው ከሁለት ሰዓት በላይ ህክምና ሳይሰጣት ደም እየፈሰሳት ቆይታ እዛው እንዳለች ትሞታለች፡፡

   (ሀ) ከወንጀል ሕጉ አንጻር በተከሣሽ ድርጊት (የመጀመሪያውን ግጭት ባደረሰው) እና በውጤቱ (በግለሰቧ ሞት) መካከል ግንኙነት አለ ተብሎ ሊወሰድ ይችላል?

   (ለ) የተከሣሹ ድርጊትም ሆነ ሌሎች ተከትለው የደረሱ ሁኔታዎች በራሳቸው ለሞቱ በቂ ምክንያት እንዳልነበሩ ቢረጋገጥ ለግለሰቧ ሞት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው ማንኛቸው ናቸው?

2. በሚከተለው ጉዳይ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት መርምሩ፡፡

ተከሣሹ ነፍሰጡር የሆነችን ሴት በእርግጫ ሆዷ ላይ ይመታትና ሆስፒታል ለሕክምና ትወስዳለች፡፡ ሕክምናው እየተሰጣት እያለ ህይወቷ ያልፋል፡፡ ሆስፒታሉ የሰጠው የሕክምና ማስረጃ የሚከተለውን ይላል፡፡ "...ሟች ከእንብርትዋ በታች ሰምበር ነበረባት፣ ፅንስ አስወርዷታል፣ በፅንሱ መውረድ ምክንያት በማህፀንዋ ውስጥ የነበረው መግልና የቅሪት ቁርጥራጭ ተጠርጎላታል፣ በማህጸኗ ውስጥ የተነሳ አጠቃላይ የሰውነት ኢንፌክሽንም ነበረ፣ ወባም በሟች ደም ውስጥ ተገኝቷል፡፡ ኢንፌክሽኑን ለመቆጣጠር..." አልተቻለም እንደነበር ይገልፅና "ለሟች ሞት ወባም ኢንፌክሽኑም አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፣ በትክክል ለይቶ ማረጋገጥ ግን አልተቻለም" ይላል፡፡

- የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ - ለሟች ህይወት ማለፍ ምክንያት ወባ ይሁን ወይስ የሰውነት ኢንፌክሽን ስላልታወቀ ተከሣሹ ጥፋተኛ ሊሆን የሚገባው ታስቦ በተደረገ ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀል ነው፡፡
- ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ - ኢንፌክሽኑን መቆጣጠር እንዳልተቻለ የተገለፀ በመሆኑ፣ በኑሮ ልማድ ዕውቀት የነፍሰ ጡር ሆድን በእርግጫ መምታት ውርጃ

የሚያስከተል ስለሆነና ከውርጃው የተነሳ በሚች ማህፀን መግል እና አጠቃላይ ኢንፌክሽን የሚያመጣና ይህም ሞትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ ተከሣሹ በተራ አስቦ ሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ነው በማለት ወስኗል፡፡

3. “ሀ” የተባለው የአዲስ አበባ ነዋሪ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደሙ ውስጥ እንዳለ እያወቀ ከፍቅር ጓደኛው ጋር ያለጥንቃቄ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጸመ፡፡ ጓደኛው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ ቢገኝባት የ “ሀ” የወንጀል ተጠያቂነት ከምክንያት እና ከውጤት አንጻር እንዴት እንደሚታይ ተወያዩበት፡፡

ንዑስ ክፍል ሦስት - <u>የወንጀል መፈጸም ሐሣብ</u>

አንድን ሰው ለፈፀመው ድርጊት በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ ድርጊቱ በሕግ የተከለከለ ስለመሆኑና ድርጊቱን ግለሰቡ የፈጸመ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ ድርጊቱን መፈፀሙን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት የፈፃሚው የሀሳብ ክፍል ምን ሁኔታ ላይ እንደነበር ማለትም ድርጊቱ የተፈፀመው በወንጀል አጥፊነት መንፈስ ስለመሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ስለዚህም ነው ጥፋተኝነት ሳይኖር የወንጀል ተጠያቂነት አይኖርም የሚባለው፡፡

የወንጀል ጥፋተኝነት ሀሳብ በሁለት ይከፈላል፡፡ አስቦ መፈፀም ወይም አውቆ አጥፊነት እና ቸልተኝነት ናቸው፡፡ አንድ ድርጊት ታስቦ ወይም በቸልተኝነት ካልተፈፀመ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም፡፡ ማለትም በድንገተኛ አጋጣሚ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈፀመ ድርጊት ጉዳት ቢያስከትልም የወንጀል ተጠያቂነትን ግን አያመጣም፡፡

አንድ ሰው አስቦ ወንጀል ፈፀመ የሚባለው በሁለት ሁኔታዎች ነው፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ቀጥተኛ የሆነ አሳብ እና ቀጥተኛ ያልሆነ አስባ ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ቀጥተኛ የሆነ አሳብ አለ የሚባለው የድርጊቱን ውጤት በእርግጠኝነት ወይም ለእርግጠኝነት በተቃረበ ሁኔታ በማወቅ ይህ ውጤት እንዲደርስ በመፈለግ አንድ ድርጊት የተፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ሁኔታና ውጤቱን በተመለከተ ዕውቀት ፈጻሚው እንደነበረው ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ሲባል ማንም ሰው ያውቃቸዋል ተብለው የሚገመቱ ሁኔታዎች በወንጀል ፈጻሚውም ይታወቃሉ የሚል ግምት ይያዛል፡፡ ለምሳሌ የጦር መሣሪያ የሚገድል ስለመሆኑ ማንም ሰው የሚያውቀው “ተራ” ነገር በመሆኑ ወንጀል ፈጻሚውም ይኸው ዕውቀት (ግንዛቤ) እንዳለው ተደርጎ ይገመታል፡፡

ወንጀልን የሚያቋቁመው ማለትም ድርጊቶችን በወንጀልነት የሚፈርጀው የሕጉ ልዩ ክፍል የወንጀል ተጠያቂነት አለ ለማለት ውጤት መገኘት እንደሚኖርበት ባመለከተበት

ሁኔታዎች ከወንጀል ድርጊቱ የተነሳ የደረሱት ውጤቶች አስቀድመው የታዩ (የተጠበቁ) እና የተፈለጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ቀጥተኛ የሆነ አሳብ አለ ለማለት አስፈላጊ ነው። ለዚህም ሲባል ወንጀል አድራጊው የድርጊቱን ተፈጥሯዊ ውጤት ወይም በአብዛኛው ድርጊቱ የሚገኘውን ውጤት የሚያውቀው መሆኑ ከተረጋገጠ በድርጊቱ ውጤቱን ማስገኘት ፍላጎቱ (ዓላማው) ነበር ለማለት ይቻላል።

ሆኖም የሕጉ ልዩ ክፍል ድርጊቱ መፈፀሙ ብቻ የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል ወይም ድርጊቱ ውጤት ባያስከትልም ያስቀጣል ብሎ ከደነገገ ወንጀል ፈጻመው ድርጊቱን በማወቅ በእራሱ ፈቃደኝነት መፈፀሙ ወንጀሉን በቀጥታ አስቦ ፈጽሟል ለማለት በቂ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ቋንቋውንና ቃላቱን እያወቀ ክብርን የሚነካ ቃል በሌላ ሰው ላይ ከሰነዘረ የፈጻሚው ሰው ፍላጎት መስደብ (ማዋረድ) እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም ተብሎ ስለሚገመት በእርግጥ ድርጊቱ የተሰዳቢውን ክብር ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሳይቀርብበት በወንጀል ሊያስጠይቅ ይችላል።

ቀጥተኛ ያልሆነ አሳብ በስፋት የሚታወቀው “ዶለስ ኢቭንቱዋሊስ” በሚለው የላቲን ስሙ ሲሆን እንዲህ ዓይነት አሳብ አለ የሚባለው ፈጻሚው ድርጊቱ ጉዳት እንደሚያስከትል በእርግጠኝነት ወይም ለእርግጠኝነት በተቃረበ ሁኔታ በማያውቅበት ሆኖም ድርጊቱ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል እየገመተ (እያወቀ) ድርጊቱን በሚፈጽምበት ወቅት ነው። በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 58 (1)(ለ) ላይ ...“የሆነው ይሁን ብሎ ውጤቱን በመቀበል...” ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ተብሎ የተመለከተው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) ከተመለከተው ቀጥተኛ የሆነ አሳብ የተለየውን ይህን ዓይነት ቀጥተኛ ያልሆነ አሳብ ለማመልከት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

ስለዚህም ፈጻሚው በድርጊቱ ምክንያት የሚከተለው ውጤት (ጉዳት) እንዲደርስ አይፈልግም፤ ሆኖም ከድርጊቱ የሚያገኘው ግብ ያለ በመሆኑ ያን ላለማጣት ሲል ድርጊቱ ሌላ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ ጉዳቱ ቢደርስም ባይደርስም የእራሱ ጉዳይ ዓይነት አቋም በመያዝ ድርጊቱን በመፈጸሙ ይቀጥላል። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው አንዱ ነጥብ አንድን ድርጊት ለመፈፀም ያለ ፍላጎትና ውጤትን ለማስገኘት ያለ ፍላጎት ሁልጊዜም

ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል ማለትም እንደ ነገሩ ሁኔታ ድርጊቱን ለመፈፀም ያለ ፍላጎት ሁሌም ውጤቱን የማስገኘት ፍላጎት መኖሩን ላያመለክት ይችላል፡፡

የወንጀል ድርጊት ታስቦ ሲፈፀም የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ ነገር ግን በቸልተኛነትም ቢፈፀም ለቅጣት ያበቃል ተብሎ የወንጀል ሕጉ በተለይ ያስቀመጠው ድርጊት ሲፈፀም የድርጊቱን ባለቤት ለቅጣት ያበቃል፡፡ በዚህም መሠረት ቸልተኛነት እንደሚያስቀጣ ሕጉ በግልጽ ደንግጎ በሚገኝበት ጊዜ ተከሣሹ ድርጊቱን አስቦ አለመፈጸሙን በማስረዳት ብቻ ከወንጀል ጥፋተኝነት ነጻ ሊሆን አይችልም፤ ተከሣሹ ቸልተኛነት እንደነበረበት ከተረጋገጠም የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

ቸልተኛነት በሙሉ ዕውቀት የሚፈፀም ቸልተኛነት (የታወቀ ቸልተኛነት) እና ባለማወቅ የሚፈፀም ቸልተኛነት (ያልታወቀ ቸልተኛነት) ተብሎ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 59 (1)(ሀ) ላይ እንደተመለከተው አንደኛው ዓይነት ቸልተኛነት ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት በመውሰድ ወይም ባለማመዛዘን የሚፈፀም ነው፡፡ ይህ advertant or conscious negligence ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን በሙሉ እውቀት የሚፈፀም ችልተኛነት ወይም የታወቀ ቸልተኛነት ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ቸልተኛነት ሁለት ነገሮችን በአንድ ጊዜ አጣምሮ ይይዛል፡፡ የድርጊቱ ፈጻሚ የድርጊቱን ባህሪ ያውቃል፤ ውጤቱንም ይረዳል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የድርጊቱ ፈጻሚ ቸልተኛነቱን ከሙሉ ዕውቀት ጋር ፈጽሞታል ሊባል ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ግን ፈጻሚው ምንም እንኳን የፈፀመውን ድርጊት ባህሪ ቢያውቅም፤ ምንም እንኳን ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ቢረዳም ይህንኑ ውጤት የማምጣት ፍላጎት የለውም፡፡ እንዲያውም ውጤቱ እንደማይደርስ ስለሚተማመን ነው ድርጊቱን የሚፈፅመው፡፡ ፈጻሚው ወንጀሉን አስቦ እንዳልፈፀመ የሚቆጠርበት ምክንያትም የድርጊቱ ውጤት እንዲከሰት በሚል (ቀጥተኛ አሳብ) ወይም ደግሞ ውጤቱ ቢከሰትም ይከሰት በሚል (ቀጥተኛ ያልሆነ አሳብ) ድርጊቱን ባለመፈፀሙ ነው፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 (1)(ለ) ላይ እንደተመለከተው ሁለተኛው ዓይነት ቸልተኛነት ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ

ባለመገመት ወይም ባለማሰብ የሚፈፀም ነው። ይህ inadvertant or unconscious negligence ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን ባለማወቅ የሚፈፀም ችልተኛነት ወይም ያልታወቀ ቸልተኛነት ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። እንዲህ ዓይነት ቸልተኛነት ፈጻሚው ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ሳያስተውል ድርጊቱን በመፈፀሙ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበት ሁኔታ ነው። የአጥፊው ተግባር በቸልተኛነት የተፈፀመ ነው ተብሎ የሚቆጠረው የአድራጊው የግል ሁኔታ በተለይም ዕድሜው፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራው እና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ሲመዘን በጉዳዩ ሁኔታዎች ሊደረጉ ይገባል ተብሎ የሚጠበቁትን ጥንቃቄዎች ያላደረገ እንደሆነ ነው።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት በመርህ ደረጃ አንድ ድርጊት የሚያስቀጣው ድርጊቱ የተፈፀመው ታስቦ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ የአባባሉን ትክክለኛነት መርምሩ፡፡ በሌላ አገላለፅ አንዳንድ የወንጀል ድንጋጌዎች የሃጣብ ክፍሉን በግልፅ ሲያስቀምጡ ሌሎች ደግሞ ወንጀሉ የሚፈፀምበት የሃጣብ ክፍል ማለትም ታስቦ ይሁን ወይንም በቸልተኝነት ሲፈፀም የሚያስቀጣ እንደሆነ አይገልፁም፡፡ እነዚህ በግልፅ የሃጣብ ክፍሉን የማይገልፁ አንቀፆች እንዴት ነው የሚታዩት ?

2. “ጥፋተኞች ሰዎች ናቸው እንጅ ድርጊቶች በእራሳቸው ጥፋተኛ አይደሉም”፡፡ የአባባሉን ትክክለኛነት መርምሩ፡፡
3. አንድ ሰው ቸልተኛ ነው ለማለት በወንጀል እና በፍትሐብሔር የተቀመጠው መመዘኛ ልዩነት አለው? (አለው ካሉ) ለምን እንደሆነ ተወያዩበት፡፡
4. የሚከተሉትን አገላለጾች አግባብነት መርምሩ፡፡
   (ሀ) በወንጀል ቸልተኛነት አለ የሚባለው የፈጻሚው ተግባር ሚዛናዊ አስተሳሰብ/ ትክክለኛ አዕምሮ ያለው ሰው (reasonable person) በፈጻሚው ቦታ ቢሆን ኖሮ ተግባሩ የሚያስከትለውን ውጤት ይገምታል፣ ፈጻሚው ግን አርቆ ባለማሰቡ ያልተፈለገው ውጤት ደርሷል በሚል ነው፡፡
   (ለ) ከወንጀል ሀሳብ አንጻር አንድ ሰው ትክክለኛ አዕምሮ ያለው ሰው (reasonable person) ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ብቻ ቸልተኛ ነው ሊባል አይችልም፣ እንደዚሁም አንድ ሰው reasonable person ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ ስላደረገ ብቻ ቸልተኛ አልነበረም ሊባል አይችልም፡፡
5. አንድ ሰው አንድን የወንጀል ድርጊት የፈፀመው “የሆነው ይሁን” በሚል (ቀጥተኛ ያልሆነ አሳብ) ወይም ድርጊቱ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል በመገመት “አይደርሰም በሚል” (ከሙሉ ዕውቀት ጋር የሚፈፀም ቸልተኛነት) ስለመሆኑ ማወቅ ወይም ማረጋገጥ የሚቻለው እንዴት ነው?
6. በሚከተለው ጉዳይ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት መርምሩ
   - አንድ መምህር የቤት ሥራ ያልሰሩ የ2ኛ ክፍል ተማሪዎችን አስወጥቶ ተንበርክከው ከክፍሉ አንድ ጫፍ ሌላኛው ጫፍ ድረስ እንዲሄዱ ካደረገ በኋላ አንደኛቸው

የሌላኛቸውን ጆሮዎች በመያዝ እንዲጓተቱ ያደርጋል፡፡ በዚህ መሀል አንድ የዘጠኝ ዓመት ሁኔታው ከአቅሙ በላይ ይሆንና አመመኝ ሲል መምህሩ የተማሪውን ጭንቅላት (አናቱ) ላይ አንድ ጊዜ በኩርኩም በኃይል ይመታዋል፡፡ ይህ ከሆነ ከሁለት ሰዓታት በኋላ ተማሪው ከአፍንጫው ደም መፍሰስ ሲጀምር ወደ ሆስፒታል ለህክምና ይወሰዳል፡፡ ሆኖም ወድያውኑ ልጁ ህይወቱ ታልፋለች፡፡

- ዐቃቤ ሕግ በመምህሩ በቸልተኛነት ሰው መግደል የመግደል ወንጀል ክስ አቀረበ፡፡
- ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ቀላል የአካል ጉዳት አስቦ በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ ብሎ እስካሁን የታሰረው በቂ ነው በማለት ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወሰነ፡፡

7. አንድ ሰው ፍሬኑ የማይሰራ መኪናን ሲያሽከረክር ሰው ገጭቶ ቢገድል በሚከተሉት ሁኔታዎች የሚኖርበትን የወንጀል ተጠያቂነት መርምሩ፡፡

(ሀ) ፍሬኑ ችግር እንዳለበት አስቀድሞ ቢያውቅም ባለው ችሎታ በመተማመን ተሽከርካሪውን መንዳቱን የቀጠለ አሽከርካሪ፣

(ለ) ፍሬኑ ችግር እንዳለበት አስቀድሞ እያወቀ እና አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል እየገመተ ወሳኝ ቀጠሮ ስላለው ከቀጠሮው ላለመቅረት ተሽከርካሪውን መንዳቱን የቀጠለ አሽከርካሪ፣

(መ) ፍሬኑ ችግር እንዳለበት አስቀድሞ ምንም ዕውቀት ያልነበረው አሽከርካሪ፣

8. “ሀ” የተባለው የአዲስ አበባ ነዋሪ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደሙ ውስጥ እንዳለ እያወቀ ከፍቅር ጓደኛው ጋር ያለጥንቃቄ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጸመ፡፡ ጓደኛው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ ቢገኝባት የ “ሀ” የወንጀል ተጠያቂነት ወንጀል ለመፈፀም ካለ ሀሳብ አንጻር እንዴት እንደሚታይ ተወያዩበት፡፡

ንዑስ ክፍል አራት - ደጋጋሚ ወንጀለኛነት (Recidivism)

አንድ ሰው ቀደም ሲል ወንጀል መፈፀሙ ወይም ከዚሁ የተነሳ መቀጣቱ ብቻ ደጋጋሚ ወንጀለኛ አያሰኘውም፡፡ አንድ ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ማለትና በተደጋጋሚ ወንጀል የፈፀመ ነው ማለት የሚያስከትለው ውጤት የተለያዬ ነው፡፡ ደጋጋሚ ወንጀለኛነት ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በተደጋጋሚ የተቀጣ መሆን ወይም የወንጀል ሪኮርድ ያለው መሆን ግን ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው በተደጋጋሚ ወንጀል የፈፀመ በመሆኑ ምክንያት ቅጣቱ የሚከብድበት ቢሆንም በመጨረሻ ለፈፀመው ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተመለከተው ቅጣት ጣራ በማለፍ ቅጣት ሊጣልበት አይችልም፡፡ ሆኖም ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ ግን በሕጉ ልዩ ክፍል ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል ከተደነገገው ጣራ በላይ ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፡፡ አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ለማለት በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ደ.ሪ የወንጀል ሕግ የተቀመጡ ተሟልተው መገኘት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡

ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 82(1)(ለ) ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት የመጀመሪያው መመዘኛ በወንጀለኛው ላይ ከዚህ ቀደም የወንጀል ክስ ቀርቦበት ቅጣት የተወሰነበት መሆን አለበት፡፡ አዲሱን ወንጀል በፈፀመበት ወቅት ቀደም ሲል ፈፅሞት በነበረው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የወንጀል ክስ ያልቀረበበት ወይም ክስ ቢቀርብበትም ገና በጉዳዩ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔና ቅጣት ያልተጣለበት ከሆነ የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መስፈርት አልተሟላም ማለት ነው፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በዚህ የመጀመሪያ መስፈርት ላይ ያደረገው ለውጥ ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም ጥፋተኛ በተባለት ወንጀል የተቀጣው በእስራት መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ሰው በመጀመሪያው ወንጀል የተፈረደበት የገንዘብ መቀጮ፣ የግዴታ ሥራ ወይም በወቀሳና ማስጠንቀቂያ ታልፎ ከሆነ ለደጋጋሚነት ማሟያ ነጥብ አይሆንም ማለት ነው፡፡

በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት ሁለተኛው መመዘኛ ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም የተወሰነበትን ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት፤ ወይም በምህረት ወይም በአዋጅ ምህረት ቅጣቱ ከቀረለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ወንጀል የፈፀመ መሆን አለበት፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በዚህ መመዘኛ ላይም አንዳንድ ለውጦችን አድርጓል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያው መስፈርት ላይ እንደተገለፀው አጥፊው ከዚህ ቀደም የተቀጣበት ወንጀል በእስራት የሚያስቀጣ መሆን ያለበት በመሆኑ ማንኛውንም ቅጣት ሳይሆን ይህን የእስራት ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት፣ ወይም ቅጣቱ በይቅርታ ከቀረለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ወንጀል የፈፀመ መሆን አለበት (አንቀጽ 67)፡፡ እዚህ ላይ ከእንግሊዝኛው አገላለፅ ጋር እንዲስማማ ተብሎ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቀድሞው ሕግ "ምህረት" በሚል ተመልክቶ የነበረው "ይቅርታ" በሚል የተተካ ሲሆን "የአዋጅ ምህረት" የሚለው ደግሞ "ምህረት" ተብሎ መመልከቱ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ስለሆነም በቀድሞው ሕግ መሠረት አንድ ሰው የአዋጅ ምህረት (ምህረት ለማለት ነው) በተሰጠው በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አዲስ ወንጀል ቢፈፅም ለደጋጋሚነት ማሟያ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ መሠረት ግን ምህረት የተደረገለት ሰው አዲስ ወንጀል ቢፈፅም ከዚህ ቀደም የፈፀመው ምህረት ያገኘበት ወንጀል ለደጋጋሚነት ማሟያ ነጥብ አይሆንም ማለት ነው፡፡

ሦስተኛው የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መመዘኛ ወንጀለኛው አዲሱን ወንጀል የፈፀመው አስቦ /intentionally/ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ በዚህ መሰረት በቸልተኝነት የተፈፀመ ወንጀል ደጋጋሚ ወንጀለኛ አያሰኝም፡፡ በዚህ የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መስፈርት ዙሪያ የቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የሚደነግጉት በተመሳሳይ ዓይነት ነው፡፡

አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት አራተኛውና የመጨረሻው መመዘኛ ወንጀለኛው የፈፀመው አዲስ ወንጀል "እጅን አሳልፎ ለመስጠት የሚያበቃ" ዓይነት ወንጀል መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ይህ መመዘኛ በ1949 በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 82(1)(ለ) ድንጋጌ ላይ ሰፍሮ የነበረው መስፈርት ሲሆን ምን ዓይነት ወንጀሎች ናቸው እጅን አስልፎ ለመስጠት የሚያበቁት የሚለው ጉዳይ በሕግ በግልፅ ያልተመለከተበት ሁኔታ ስለነበረ በወንጀለኛ መቅጫ

ሕጉ መሠረት አንድን አጥፊ ደጋጋሚ ወንጀለኛ (recidivist) ነው ለማለትና ይህን መሠረት አድርጎ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ አክብዶ በአጥፊው ላይ ለመወሰን አስቸጋሪ ወይም የማይቻልበት ሁኔታ ነበር፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 መሰረት ግን አንድ አጥፊ ደጋጋሚ ወንጀለኛ (recidivist) ነው የሚባለው አጥፊው አስቦ የፈፀመው አዲስ ወንጀል መነሻ ቅጣቱ ስድስት ወር የሆነ ቀላል እስራት ማስቀጣት የሚችል ወንጀል የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ወንጀለኛው አዲስ የፈፀመው ወንጀል የሚያስቀጣው ከስድስት ወር ቀላል እስራት በታች ከሆነ ለደጋጋሚ ወንጀለኛነት በወንጀል ሕጉ የተቀመጠው መስፈርት ስላማይሟላ በወንጀለኛው የሚጣለው ቅጣት እንዲከብድ የሚደረገው በልዩ ሁኔታ ሳይሆን እንደ መደበኛ የቅጣት ማበክጃ ምክንያት ተወስዶ ነው፡፡

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ ደጋጋሚ ለመባል ወንጀለኛውን ከዚህ ቀደም ያስቀጣውና አዲስ የተፈፀመው ወንጀል የግድ ተመሳሳይ መሆን የማይኖርባቸው መሆኑ ነው፤ ማለትም መስፈርቶቹ እስከተሟሉ ድረስ የወንጀሎቹ ዓይነት ቢለያይም የሚያከስትለው ለውጥ የለም፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቅጣት የተገደበለት ሰው ሌላ ወንጀል ሲፈፅም እንደ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ወይስ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደፈፀመ ሰው ነው የሚቆጠረው?

2. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 መሠረት አንድ ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ለማለት ሌሎች መመዘኛዎች እንደተጠበቁ ሆነው አጥፊው አስቦ የፈፀመው አዲስ ወንጀል መነሻ ቅጣቱ ስድስት ወር የሆነ ቀላል እስራት ማስቀጣት የሚችል ወንጀል የሆነ እንደሆነ ነው። ይህ የስድስት ወር ቀላል እስራት መነሻ ቅጣት አጥፊው አዲስ ለፈፀመው ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል የተደነገገውን ዝቅተኛ ቅጣት ወይስ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል አጥፊው ደጋጋሚ መሆኑን ግምት ውስጥ ሳያስገባ የሚጥለውን ቅጣት የሚመለከት ይመስላችኋል? ሁለቱ አተረጓጎሞች የሚኖራቸውን ውጤት ተወያዩበት።

ንዑስ ክፍል አምስት - ተደራራቢ ወንጀሎችና ቅጣት አወሳሰን

1.5.1. ተደራራቢ ወንጀሎች እና ተደራራቢ የሚመስሉ ተግባሮች

በአጠቃላይ ተደራራቢ ወንጀሎች (Concurrence offences) በአንድ ሰው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ ያለውን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ሁለት ወይም ቁጥራቸው ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎች ተደራራቢ ናቸው ሊባሉ የሚችሉት ሁለተኛው ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት መጀመሪያ በተፈፀመው ወንጀል ላይ ፍርድ አልተሰጠ እንደሆነ ነው። የወንጀሎች መደራረብ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል።

ግዙፍ የሆነ (ቁሳዊ) መደራረብ /Material concurrence/-አንድ ሰው ተመሳሳይ ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት በመፈጸም እንደ አንድ ወንጀል የማይቆጠሩ ወንጀሎችን ሲፈፅም ወይም ተመሳሳይ ያልሆኑ ማለትም የተለያዩ ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት በመፈጸም በተለያዩ የወንጀል ድንጋጌዎች ሥር የሚወድቁ ወንጀሎችን የፈፀመ እንደሆነ ግዙፍ የሆነ (ቁሳዊ) መደራረብ አለ ይባላል። የእንዲህ ዓይነት ተደራራቢ ወንጀሎች ዓይነተኛ መለያ የድርጊቶች መደጋገም ነው። የድርጊት መደጋገም እስካለ ድረስ የተፈፀሙት ወንጀሎች ዓይነታቸው አንድ ቢሆንም ወይም ባይሆንም የተደራረቡ ወንጀሎች ናቸው። ማለትም እንደ አንድ ወንጀል የማይቆጠሩ ነገር ግን በአንድ አንቀጽ ስር የሚወድቁ በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀሙ ተመሳሳይ ድርጊቶችም ቢሆኑ ግዙፍ የሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው።

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ተደብቆ እየገባ የተለያዩ ንብረቶች ቢሰርቅ ወይም ደግሞ ዛሬ ጠዋት አንድ ሰው ቢገድል እና ማታ ላይ ደግሞ አንዲት ሴት አስገድዶ ቢደፍር የወንጀል ድርጊቶቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም ባይሆኑም እንደ አንድ ወንጀል ተቆጥረው በአንድ አንቀጽ ብቻ አንድ የወንጀል ክስ የማይቀርብበት እስከሆነ የተደራረቡ ወንጀሎችን ፈጽሟል። እንዲህ ዓይነት መደራረብ የድርጊትን መደጋገም የሚያመለክት በመሆኑ ግዙፍ የሆነ ወይም ቁሳዊ መደራረብ በመባል ይጠራል።

<u>ሐሳባዊ (ጣምራዊ) መደራረብ</u> /Notional concurrence/ - አንድ ሰው በአንድ ድርጊት ግዙፍነት ያላቸው ወይም የሌላቸው ውጤቶችን በማስከተል ከአንድ በላይ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ሐሳባዊ መደራረብ አለ ይባላል፡፡ የሀሳባዊ መደራረብ መለያ ባህሪ በአንድ ነጠላ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ወንጀሎች መፈፀማቸው ነው፡፡ በድርጊት ደረጃ የተፈፀመው ተግባር አንድ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም የተፈፀመው አንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ግዙፍ የሆኑ ውጤቶችን ካስከተለ ወይም ደግሞ ድርጊቱ ከአንድ በላይ የሆኑ ግዙፍ ውጤቶችን ባያስከትልም ከሕግ አንጻር በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ተግባር ሆኖ ከተገኘ የተደራረቡ ወንጀሎች ተፈጽመዋል ተብሎ ይወሰዳል፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በአንድ ጥይት አስቦ አንድ ሰው ቢገድል እና በዚያው ጥይት ደግሞ ሌላ ሰው ቢያቆስል በድርጊቱ ላደረሰው ሞት በግድያ ወንጀል እና በዚያው ድርጊት ላደረሰው ማቁሰል በመግደል ሙከራ ወንጀሎች ሊጠየቅ የሚችል ሲሆን በዚህም መሰረት የተፈፀመው ድርጊት አንድ ብቻ ቢሆንም ያስከተላቸው ውጤቶች ግን ሁለት የሚታዩ ግዙፍነት ያላቸው ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ባለትዳር የሆነ ሰው አንዲት ሴት አስገድዶ ቢደፍር በአንድ ድርጊት የአመንዝራነት /የሴሰኝነት/ እና የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን ፈፅሟል፡፡ እዚህ ላይ ለማንኛውም ሰው ግልፅ ሆኖ የሚታየው የድርጊቱ ውጤት በሴትዮዋ ላይ በማስገደድ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈፀመባት መሆኑ ነው፡፡ ሌላ የሚታይ ግዙፍ ውጤት የለም፡፡ ሆኖም ከሕግ አንጻር ሲታይ ግለሰቡ በፈፀመው አንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የወንጀል ድንጋጌዎችን በመጣስ የተደራረቡ ወንጀሎችን ፈፅሟል፡፡ በዚህም መሠረት በሁለቱም ምሳሌዎች ላይ ከአንድ ድርጊት የተነሳ ከአንድ በላይ ወንጀሎች በመፈፀማቸው የተደጋገመው ድርጊቱ ሳይሆን ወንጀሎቹ ናቸው፡፡

በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ጣምራ ወንጀሎችን በመፈፀሙ ተደራራቢ ወንጀሎችን እንደፈፀመ የሚቆጠረው በአንድ ድርጊት የተለያዩ የወንጀል ድንጋጌዎችን ጥሶ ሲገኝ የነበረ ሲሆን በአንድ ድርጊት ተመሳሳይ የወንጀል ድንጋጌዎችን ከጣሰ አንድ ወንጀል እንደፈፀመ የሚቆጠርበት ሁኔታ ወይም ቢያንስ የብዙ ባለሙያዎች አረዳድ የተፈፀመው ወንጀል አንድ ነው የሚል ነበር፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ መሠረት ግን አንድ ሰው በአንድ ድርጊት የጣሰው አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ ቢሆንም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ካደረሰ ተደራራቢ ወንጀሎችን እንደፈፀመ እንደሚቆጠር በአንቀጽ 60(ሐ) ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ተደራራቢ ወንጀሎች ተደራራቢ ከሚመስሉ ተግባሮች ጋር ያላቸው አንድነትና ልዩነት ምንድነው የሚለውን በአግባቡ መለየት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61 እና አንቀጽ 63 ላይ ተደራራቢ የሚመስሉ ተግባሮችን አስመልክቶ ድንጋጌዎች ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህ ተግባሮች በዋናነት በአራት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እነርሱም፡-

1. የተቀላቀሉ የወንጀል ተግባሮች - ይህ ሁኔታ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ተግባሮች በአንድ ሰው የተፈፀሙ የሚመስሉበት ሁኔታ መኖሩን ሆኖም ሕጉ እንደ አንድ ወንጀል የወሰደበት ሁኔታ መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ ተግባሮች በአንድ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ በተመሳሳይ የሀሳብ ሁኔታ (በአንድ ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ) የተፈፀሙ በአንድ ድንጋጌ የሚሸፈኑ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ድርጊቶቹ በተናጠል ሲታዩ በልዩ ልዩ አንቀጾች የሚያስቀጡ ቢመስሉም ሁሉንም በተመሳሳይ ጊዜ የተፈፀሙ ድርጊቶች አቀላቅሎ በመሸፈን እንደ አንድ ወንጀል በመቁጠር ቅጣት የሚያስቀምጥ ድንጋጌ በመኖሩ እንደ አንድ ወንጀል እንጅ እንደ ብዙ ወንጀሎች አይቆጠሩም፡፡
2. ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ የወንጀል ተግባሮች - በአንድ መብት ላይ በአንድ ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተፈፀሙ ተግባሮች ምንም እንኳን ተግባሮቹ የተፈፀሙት ከአንድ ጊዜ በላይ ቢሆንም እንደ አንድ ይቆጠራሉ፡፡
3. አንድ የተወሰነ ውጤትን ግብ ለማድረስ የሚፈፀሙ ተያያዥነት ያላቸው ተግባሮች - የመጀመሪያውንና መሠረታዊውን ተግባር ለውጤት ለማብቃት የተፈፀሙ ተግባሮች በዋናው ተግባር የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ማለትም አንድ ድርጊት የተፈፀመው የመጀመሪያውን የወንጀል ድርጊት የመጨረሻ ውጤት ለማስገኘት የሆነ እንደሆነ ከመጀመሪያው መሠረታዊ ወንጀል አስከትሎ የተፈፀመው ተግባር ተደራቢ ወንጀል አይሆንም - በዋናው ወይም በመሠረታዊው ወንጀል ይጠቃለላል ማለት ነው፡፡
   ከዚህ አኳያ ሀሰተኛ ገንዘብን ማዘዋወር ሀሰተኛው ገንዘብ የተሰራበትን ዓላማ ለማሳካት የሚደረግ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የወንጀል ድርጊት ፈጻሚውን በሀሰተኛ ገንዘብ

መስራት (አንቀጽ 356) ወንጀል ተጠያቂ ካደረግነው ገንዘቡን የማዘዋወር ተግባር ፈጽሞ ቢገኝ እንኳን ለሀሰተኛ ገንዘብ መሥራት ወንጀል ተጠያቂ ያደረግነው ተከታዩን የማዘዋወር ተግባር ቅጣት እንደያዘ አድርጎ ሕጉ ይቆጥረዋል።

4. የተዛመዱ ወንጀሎች (Related crimes) - የቀድሞው ሕግ የተቀራረቡ ወንጀሎች በማለት እነዚህን ወንጀሎች ይጠራቸው የነበረ ሲሆን ይህ ሁኔታ የሚኖረው አንድ ወንጀል የተፈፀመው ሌላ ወንጀልን ለመፈፀም በማቀድ ወይም አስቀድሞ የተፈፀመው ወንጀል እንዳይገለፅ ለማድረግ የሆነ እንደሆነ ነው።

   ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 63 ድንጋጌ ለመረዳት እንደሚቻለው አንዳንድ ጊዜ ሕጉ የተዛመዱ ወንጀሎችን እንደ አንድ ነጠላ ሆኖም ከባድ የሆነ ወንጀል አድርጎ የሚቆጥርበት ሁኔታ ይኖራል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ የተዛመዱ ወንጀሎች እንደ ተደራራቢ ወንጀሎች አይቆጠሩም።

1.5.2. <u>ለተደራራቡ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን</u>

ከዚህ በላይ ባለው የጽሑፉ ክፍል ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ወንጀሎች ተደራረቡ የሚባለው አንድ ሰው የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን አከታትሎ በመፈፀም ግዙፍነት ያላቸውን የተለያዩ ወንጀሎችን ሲፈፅም ወይም በአንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ጣምራ ወንጀሎችን ፈፅሞ ሲገኝ ነው። የወንጀሎች መደራረብ በሚኖርበት ጊዜ ቅጣትን ለመወሰን የሚያገለግሉ መሠረታዊ ዘዴዎች ሦስት ናቸው።

የመጀመሪያው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ የማዳመር (cumulation) ዘዴ ሲሆን ይህ ዘዴ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎችን አንድ ሰው ፈጽሞ በሚገኝበት ጊዜ በመጀመሪያ ለእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመነውን ቅጣት በመወሰን በመጨረሻ ሁሉም ቅጣቶች አንድ ላይ እንዲደመሩ የሚደረግበት አሰራር ነው። ይህን ዘዴ የሚከተሉ አንዳንድ አገሮች የቅጣቶች አጠቃላይ ድምር በሕጉ ላይ ለቅጣቱ ዓይነት የተቀመጠውን ጣራ እንዳያልፍ ገደብ የሚያደርጉ ሲሆን ሌሎች አገሮች ደግሞ ቅጣቶቹ ያለገደብ እንዲደመሩ ያደርጋሉ። ስለሆነም በእነዚህ ገደብ በማያስቀምጡ የማዳመር የቅጣት

አወሳሰን ዘዴን በሚከተሉ አገሮች አንድ ሰው ለፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ሁለት መቶ ዓመት ወይም ሦስት መቶ ዓመት እስራት ሊፈረድበት ይችላል፡፡

ሁለተኛው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ የማጠቃለል (absorption) ዘዴ ሲሆን ይህ ዘዴ በ1923 ዓ.ም ወጥቶ በነበረው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ ተካትቶ የነበረ አሰራር ነው፡፡ በዚህ ዘዴ መሠረት ወንጀለኛው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘባቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ ከባድ (ከፍተኛ) ለሆነው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት ለሌሎች ወንጀሎች ይወሰን የነበረውን ቅጣት አጠቃልሎ እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡

ሦስተኛው ለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት የሚወሰንበት ዘዴ የማክበድ (aggravation) ዘዴ የሚባለው ሲሆን ይህ ዘዴ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የማዳመር እና የማጠቃለል ዘዴዎችን በማጣመር የሚሰራበት ዘዴ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ በዚህ የቅጣት አወሳሰን መርሕ መሰረት በወንጀለኛው ከተፈፀሙት ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ ከባድ ለሆነው ወንጀል ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ለቀሪዎቹ ወንጀሎች በሕግ በተወሰነው መጠንና ገደብ መሰረት የመጀመሪያው ቅጣት እንዲከብድ ይደረጋል፡፡

በተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን ዙሪያ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሚለይባቸው የተለያዩ ጉዳዮች ቢኖሩም መሠረታዊ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው ልዩነት ግን የተደራረቡ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ ቀደም ሲል ቅጣት ይወሰንበት የነበረውን መሠረታዊ መርህ የለወጠው መሆኑ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አካሄድ ለከባዱ ወንጀል ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ለሌላው ወንጀል እስከ መጀመሪያው (የከባዱ) ወንጀል ማስቀጫ አንቀጽ የቅጣት ጣራ አጋማሽ ድረስ ቅጣት ይጨመር የነበረበት የማክበድ (aggravation) መርህ ቀርቶ ለየቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገውን የቅጣት ጣራ እስካላለፈ ድረስ ለሁሉም ወንጀሎች የሚወሰኑ ቅጣቶች እንዲደመሩ ሆኗል፡፡ በተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን ዙሪያ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተካተቱትን ነጥቦች ቀጥለን በአጭሩ እንመለከታቸዋለን፡፡

ሀ. <u>ከተደራራቡት ግዙፍ ወንጀሎች ውስጥ ለአንደኛው የሚጣለው ቅጣት የቀሪዎችን ወንጀሎች ቅጣት የሚያጠቃልል በሆነ ጊዜ፣</u>

ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ከተወሠነ ይህ ውሳኔ ለሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሠነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ ይይዛል (አንቀጽ 184(1)(ሀ))። ይህም ማለት ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ በአንዱ ምክንያት የሞት ቅጣት ወይም የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት፣ የ25 ዓመት ፅኑ እስራት ወይም የአምስት ዓመት ቀላል እስራት ከተወሠነ በሌሎች ተመሣሣይ ዓይነት ቅጣት በሚያስፈርዱ ወንጀሎች ምክንያት ከተገለፀው ቅጣት በላይ መወሠን አይቻልም። (በአንቀጽ 184/1//ሀ/ የተደነገገው ሁኔታ ቅጣቱ ቢከብድም ከተደራረቡት ወንጀሎች በአንደኛው ውስጥ በሕጉ ልዩ ክፍል ቅጣቱ ተካትቶ /ተሸፍኖ/ የምናገኝበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው)።

ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ከባድ ለሆነው ለአንደኛው ወንጀል የሞት ቅጣት፤ የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት መወሰኑን ትቶ ዝቅ ያለ ቅጣት ከወሠነ፤ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን አክብዶ መወሠን ይችላል። ለምሳሌ አንድ ጥፋተኛ ከሚፈረድበት ወንጀሎች ውስጥ በአንደኛው ምክንያት የሀያ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት የሚወሰንበት ከሆነ በሌሎች አነስተኛ ወንጀሎች ምክንያት የእስራት ቅጣት ሊወሰንበት አይችልም። ምክንያቱም ለፅኑ እስራት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተቀመጠው ከፍተኛ የቅጣት ጣራ ሀያ አምስት በመሆኑ ከዚያ አልፎ ሰላሳ ዓመት ወይም ደግሞ የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ፍርድ ቤቱ ሊወስን ዓይችልም። የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሊወሰን የሚችለው ወንጀለኛው ከፈፀማቸው ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው። ምንም እንኳን ወንጀለኛው የፈፀመው ከባዱ ወንጀል በሀያ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት ሊያስቀጣ የሚችል ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ከቅጣት ጣራው ዝቅ በማድረግ ለከባዱ ወንጀል ቅጣት የሚጥል ከሆነ ሌሎች ጥፋተኛው የፈፀማቸው ወንጀሎች ግምት ውስጥ ገብተው ቅጣቱ እንዲከብድ ይደረጋል።

በዚህ ሁኔታ ለተደራራቢዎቹ ወንጀሎች የሚወሰነው ቅጣትም ለሁሉም ወንጀሎች ለየራሳቸው ቅጣቶችን በመጣል እንዲደመሩ በማድረግ ይሆናል፡፡

ለ. <u>በእስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ፣</u>

ጥፋተኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ የየትኛውም ወንጀል ቅጣት የቀሪዎችን ወንጀሎች ቅጣት የሚያጠቃልል ካልሆነና ወንጀሎቹ በእስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ከሆኑ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም እንዲደመር ይደረጋል፡፡ ሆኖም ምንጊዜም ቢሆን ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት ማለፍ አይቻልም/አንቀጽ 184/1//ለ/፡፡

አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ከፊሎቹ የሚያስቀጡት በቀላል እስራት ከፊሎቹ ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሚሆኑበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ በምን ዓይነት መንገድ እንደሚሰላ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ ላይ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይኸውም እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ቅጣቶችን ለመደመር እንዲያመች ሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት ይቆጠራል፡፡ ይህ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ላይ በፅኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው /ተቀላቅለው/ ከተገኙ የእስራት ቅጣቶችን ለመደመር እንዴት እንደሚቻል የሚያመለክተው ድንጋጌ በ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ያልነበረ አዲስ የተጨመረ ሲሆን የቀድሞው ሕግ በግልፅ የደነገገው ነገር ባለመኖሩ ምክንያት የነበረውን የተዘበራረቀ አሰራር ወጥ በሆነ አሰራር እንዲተካ የሚያደርግ ነው፡፡

ሐ. <u>ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ በገንዘብ የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ፣</u> /አንቀጽ 184/1//መ/

አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በገንዘብ ቅጣት (በመቀጮ) የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች የሆኑ እንደሆነ ወይም ከሌሎች ቅጣት ጋር ተጣምረው ለተደራራቢ ወንጀሎቹ የገንዘብ ቅጣቶች በጥፋተኛው ላይ የሚጣሉ በሚሆንበት ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው የገንዘብ ቅጣት ተወስኖ ሁሉም ይደመራል፡፡

ሆኖም ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈፀመ ካልሆነ በቀር ምንጊዜም ቢሆን በወንጀለኛው ላይ የሚጣለው የመቀጮ ቅጣት አጠቃላይ ድምር በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተመለከተው ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት ወሠን ማለፍ አይችልም፡፡

የመውረስና የገንዘብ መቀጮ በሚያጋጥምበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ ምን ሊሆን ይገባል የሚለውን በተመለከተ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተካተተው ሀሳብ ተመሳሳይ ነው፡፡ ከተደራራቢዎቹ ወንጀሎች በአንዱ ምክንያት የተቀጪው ንብረት እንዲወረስ ከተወሰነ በሌላው ወንጀል ምክንያት መቀጮ በተጨማሪ ሊወሠን አይችልም /ቁጥር 189(ሠ)፣ አንቀጽ 184(1)(ሠ)/

በዚህም መሠረት ጥፋተኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢዎቹ ወንጀሎች ውስጥ በአንደኛው ወንጀል ምክንያት ከሚፈረድበት ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ የወንጀለኛው ንብረት እንዲወረስ ከተፈረደበት በሌሎች ተደራቢ ወንጀሎች ምክንያት የገንዘብ መቀጮ መፍረድ አይቻልም ማለት ነው፡፡

መ. <u>ጣምራ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ</u>

አንድ ሰው በአንድ ድርጊት የሚጥሰው አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ ቢሆንም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ካደረሰ ተደራራቢ ወንጀሎችን እንደፈፀመ እንደሚቆጠር በአንቀጽ 60(ሐ) ላይ ተደንግጓል፡፡ ቅጣቱ የሚወሰነውም በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር ከዚህ በላይ በተጠቀሠው ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ነው (አንቀጽ 184(2))፡፡

በአንድ ድርጊት የተደራረቡ ጣምራ ወንጀሎች የፈፀመ ቢሆንም የጉዳዩን አካባቢ ሁኔታዎች በመመርመር ፡-

- ጣምራ ወንጀሎቹን የፈፀመው ከዚህ በታች ከተጠቀሰው ሁኔታ ውጭ ከሆነ በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት ወሰን ባለማለፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን አክብዶ ይወስናል (አንቀጽ 187(1))፡፡
- ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕጉን ጥሶ ከሆነ ወይም ግልፅ የሆነ መጥፎ ፀባይ አሳይቶ እንደሆነ ግን በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰንበታል፣

- ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎች ተፈፅመው በተገኙ ጊዜ ግን፡-
    - ❖ ጥፋተኛው ከተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንደኛውን አስቦ ያደረገ እንደሆነ በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰንበታል (አንቀጽ 187/2/ሀ)፣
    - ❖ ጥፋተኛው ጣምራ ወንጀሎቹን የፈፀመው በቸልተኝነት ከሆነ በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ወሰን ባለማለፍ ይወሰንበታል (አንቀጽ 187/2/ለ)፣

ሠ. <u>የተዛመዱ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ</u>

የተዛመዱ ወይም የተቀራረቡ ወንጀሎች ተፈፀሙ የሚባለው አንዱ የተደረገው ሌላው ወንጀል እንዲፈፀም ለማድረግ፤ ወይም ለማመቻቸት ወይም ለሌላው ከለላ እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ ሲሆን ነው (አንቀጽ 63)፡፡ በመርህ ደረጃ የተዛመዱ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ነው /አንቀጽ 185/1//፡፡

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የተዛመዱ ወንጀሎች እንደ አንድ ነጠላ ወንጀል የሚቆጠሩበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም የሚሆነው ወንጀል ፈጻሚው ዋናውን ወንጀል እግብ ለማድረስ ሲል ሌላ ወንጀል የፈፀመ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ሕግ አውጭው አጥፊው ለዋናው ወንጀል ብቻ ተጠያቂ እንዲሆን በሚደነግግበት ጊዜ ወይም ተዛማጅ ወንጀሎችን እንደ አንድ ነጠላ ወንጀል በመውሰድ የሚደነግግ በወንጀል ሕጉ ውስጥ አንድ ድንጋጌ በሚኖርበት ጊዜ ነው፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ለምሳሌ እንደ ከባድ ግድያ ወይም ከባድ ውንብድና የመሳሰሉ /የተዛመዱ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች/ ቅጣት የሚያከብዱ አንድ ወንጀልን የሚያቋቁሙ መሆናቸው በሕጉ ልዩ ክፍል በተደነገገ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው ለእነዚሁ ወንጀሎች የተመለከቱት ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

ንዑስ ክፍል ስድስት - <u>በወንጀል ተካፋይነት</u>

አንድ ወንጀል በአንድ ሰው የወንጀል ሀሳብ ጠንሳሽነት ተጀምሮ በዚሁ ሰው ድርጊቶች ፍጻሜ ሊያገኝ እንደሚችል ሁሉ በአንድ የወንጀል ሥራ ላይ ወንጀሉን በአካል ከሚፈጽመው ሰው በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች ከአጀማመሩ እስከ ፍጻሜው ባለው ሂደት ወይም ከዚያ በኋላ በተለያዩ ደረጃዎች ሊካፈሉ ወይም ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ እነዚህም የወንጀል ተካፋይነት ዓይነቶች የሚከተሉትን በዋናነት ይይዛል፡-

(ሀ) <u>ዋና ወንጀል አድራጊነት</u>

ዋና ወንጀል አድራጊነት በተለያዩ ገጽታዎች ሊከሰት የሚችል ሲሆን እነዚህ ገጽታዎች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እነርሱም ወንጀልን በቀጥታ መፈፀም እና ወንጀልን በእጅ አዙር መፈፀም ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ አንድ ሰው የወንጀል ድርጊቱን በቀጥታ በግሉ አካላዊ እንቅስቃሴ ሊፈፅም የመቻሉን ያህል በቀጥታና በግል ድርጊቱ ባይፈፅምም በተዘዋዋሪ ሲፈፅም ዋና ወንጀል አድራጊ ተድረጎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን በተዘዋዋሪ ወንጀል ሊፈፀም የሚችልባቸው ሁኔታዎችም በእንስሳት ወይም በግዑዝ ነገሮች አማካኝነት ወይም የወንጀል ኃላፊነት በሌላቸው ሰዎች አማካኝነት ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም አንድ ሰው በመላ አሳቡና አድራጎቱ የአንድ ወንጀል ሙሉ ተካፋይ ሲሆን (የሞራል ወንጀለኛ) ዋና ወንጀል አድራ ተብሎ ይቆጠራል፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው ከበስተጀርባ ሆኖ በሌሎች ሰዎች አማካኝነት ለሚፈፀመው ወንጀል እቅድ በማውጣት፣ ወንጀል ፈጻሚዎችን በመመልመል፣ ወንጀል የሚፈፀምበትን ሰው፣ ንብረት፣ ቦታና ጊዜ እንዲሁም ወንጀሉን ለመፈፀም የሚያስፈልገውን መሣሪያ በመምረጥ በአጠቃላይ ወንጀሉ የሚፈፀምበትን ሥልት በመንደፍና በማዘጋጀት የወንጀል ድርጊቱን የእራሱ ያደረገ እንደሆነ ዋና ወንጀል አድረጊ ነው፡፡

በዚህም መሠረት የሞራል ወንጀለኛ ዋና ዋና መመዘኛዎች ተብለው ሊወሰዱ የሚችሉት ጉዳዮች፡-

- ተከሣሹ ከወንጀል ድርጊቱና ከውጤቱ ጋር የተሟላ የሀሳብ ውህደት የነበረው መሆኑ፣ ማለትም በቀጥታ በአካል ወንጀሉን የሚፈፅመውን ሰው ሙሉ በሙሉ

የመደገፍና ድርጊቱንና የድርጊቱን ውጤት እንደ እራስ ድርጊትና ውጤት አድርጎ መቁጠር፣

- አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የወንጀል ድርጊቱ በሌላ ሰው በአካል ካልተፈፀመ ድርጊቱን እንዲፈፅም የታቀደውን ሰው በመተካት ወንጀሉን በቀጥታ ለመፈፀም ዝግጁ መሆን ናቸው።

በ1949 ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዋና ወንጀል አድራጊ እና ግብረአበር በሚል በቁጥር 32 ላይ ተመልክቶ የነበረው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ ላይ ግን ዋና ወንጀል አድራጊነት ተብሎ ተመልክቷል። በወንጀል ሕጉ ሐተታ ዘምክንያት ላይ እንደተጠቀሰው ለዚህ በምክንያትነት የሰፈረው፤ የቀድሞው ሕግ ድንጋጌ ስያሜ አንድ ቀንደኛ ወንጀል አድራ እንዳለና ሌሎቹ ከእርሱ ያነሰ ሚና ያላቸው እንደሆኑ የሚያስመስል እና በአንቀጹ የተዘረዘሩት ወንጀል አድራጊዎች ሁሉ እንደ ዋና ወንጀል አድራጊ እንጂ አንዱን እንደ ዐብይ ወንጀለኛ ሌሎች ግን እንደ አነስተኛ ወንጀለኞች የሚቆጥር ባለመሆኑ እንዲሁም በወንጀሉ አፈጻፀም ላይ የወንጀል አድራጊዎች በግብር (በድርጊት) ላይሳተፉ የሚችሉ ማለትም አንዳንዶቹ በቀጥታ በድርጊት ተካፋይ ቢሆኑም ሌሎቹ ደግሞ አሳብ ወይም መመሪያ በመስጠት ብቻ ሊሳተፉ የሚችሉ ሆኖ እያለ ግብረአበሮች የሚለው ቃል ግን በግብር ወይም በድርጊት ተካፋይ የሆኑትን ብቻ የሚያመለክት በመሆኑ ይን ችግር ለማስቀረት ሲባል ግብረአበርነት የሚለው ከወንጀል ሕጉ እንዲወጣ የተደረገ ስለመሆኑ ተገልፏል።

(ለ) <u>በልዩ ወንጀሎች ተካፋይ ስለመሆን</u>

አንዳንድ ወንጀሎች በባህሪያቸው የተነሳ በመሠረቱ በሁሉም ሰዎች ሊፈፀሙ የማይችሉ ዓይነት ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ለምሳሌ የኩብለላ ወንጀልን ለመፈፀም ወታደር መሆንን፣ በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀልን ለመፈፀም የመንግሥት ሠራተኛ መሆንን፣ የአመንዝራነት (የሴሰኝነት) ወንጀልን ለመፈፀም ባለትዳር መሆንን በዋናነት ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም አንድ ሰው እነዚህን የተለዩ ጠባይ (ባህሪ) ያላቸውን ወንጀሎች ለመፈፀም የሚያስችለው ሁኔታ ባይኖረውም በመላ አሳቡና በአድራጎቱ እንዚህን ወንጀሎች ለመፈፀም የተለዩ ሁኔታ ካላቸው ሰዎች ጋር ካዋሀደ (ከተባባረ) በዋና ወንጀል አድራጊነት ሊጠየቅ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።

(ሐ) **<u>በሕብረት ስለሚፈፀም ወንጀል</u>**

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 ላይ እንደተደነገገው በአንድ ክፍል በተመደቡ ሰዎች እንደ አድማ እና እንደ አምባጓሮ የመሳሰሉት ወንጀሎች በተደረጉ ጊዜ በህብረቱ ውስጥ መገኘቱ የተረጋገጠበት ሰው በወንጀሉ ተካፋይ አለመሆኑን ካላስረዳ በቀር ለወንጀሉ ተጠያቂነት አለበት፡፡

በመሠረቱ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ሰዎች ወንጀል ተፈጽሟል ተብሎ ሲገመት እያንዳንዱ ሰው በወንጀሉ ውስጥ የነበረው ወይም ያደረገው ተሳትፎ በማስረጃ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህ እንደ አጠቃላይ ለማናቸውም የወንጀል ዓይነት ተፈጻሚ የሚሆን መርህ ነው፡፡ ነገር ግን እንደ አድማ እና አምባጓሮ በመሳሰሉት ወንጀሎች እያንዳንዱ ሰው በህብረት በተፈፀመው ወንጀል ውስጥ መሳተፉ እስከተረጋገጠ ድረስ ምን ምን ድርጊቶችን እንደፈፀመ ማረጋገጫ እንዲቀርብ አይጠበቅም፡፡ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ እና ቦታ ተከሣሹ የተገኘ ቢሆንም አስቦ የወንጀሉ ተካፋይ አለመሆኑን ማስረዳት የሚኖርበት እራሱ ተከሣሹ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ግን ለማንኛውም ዓይነት ወንጀል ተፈጻሚነት ያለው አይደለም፡፡

(መ) **<u>አባሪነት</u>**

ለአንድ የወንጀል ድርጊት እርዳታ የሰጠ ሰው አባሪ በመባል ይጠራል፡፡ የአባሪነት እርዳታ ወንጀሉ ከመፈፀሙ በፊት ወይም በመፈፀም ላይ እንዳለ የተሰጠ መሆን ይኖርበታል፡፡ ወንጀሉ ተፈጽሞ ካበቃ በኋላ የሚሰጥ እርዳታ አባሪነት በሚለው የወንጀል ሕጉ አገላለጽ የሚሸፈን አይደለም፡፡

አባሪ በወንጀል ድርጊቱ አፈጻፀም ላይ እና በውጤቱ ሙሉ ተካፋይ ሳይሆን የወንጀሉ አፈጻፀም የተቃና እንዲሆን በማሰብ ድጋፍ የሚሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም አባሪነት ምንጊዜም ቢሆን ታስቦ የሚፈፀም ተግባር ሲሆን በቸልተኝነት የሚሰጥ ድጋፍ አባሪነት ተብሎ ሊወሰድ አይችልም፡፡

አባሪነት የወንጀል ተሣትፎ አንድ ገፅታ ሲሆን ዋናው ወንጀል አድራጊ በተለያየ ጊዜ ከሌሎች ሰዎች የሚያገኘው እገዛ ነው፡፡ የአባሪነት እርዳታ በተለያየ መልክ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ እርዳታዎቹ ቁሣዊ ወይም ሞራላዊ ወይም አካላዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ወንጀሉን የሚፈፅምበት መሣሪያ መስጠት ቁሣዊ እርዳታ ነው፤ ስለወንጀሉ አፈፃፀም የሚመለከት መረጃ መስጠት

አንደኛው የድጋፍ ዓይነት ነው። ስለሆነም የአባሪነት እርዳታ በተለያዩ መልኩ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን እርዳታው ታስቦ እስከተሰጠ ድረስ የእርዳታው ትልቅነት ወይም ትንሽነት የሚያስከትለው ለውጥ የለም።

አባሪነት ምን ጊዜም ቢሆን ታስቦ (በአወቆ አጥፊነት) የሚፈፀም ወንጀል ነው። አንድ አባሪ የሚሰጠው እርዳታ የወንጀሉ ስራ እንዲቃና በማሰብ የተሰጠ መሆን አለበት። ስለሆነም በቸልተኝነት የሚሰጥ እርዳታ በአባሪነት አያስጠይቅም።

(ሠ) <u>አነሳሽነት</u>

አንድ ሰው ሌላ ሰው ወንጀል እንዲፈፅም በገንዘብ፣ በስጦታ፣ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ያግባባ አንደሆነ አነሳሽ ተብሎ ይቆጠራል። በዚህም አንድ የሆነ ወንጀል እንዲፈፀም ፍላጎት ያለው ሰው የወንጀል ድርጊቱን በአካል ባይፈፅምም የፈለገው ወንጀል እንዲፈፀም ለማድረግ ሌላውን ሰው በተለያዩ መንገድ አግባብቶ በመሣሪያነት ሲጠቀምበት በአነሳሽነት ተጠያቂ ይሆናል። ሆኖም አንድ ሰው አነሳሺ ተብሎ በወንጀል የሚጠየቀው ተነሳሺው ቢያንስ ዋናውን ወንጀል የመፈፀም መነሻራ አድርጎ እንደሆነ ነው (አንቀጽ 36(2))።

(ረ) <u>ወንጀለኛን መርዳት</u>

ይህ ማለት አንድ ሰው ወንጀል ከፈፀመ በኋላ በዚሁ ወንጀል እንዳይከሰስ ወይም እንዳይቀጣ እርዳታ መስጠት ማለት ነው። ወንጀለኛን መርዳት እንድ አባሪነትም ሆነ በመሠረቱ እንደ የወንጀል ተካፋይነት የማይቆጠረው ከወንጀሉ በኋላ እርዳታውን በሚሰጠው እና የወንጀል ድርጊቱን በሚፈፅመው ሰው መካከል መጀመሪያ የተፈፀመውን ወንጀል በተመለከተ ምንም ዓይነት የሀሳብ አንድነት ባለመኖሩ ነው።

ከዚህም የተነሳ አባሪ ወይም አነሳሽ በመርህ ደረጃ ዋናው ወንጀል አድራጊ በሚከሰስበት የወንጀል ድንጋጌ የሚከሰስና በዚሁ አንቀጽ ላይ የተደነገገው ቅጣት የሚወሰንበት ሲሆን ወንጀለኛን የሚረዳ ግን አስቀድሞ ለተፈፀመው ወንጀል ያደረገው አስተዋፅኦ ባለመኖሩ እራሱ ለፈፀመው የወንጀል ድርጊት አግባብነት ባለው የወንጀል አንቀጽ ብቻ ተከስሶ በዚያው መሠረት ቅጣት ይጣልበታል።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ከአድማ እና ከአምባጓሮ በተጨማሪ የህብረት ወንጀል በሚለው በአንቀጽ 35 መሠረት ሊታዩ የሚችሉ የወንጀል ጉዳዮች እንዴት ዓይነት የወንጀል ዓይነቶች እንደሆኑ መርምሩ።
2. በአባሪነት እና በሞራል ወንጀለኛ (ዋና ወንጀል አድራጊ) እንዲሁም በአነሳሽነት መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነቶች ምን ምን እንደሆኑ ተወያዩበት።
3. አንድ ሰው ሌላ ሰው ወንጀል እንዲፈፅም ፈልጎ ካግባባው የማነሳሳቱ ድርጊት በዚሁ ደረጃ ላይ እንዳለ አነሳሺው ሊያደርገው ከሚችለው አንጻር ፍጻሜ ያገኘ በመሆኑ ዋናው ወንጀል ባይሞከር እንኳን አነሳሺው የወንጀል ተጠያቂነት እንዳይኖርበት መደረጉ አግባብነት ያለው ይመስላችኋል?
4. ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች አንድ ወንጀል ሲፈፀምና በህብረት የሚፈፀም ወንጀል ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ምንድነው?
5. አዲስ አበባ ውስጥ አንድ የሆነ ቦታ ላይ የተጠመደ ፈንጅ ፈንድቶ የአስር ሰዎችን ሕይወት እና በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት አጠፋ። ለዚህም አንድ የሆነ "ድርጅት" ኃላፊነቱን እንደሚወስድ አሳወቀ። በዚህ ሁኔታ ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ኃላፊነቱን እወስዳለሁ ያለው ድርጅት አባል ሆኖ ነገር ግን ድርጊቱን በአካል ያልፈፀመ ወይም ጭራሽ ስለሁኔታው ምንም የሚያውቀው ነገር ያልነበረ ሰው የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበት እንደሆነ ተወያዩበት።
6. አንዲት የቤት ሠራተኛ የምትሰራበትን ቤት ጓደኛዋ እንዲዘርፈው የቤቱን ቁልፍ ሰጥታው ሆኖም ግን ጓደኛዋ ለዘረፋ ሲሄድ የቤቱ በር ክፍት ሆኖ ቢያገኘው የቤት ሠራተኛዋን አባሪ ማድረግ ይቻላል?

ክፍል ሁለት - <u>በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የሚስተዋሉ አንዳንድ የትርጉምና የአፈጻፀም ችግሮች</u>

ንዑስ ክፍል አንድ- <u>የሰው መግደል ወንጀል</u>

በህይወት መኖር የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቱ ነው፤ ሰብዓዊ መብት ስንል ሰው ሰብዓዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ የሚኖረው መብት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 10(1) ላይ “ከሠው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጨ” ሲል ሰው ሰው ሆኖ በመወለዱ ብቻ ማናቸውም ቅድመ ሁኔታ ሣያስፈልግ የሚኖሩት መብቶች ብሎ እውቅና ከሚሰጣቸው ሰብዓዊ መብቶች ውስጥ አንዱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 15 ላይ የተመለከተው የሕይወት መብት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን ሊያጣ አይችልም፡፡

በሰው ህይወት ላይ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች ውስጥ አንደኛው የሰው መግደል ወንጀል (homicide) ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ በመሆኑም በሌላ ሰዉ የወንጀል ድርጊት ምክንያት አንድ ሰዉ ሰዉ በመሆኑ ብቻ የሚያገኘዉና ህገ መንግስታዊ ዕዉቅና የተሰጠዉን እጅግ በጣም ዉድ የሆነዉን በህይወት የመኖር መብቱን ልያጣ ይችላል ማለት ነዉ፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግም ይሄንን መሠረታዊ የሰው ልጆች መብት ጥበቃ ለማድረግ የወንጀል ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ የወንጀል ሕጉም የሰው መግደል ወንጀልን ሆን ተብሎ (ታስቦ) የሚፈፀም የሰው መግደል ወንጀል፣ በቸልተኝነት የሚፈፀም የሰው መግደል እና ህጻንን መግደል በሚል በሦስት መልኩ ያስቀመጠ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ሀ. አስቦ ሰዉ መግደል

ታስቦ የሚፈፀመውን የሰው መግደል ወንጀል ለብቻ አውጥተን ስንመለከተው በሦስት ተከፍሎ እናገኘዋለን፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539፣ 540 እና 541 ላይ ሆን ተብሎ የሚፈፀም የሰው መግደል ተግባር ከባድ የሰው ግድያ፣ ተራ የሆነ የሰው ግድያ እና ቀላል የሆነ የሰው ግድያ ተብለው በንዕዕር ዓይነት ተመልክተዋል፡፡ እነዚህን ሦስቱን የሰዉ መግደል ወንጀሎች አንድ የሚያደርጋቸዉ ነገር ቢኖር ሁላቸዉም ታስቦ የሚፈጸሙ የሰዉ መግደል ወንጀሎች መሆናቸዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም በሦስቱ መካከል ያለዉን ልዩነት ለማወቅ ግምት ዉስጥ መግባት ያለበት አስቦ ሰዉን ለመግደል የሃሳብ ክፍል መኖሩና አለመኖሩ ሳይሆን ወንጀሉ የተፈጸመበት ሁኔታ፤ የወንጀሉ አድራጊ ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀመበት መሣሪያ ወይም ዘዴ፤ ወንጀሉን ለመፈጸም ያነሳሱት ምክንያቶች መኖራቸዉና አለመኖራቸዉን መሰረት በማድረግ መሆኑን ከህጉ አጠቃላይ ምልከታ መረዳት ይቻላል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ በሦስቱም መካከል ሰፋ ያሉ ልዩነቶች መኖራቸውም ሌላዉ በትኩረት መታየት ያለበት ነጥብ ነዉ፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539 ሥር በከባድ የሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ የሆነ ሰው በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት የሚቀጣ ሲሆን፣ በ540 ሥር በተራ የመግደል ወንጀል ጥፋተኛ የሆነ ሰው ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚቀጣ ሆኖ በአንቀጽ 541 ሥር በቀላል የሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ የሚሆን ሰዉ ደግሞ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት የሚቀጣ መሆኑን ከህጉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆኔም በእያንዳንዱ አንቀጽ ሥር ወንጀሉን ለማቋቋም የተቀመጡትን ምክንያቶች በአግባቡ ካለመረዳት የተነሳ በአንደኛው ስር ጥፋተኛ መሆን የሚገባውን ሰው በሌላኛው ሥር ጥፋተኛ ማድረግ ግለሰቡ መቀጣት በማይገባው ቅጣት (የበዛ ወይም ያነሰ ቅጣት) የመቀጣትን ውጤት ስለሚያስከትል በአጠቃላይ የወንጀል ህጉን ዓላማ ከግብ ከማድረስ አንፃር የራሱ ተፅዕኖ ያለው መሆኑ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም በእያንዳንዱ አንቀጽ መካከል ያለውን ወሰን በአግባቡ ተገንዝቦ ሥራ ላይ ማዋል የግድ ይላል፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539 መሠረት ከባድ የሰው መግደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ሦስት ምክንያቶች በአማራጭ ተቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው በአንቀጽ 539/1/ /ሀ/ ስር የተቀመጠው ሲሆን በዚህ አንቀጽ መሠረት አንድ ሰው ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ሰውን በመግደል አስቀድሞ የነበረ ሃሳብ መኖሩ፣ ለመግደል የተጠቀመበት መሣሪያ ወይም ዘዴ እንዲሁም ያገዳደሉ ሁኔታ ወይም ቅጣትን ለማክበድ ምክንያት የሚሆኑትና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 84 ሥር የተመለከቱት ጠቅላላ ምክንያቶች ወይም ቅጣትን ለማክበድ በዚህ አንቀጽ (84) ሥር ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ዉጪ ፍርድ ቤት በእራሱ እይታ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 86 መሠረት ግምት ዉስጥ ልያስገባቸዉ የሚችላቸዉ ሌሎች ምክንያቶች መኖራቸዉ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ከባድ ልሆን የሚችለዉ የእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ወይም ከእነዚህ የአንዱ ምክንያት መኖር (በዚህ ንዑስ አንቀጽ ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች የሚታዩት ተደምረዉ ነዉ ወይስ በአማራጭ ነዉ የሚለዉ በቡድን ዉይይት የሚታይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነዉ) የሰዉየዉን (የገዳዩን) ጨካኝነት ወይም ነዉረኛነት ያሳያል ተብሎ የሚገመት መሆኑንም ከህጉ መረዳት ይቻላል፡፡

ከባድ የሰዉ መግደል ወንጀል ለማቋቋም እንደ ምክንያት የተቀመጡት በወንጀል ህጉ 539 (1)/ለ/ እና /ሐ/ ሥር የተመለከቱት ናቸዉ፡፡ በዚህ ሥር የተቀመጡት ምክንያቶች መኖራቸው

ከተረጋገጠ ምናልባትም ሰውየው ሰው ለመግደል አስቀድሞ የነበረው ሃሳብ መኖር አለመኖሩ ወይም ገዳዩ በተለይ ጨካኝ ወይም ነውረኛ መሆኑን የሚያሳይ ሁኔታ ወይም ድርጊት ባይኖርም፤ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል የሚቋቋም መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም አገዳደሉ ተራ ቢሆንም ገዳዩ ሰው ለመግደል ወይም ሌላ የውንብድና ወንጀልን ለመፈፀም በተደራጀ የወንበዴ ቡድን አባል ከሆነ (539(1፣ለ) ወይም ድርጊቱን የፈፀመው ሌላ ወንጀልን ለመፈፀም ወይም የተፈፀመው ወንጀል እንዳይገለፅበት ሲል አስቦ መግደሉ ከተረጋገጠ ((539(1፣ሐ) እነዚህ ሁኔታዎች መኖራቸው ብቻ የመግደል ወንጀሉን ከባድ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡ ስለሆኔም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539 (1፤ሀ) ሥር ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ዉጭ አንድ ሰዉ ሌላዉን ሰዉ አስቦ በመግደሉ በከባድ የሰዉ መግደል ወንጀል የሚጠየቀዉ እነዚህ ምክንያቶች (በ539(1-ለ፣ሐ ስር የተዘረዘሩት ምክንያቶች ማለት ነዉ) ሲኖሩ ብቻ ነዉ ማለት ነዉ፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539 ከተመለከተው በተቃራኒው ማለት ይቻላል፣ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 541 ሥር የተመለከተው ደግሞ ቀላል የሰው መግደል ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቀላል የሰው መግደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ሁለት ምክንያቶች በአማራጭ ተቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ገዳዩ ወንጀሉን የፈፀመው አስገዳጅ ሁኔታን ለማስቀረት ወይም ህጋዊ መከላከልን ተግባራዊ ለማድረግ ሲል ሆኖ የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን ወይም የህጋዊ መከላከሉን መጠን የተላለፈ እንደሆኔ ሲሆን (አንቀጽ 541 (1) ይመለከተዋል)፤ ሁለተኛው ምክንያት አድራጊዉ ድርጊቱን የፈፀመው ቅጣትን የሚያቀሉ ወይም በከፊል ይቅርታን የሚያሰጡ ምክንያቶች ባሉበት ሁኔታ ዉስጥ ሆኖ እንደሆነ ነዉ (አንቀጽ 541 (1) ይመለከተዋል)፡፡

ከመጀመሪያዉ ምክንያት ለመጀመር፤ እንደሚታወቀው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 75 መሠረት ማንም ሰው የራስን ወይም የሌላ ሰውን መብት በቅርብ ከሚደርስ ከባድ ከሆነ አደጋ ለማዳን ሲል ተመጣጣኝ እርምጃ ከወሰደ በፈፀመው ድርጊት የማይቀጣ መሆኑ በመሪህ ደረጃ የተቀመጠ ሲሆን ድርጊቱ የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን የሚያልፍ ከሆኔ ግን አድራጊዉ ከተጠያቂነት (ከቅጣት) ነፃ እንደማይሆን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 76 ሥር ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው በቅርብ ከሚደርሰው ህገ ወጥ ጥቃት ለማዳን በወሰደው እርምጃ ሊቀጣ የማይችል በህጉ አንቀጽ 78 ሥር የተመለከተ ሲሆን ይህ ሆኖም ግን የተወሰደው እርምጃ የህጋዊ መከላከልን መጠን መተላለፉ ከተረጋገጠ አድራጊዉ ከቅጣት የማይድን መሆኑ

በዚሁ ህግ አንቀጽ 79 ሥር ተመልክቷል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 541 (1) ሥር ቀላል የመግደል ወንጀልን ለማቋቋም እንግዲህ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት፤ አድራጊው ድርጊቱን ሆን ብሎ መፈጸሙ፤የፈጸመበትም ምክንያት በቅርብ ከሚደርስ ከባድ አደጋ ወይም በቅርብ ከሚደርስበት ህገ ወጥ ተግባር ራሱን ወይም ሌላዉን ሰዉ ለማዳን ወይም ለመከላከል ሲል ከወሰን ወይም ከመጠን ያለፈ ተግባር መፈጸሙ ነዉ፡፡

ወደ ሁለተኛዉ ምክንያት ስንመለስ፤ በወንጀል ህግ አንቀጽ 541 (2) መሠረት ቀላል የሰዉ መግደል ወንጀል የሚቋቋመዉ ወንጀል አድራጊዉ ወንጀሉን የፈጸመዉ ከፍ ባለ ደም በሚያፈላ ምክንያት ወይም ባልጠበቀዉ ሕሊናን በሚያዉክ ድንገተኛ ምክንያት ወይም በከፍተኛ ስሜት ወይም በብርቱ ዝንባሌ ተነሳስቶ መሆኑና በአእምሮ ግምት ድርጊቱን ለመፈጸም የሚያደርሱና በከፊል ይቅርታን የሚያሰጡ ምክንያቶች መኖራቸዉ ሲረጋገጥ መሆኑን ከህጉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ምክንያት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 82 ቅጣት ማቅለያ እንደምክንያት ከተቀመጡት በተለይ በአንቀጽ 82 (1፤መ) ሥር ከተመለከተዉ ምክንያት ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል መሆኑ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በአንቀጽ 541 (2) ሥር ለተመለከተዉ ለደም ፍላቱ ወይም ለብርቱ ዝንባሌዉ ምክንያት መሆን ያለበት ተበዳዩ ነዉ ወይስ ሌላም ሊሆን ይችላል የሚለዉ ጥያቄ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፤ በህጉ አንቀጽ አንቀጽ 82 (1፤መ) መሠረት አንድ ሰው ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ድርጊት የፈጸመዉ የተበደለዉ ሰዉ ጠባይ በብርቱ ፈተና ጥሎት፤ በከባድ ፀብ ቀስቃሽነት ወይም በአፀያፊ ስድብ ምክንያት ወይም ደም ከሚያፈላ ንዴት፤ ስቃይ ወይም ብስጭት ላይ ጥሎት ወዘተ መሆኑ ከተረጋገጠ ይሄዉ ለተከሳሹ የቅጣት ማቅለያ ልሆንለት የሚችል መሆኑን ህጉ ስለሚደነግግ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ (በ541) ሥር ከተገለጹት ሁለት ምክንያቶች አንዱ መሟላቱ ከተረጋገጠ ቀላል የሰው መግደል ወንጀል የሚቋቋም መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ሌላው መታየት ያለበት ነጥብ ተራ የሰው መግደል ወንጀል ተብሎ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 540 ስር ስለተደነገገው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር “ተራ” የሚለው ቃል የግድያውን ቀላልነት የሚያሳይ ሳይሆን በከባድ ግድያና በቀላል ግድያ መካከል የሚገኝ የግድያ ዓይነት መሆኑን ለማሳየት የተቀመጠ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ‘ተራ’ የተባለበት ምክንያት የሰው መግደል ድርጊቱ የተፈፀመው ከባድ የሰው መግደል ወይም ቀላል የሰው መግደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ

ሁኔታዎች ባልኖሩበት ሁኔታ የሚፈፀመው የሰው መግደል ወንጀል መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡ በመሆኑም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539 ወይም 541 ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ የሚፈጸም አስቦ የሰው መግደል ወንጀል በወንጀል ህጉ አንቀጽ 540 መሰረት ተራ የሰዉ መግደል ወንጀል መሆኑ ነዉ፡፡

ለ. በቸልተኝነት ሰዉ መግደል

በቸልተኝነት ሰዉ የመግደል ወንጀል በኢፌድሪ የወንጀል ህግ ከተካተቱት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በአተረጓጎም ረገድ ከፍተኛ ክርክርና የአቋም ልዩነት ከሚያስከትሉት ድንጋጌዎችም አንዱ አንዱ የቸልተኝነት ግድያን አስመልክቶ የተደነገገው ድንጋጌ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 አኳያ በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሦስት ከፍሎ ያያቸዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ማንኛውም ሰው የሚፈፅመው የቸልተኝነት ግድያ፣
2. በተለዩ ሕይወት፣ ጤንነት ወይም ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም የሌላ ግዴታ ያለበት ሰው ግዴታውን በመጣስ የሚፈጽመው የቸልተኝነት ግድያ፣
3. ጥፋተኛው ሁለት ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልጽ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያን ተላልፎ እንደሆነ ወይም የሚያስክሩ ወይም የሚያፈዙ ንረ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰድ እራሱን ከኃላፊነት በሚያስወጣ ሁኔታ ካስገባ በኋላ የተፈፀመ ግድያ ናቸዉ

ከዚህ የሚንረዳዉ በቸልተኝነት ሰው የመግደል ወንጀልን ህጉ በጠቅላላዉ በሁለት ከፍሎ ያስቀመጠ መሆኑን ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ በአንቀጽ 543/1/ ላይ የተመለከተው ሆኖ ማንኛውም ሰው በቸልተኝነት የሚያደርሰውን የሰው መግደል ወንጀልን የሚመለከት ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ የሰውን አካል ወይም ጤና የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት ሰዉ የሚፈጽመዉ በቸልተኝነት የሰዉ መግደል ወንጀልን የሚመለከት ነዉ፡፡ ሁለተኛዉን በራሱ ህጉ በሁለት ከፍሎ ያስቀመጠ ሲሆን፤ የመጀመሪያዉ በአንቀጽ 543/2/ ተጠያቂ የሚሆነዉ የወንጀሉ አድራጊ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት ሰዉ ሆኖ በድርጊቱ የሞተዉ ሰዉ ቁጥር አንድ ብቻ ሆኖ ድርጊቱንም የፈፀመዉ በህጉ አንቀጽ 543/3/ ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉጪ በሆነ ሁኔታ ሲሆን ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ወንጀሉን የፈፀመው የሰውን አካል ወይም ጤና የመጠበቅ የሙያ ግዴታ ያለበት ሰው ሆኖ የድርጊቱ ዉጤት ወይም ድርጊቱ የተፈጸመበት ሁኔታ

በአንቀጽ 543/3/ ስር ከተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ መኖሩ ከተረጋገጠ ብቻ ልመጣ የሚችል ኃላፊነት ነዉ፡፡ በ543 (2) ስር ከተቀመጠዉ ከፍ ባለ ቅጣት ቅጣት ሊከብድበት የሚችል በአንቀጽ ስር የተመለከተዉ ነዉ ፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ሰው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት ሆኖ የሙያ ግዴታውን በሚያከናውንበት ወቅት በፈፀመው ቸልተኝነት ሰው የገደለ ሆኖ የሞተው ሰው ቁጥር ሁለት እና ከዚያ በላይ ከሆነ፤ ወይም የሞተው ሰው ቁጥር አንድ ቢሆንም እንኳን ተከሳሹ ወንጀሉን የፈፀመው ግልጽ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያን ተላልፎ እንደሆነ ወይም የሚያስክሩ ወይም የሚያፈዙ ንጥረ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰድ እራሱን ከኃላፊነት ነፃ በሚያወጣ ሁኔታ ውስጥ ካስገባ በኋላ መሆኑ ከተረጋገጠ ተጠያቂ የሚሆነው በአንቀጽ 543/3/ ሥር መሆኑ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም በህጉ አንቀጽ 543 (2) ስር በተመለከተዉ መሠረት ልዩ የሙያ ግዴታ ያለበት ሰዉ በቸልተኝነት ሰዉ በመግደል ወንጀል ተከሦ በ543 (3) መሠረት ጥፋተኛ ለመባል መረጋገጥ ያለበት የሙያ ግዴታ ያለበት መሆኑና በድርጊቱ ሰዉ መሞቱ ብቻ ሳይሆን በአንቀጹ ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላትም ጭምር ነዉ፡፡

ከዚህ ጋ በተያያዘ ትኩረት ተሰጥቶት መታየት የሚገባዉ ነጥብ በሦስቱም ላይ የሚጣለዉ ቅጣት በጣም የተለያ መሆኑ ነዉ፡፡ በመጀመሪያው (543 (1) ጥፋተኛ የተባለ ሰው ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከሁለት ሺህ እስከ አራት ሺህ በሚደርስ መቀጮ የሚቀጣ ሲሆን፤ በሁለተኛው (543(2) ጥፋተኛ የተባለ ሰው ደግሞ የሚቀጣው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ብር ሊደርስ የሚችል መቀጮ ነው፡፡ በሦስተኛው (543(3) ጥፋተኛ የተባለ ሰዉ ደግሞ የሚቀጣው ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ እስከ አስራ አምስት ሺህ ብር ሊደርስ የሚችል መቀጮ ነው፡፡በመሆኑም ሦስቱ ሁኔታዎች የሚያስከትሉት ቅጣት የተለያዩ ነው፡፡

ስለዚህ አንድን ተከሣሽ በአንደኛው ወይም በሌላኛው ምድብ መሠረት ጥፋተኛ ማድረጉ የቅጣቱን መጠን የሚለያየው እንደመሆኑ ድንጋጌውን በሚገባ በመመርመርና በስሩም የተጠቀሱትን የግድያ ወንጀሎች ድንበር አበጅቶ በተገቢው መንገድ ቅጣቱን መወሰን ያስፈልጋል፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 542 ላይ በተገለፀው ራስን ማጥፋት ወይም (Suicide) ድንጋጌ ተጠያቂ የሚሆነው ድርጊቱን ፈፃሚው ሣይሆን ድርጊቱ እንዲፈፀም ያነሣሣ ነው፡፡ ድርጊት ፈፃሚው የሚያጠፋው የራሱን ህይወት በመሆኑ የማይጠየቅበት ምክንያት ግልፅ ነው፡፡ በወንጀል ህጉ ላይ ራስን ማጥፋት ወንጀል ነው ተብሎ አልተደነገገም፡፡ በወንጀል ሕግ መሠረት ተለይቶ ወንጀል ነው የልተባለ ነገር ደግሞ እንደማያስጠይቅ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም አንፃር ዋናው ድርጊት ወንጀል ነው ባልተባለበት ሁኔታ ማነሣሣት ወንጀል ይሆናል ከተባለ ከህጉ መሠረታዊ መርህ ጋር ይጣጣማል?

2. አጥፊው በተለዬ ሕይወትን፣ ጤንነትን ወይም ደህንነትን የመጠበቅ የሙያ ወይም የሌላ ግዴታ ያለበት በቸልተኝነት ለፈፀመው የግድያ ወንጀል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 (2) መሰረት ይጠየቃል፡፡ ምን ዓይነት ሙያ ወይም ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ናቸው በዚህ ድንጋጌ የሚሸፈኑት? አንድ መምህር በቸልተኝነት ተማሪ ቢገድል በዚህ ድንጋጌ ይሸፈናል?

3. አጥፊው በተለዬ ሕይወትን፣ ጤንነትን ወይም ደህንነትን የመጠበቅ የሙያ ወይም የሌላ ግዴታ ያለበት በቸልተኝነት ለፈፀመው የግድያ ወንጀል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 (2) መሰረት ተጠያቂ የሚሆነው ወንጀሉን የፈፀመው በሙያ ተግባሩ ላይ እያለ ወይስ ከዚያ ውጭ ቢሆንም (ለምሳሌ አንድ የሕክምና ባለሙያ የሕምና ሥራውን በሚሰራበት ወቅት ወይስ በማናቸውም ጊዜ በቸልተኝነት አንድ ሰው ቢገድል በአንቀጽ 543(2) መሠረት ሊጠየቅ ይችላል)?

4. ማናቸውም የመኪና አሽከርካሪ በተለዬ ሕይወትን፣ ጤንነትን ወይም ደህንነትን የመጠበቅ የሙያ ግዴታ አለበት ተብሎ ሊወሰድና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 (2) ተጠያቂ ሊሆን ይችላል ወይስ ሹፌርነት በሙያነት ይዘው የሚሰሩበትን ነው ድንጋጌው የሚሸፍነው?

5. አንድ ሹፌር በጫናቸው ሰዎች ላይ ወይስ በሌሎች ሰዎች ላይ በቸልተኝነት ሞትን ሊያስከትል ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ድናጋጌ መሠረት ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው? ከዚህ አኳያ የሚከተለውን የፍርድ ቤት ውሳኔ ሀተታ አግባብነት መርምሩ፡፡

“ … ይህ አንቀጽ ኃላፊነቱን በሐኪሞችና በነርሶች ላይ ብቻ አይወስነውም። ሙያተኛ የሚለው ቃል … የሰውነታቸው ደህንነት ጥበቃ በእነርሱ ስር የሚገኙትን ሰዎች ህይወትና ጤና በተለይ እንዲጠብቁ የሥራ ተግባራቸው የሚያስገድዳቸውን ሰዎች ይመለከታል። ሙያተኛ የሚለው ቃል የአውሮፕላን ነጂዎችን፣ የአውቶቡስና ሌሎች የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች ሾፌሮችን ይጨምራል። ሆኖም የእነዚህ ሰዎች ግዴታ በአጠቃላይ ሰዎችን ሁሉ የሚመለከት ሳይሆን በተለይ እነሱ ኃላፊነቱን ለወሰዱባቸው ሰዎች ማለትም በአውሮፕላን ውስጥ ላሉ ተሳፋሪዎችና የአውቶቡስ ተሳፋሪዎች ሲሆን እነዚህ ሙያተኞች ለእግረኞች ወይም በማመላለሻው ውስጥ ለሌሉ ሰዎች ከሚኖርባቸው ጠቅላላ ግዴታ በቀር ልዩ ግዴታ የለባቸውም።” በማለት ከመኪና ውጭ ላለ ሰው ሹፌሩ የሚጠየቀው እንደማንኛውም በቸልተኝነት ሰው የገደለ ግለሰብ ነው የሚል አቋም በመያዝ ውሳኔ ሰጥቷል።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የሚከተሉት ሁለት ዉሳኔዎች የሰዉ መግደል ወንጀልነ በተመለከቱ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰኑ ናቸዉ። እነዚህን ዉሳኔዎች በማንበብ በሶስቱም አስቦ የሰዉ መግደል ወንጀሎች (ከባድ፤ ቀላል እና ተራ ግድያ) መካከል ያሉትን ልዩነቶች ለይቶ ከመወሰን አንፃር በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት ተወያዩበት።

<u>ማሳሰቢያ</u>

በውሳኔዎቹ ላይ አንቀጽ 522፣524፣81 እና 83 ተብለው የተጠቀሱት የቀድሞዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፆች ሲሆኑ አሁን በሥራ ላይ ባለው የወንጀለ ህግ በቅደም ተከተል አንቀጽ 539፣541፣84 እና 86 መሆናቸው ነው።

<u>ጉዳይ 1 - የሰበር መዝገብ ቁጥር 22069</u>

……ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ተጠሪ ሟችን /ሚስቱ የነበረችውን ገነት ገበዬን/ ጨካኝና ነውረኛ በሆነ አኳኋን በመግደሉ በወ/መ/ህግ አንቀጽ 522/1/ሀ/ አመልካች መሰሪያ ቤት ክስ አቅርቦ የሰር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከተጠሪው የወንጀል አፈጻጸም አኳያ በተጠቀሰው የወንጀል ሕግ አንቀጽ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቶ በሃያ /20/ ዓመት ጽኑ

እሥራት እንዲቀጣ ፈርዶበታል። በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የወንጀሉን አፈጻጸም መነሻ ምክንያትና ሁኔታ በመዘርዘር ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል በወ/መ/ህ አንቀጽ 523 መሠረት ጥፋተኛ በማለት በዚሁ መሠረት በአሥራ ሦስት /13/ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል። ይህ ፍርድ በመሠረቱ የሕግ ስሕተት አለው ሲል አመልካች ያቀረበው አቤቱታ የተጠሪ የወንጀል አፈጻጸም በወ/መ/ህ አንቀጽ 522/1/ሀ/ ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ሳለ ወደ 523 ለመለወጥ የሕግ መሠረት የለውም የሚል ነው።

ከዚሁ አኳያ የሰበር ችሎቱ መዝገቡን መርምሯል። በስፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሐተታ እንደተመለከተው ሐምሌ 16 ቀን 1994 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ ተጠሪና ሟች መኖሪያ ቤት ውስጥ ሆነው ተጠሪ የመኖሪያ ቤታቸውን በር ከዘጋ በኋላ ሟችን በበር መቀርቀሪያ ግንባሪን መትቷት በወደቀችበት ቦታ ሁለት እጆቿን በማሰር ብልቷ ውስጥ እጁን በማስገባት ከባድ ጉዳት እንዳደረሰባት እና በዚሁ ምክንያት ሐምሌ 23 ቀን 1994 ዓ.ም ሕይወቷ እንዳለፈ በሰር ፍ/ቤት ተረጋግጧል። ይህንን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ የድርጊቱ አፈጻጸም የተጠሪን ጨካኝነት እና ነውረኛነት ያረጋግጣል በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ለመለወጥ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ያስቀመጠው ምክንያት "የተጠሪው ድርጊት ዘግናኝ ቢሆንም ሟችን ለመግደል አስቀድሞ ያሰበና የተዘጋጀ ለመሆኑ አልተረጋገጠም" የሚል ነው። ይህንን የጠቅላይ ፍ/ቤቱን አቋም ከወ/መ/ህግ አንቀጽ 522 ይዘት አንፃር መመርመር አግባብነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል።

በመሠረቱ በወንጀል ሕግ የሀሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈጻጸም መሆኑ አከራካሪ አይደለም። በዚሁ ጉዳይ ላይ የተጠሪ የወንጀል አፈጻጸም በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 522/1/ሀ/ ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ እንዲወድቅ ያደረገው ድንጋጌው "አስቀድሞ ማሰብን" እንደዋነኛ ምክንያት ወይም ብቸኛ ምክንያት የተመለከተ አለመሆኑ ነው። በዚህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ከባድ የግፍ አገዳደል ወንጀል መፈጸሙን ለማረጋገጥ ወይም ለማቋቋም የሚታዩት ሁኔታዎች በአማራጭ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች መሆናቸው እንጂ አንዱ ከሌላው ጋር በተደራራቢነት እና በጋራ የሚታዩ ጉዳዮች መሆናቸው አልተመለከተም። በመሆኑም የተጠሪን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው በመጀመሪያ በቀን የመኖሪያ ቤቱን በር በመዝጋት በሟች ጩኸት የአካባቢው ሰው ደርሶ እንዳያስጥለው ማድረጉ ሟች ራሷን እንዳትከላከል በገመድ እጇን ወደ ኋላ ማሰሩ እንዲሁም ሟችን በበር መቀርቀሪያ

ግንባሯን መትቶ ከጣለት በኋላ ብልቷ ውስጥ እጁን በመክተት እጅግ ከፍተኛ ለሆነ ጉዳት በዳረጉ ሲታዩ ተጠሪው የድርጉቱ ውጤት ይህንን እንዲያስከትል የፈለገ መሆኑና አስቀድሞ ማሰቡን የሚያመለክቱ ከመሆናቸውም በላይ በሚሰቱ በመዋለጃ አካል ላይ የዚህ ዓይነት ድርጊት መፈጸሙ ነውረኛ እና ጨካኝ መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ከላይ በማመልከት እንደተሞከረው የተጠሪ የሀሳብ ሁኔታ ከድርጊቱ በመነሳት የሚገመት መሆኑ እንዳለ ሆኖ የድርጊቱ አፈጻጸም በራሱ እጅግ ጨካኝና ውረኛ መሆኑን ያረጋግጣል። ከዚህም ባሻገር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ውሳኔውን ለማሻሻል መሠረት ያደረገው ሁኔታ የተጠሪን "የስንፈተ ወሲብ" ችግር ሕብረተሰቡ ከሚያደርስበት ተፅኖ አንፃር በማየት እንደሆነ በውሳኔው ተመልክቷል። ይህም ሁኔት የተጠሪው የተፈጥሮ ችግር ቢኖር እንኳ ጋብቻቸውን ከማፍረስ አልፎ የሚችን ሕይወት ለማጥፋቱ እንደተገቢ ምክንያት ተደርጐ መወሰድ አግባብነት የለውም። ባጠቃላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም በማስረጃ በማጣራት አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 522 /1/ ሀ ሥር የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በቂ የሕግ ምክንያት ሳይኖረው መቀየሩ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ሆኖ ተገኝቷል።

ጉዳይ 2 የሰ/መ/ቁ 22452

.....በአመልካችና በተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ መካከል የነበረውን በግፍ ሰው የመግደል እና በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ የወንጀል ክርክር የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በሰማ በኋላ በወ/መ/ቁ. 258/94 ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪን በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል በዐቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት ድንጋጌ በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ደግሞ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰበትን ድንጋጌ ዝቅ በማድረግ ተራ በሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል በሚያስጠይቅ ድንጋጌ ጥፋተኛ ከአደረገው በኋላ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነውን ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያደረገባቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን ዝቅ በማድረግ ቅጣቱን በተመለከተም ተጠሪን የሚያርመው ተመጣጣኝ ቅጣት የ8 /ስምንት/ ዓመት ጽኑ እስራት ነው በማለት በመወሰኑ ይኸው ውሣኔ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለባቸው የሕግ አንቀጾችም ሆኑ የቅጣት አወሣሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሣያል በማለት የአሁኑ አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

አቅርቦ ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ውሣኔውን በማጽናቱ ነው።

አመልካች በቁጥር 05/I/A-11/1120 በቀን 20/04/98 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የተጠሪ አድራጉት በስር ፍ/ቤት ጥፋተኛ በተባሉባቸው ድንጋጌዎች የሚሸፈን ሆኖ እያለ ውሣኔ የተሰጠበት የሕግ አንቀጽ መለወጡ አግባብነት ስለሌለው ተሰተካክሎ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል። በዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጐም ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መልሱን ሰጥቷል።

ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከበታች ፍ/ቤቶች የውሣኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያደረገባቸውን የህግ አንቀጾች የለወጠው በአግባቡ /በሕጉ ረገድ/ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል። ተጠሪ በወ/መ/ህ/ቁ.522/1/ሀ/ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሟች ባለቤቱን ወ/ሮ ዝናሽ ለማ የተባለችውን ሕፃን ልጅ ወልዳ አራስ ቤት በተኛችበት ስፍራ ማካሮቭ ሽጉጥ ተኩሶባት አናቷ ላይ ሁለት ቦት መቷት ለህልፈተ ህይወት ዳርጓታል፤ በወ/መ/ሕ/ቁ.27/1/ና 522/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ደግሞ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሰሚች ዝናሽ ለማ ጋር እንዳይጣላ ሰዎች ጣልቃ ገብተው ለማለያየት ሊገላግሉ ሲሉ እናንተ ነገ ምስክሮች ትሆኑብኛላችሁ አይደል በማለት ማካሮቭ ሽጉጡን በመተኮስ የግል ተበዳይ የሆኑትን 1ኛ/ወ/ሪት እስከዳር ጋሻውን በሁለት ጥይት ከፊቷ ላይ መቷት አንዱ ጥይት ከአንገቷ በስተኋላ ሲወጣ አንዱ ጥይት ደግሞ ከአንገቷ ከአንገቷ ስር በሰውነቷ ውስጥ የቀረ በመሆኑ 2ኛ/ወ/ሪት መና መሐመድ በምትባለው ላይም አንድ ጥይት ተኩሶባት በመሸሸዋ ህይወቷ መትረፍ የቻለ መሆኑን በመግለጽ በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ክስ በአመልካች በኩል ቀርቦበት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሀሩ ከፍ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪን የመከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃዎች አያስተባብልም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጐ ተጠሪን በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ሀ/፣ 522/1/ሀ/ና 523 ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጓል።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ግን በተጠሪ ላይ የተሰጠውን የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተቀበለ በኋላ አድራጐቶቹ የሚሸፈኑባቸው ድንጋጌዎች ግን የስር ፍ/ቤት የጠቀሣቸው አለመሆናቸውን በመግለጽ አግባብነት አላቸው ወደ አላቸው ድንጋጌዎች ለውጦ ተጠሪን ጥፋተኛ አድርጓል። ይህ ችሎት ለሕግ አንቀጾች መቀየር ዋነኛ ምክንያት አድርጐ የያዘው ተጠሪ በወቅቱ በ1ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ተሰድቧል የተባለው የስድብ ዓይነት ሲታይ ለወንጀል ድርጊቶቹ ቅድመ ዝግጅት እና ማነሣሣት፣ የክፋትና የጭካኔ ስሜት በሚያሣይ ሁኔት ሣይሆን በምስክር ድርጊት የተነሣ በንዴት ስሜት ውስጥ በመግባት እራሱን መቆጣጠር በማይችልበት ሁኔት ውስጥ ሆኖ ነው የሚለውን ነጥብ ነው።

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ መሰረት አንድን ሰው የሚያስጠይቀው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በዘጋጅት ሲፈፀም ወይም በቁጥር 81 ወይም በቁጥር 83 የተመለከቱት አክባድ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ ወይመ አደገኛ መሆኑኑ ሲያመለክቱ ስለመሆኑ በተጠቃሹ አንቀጽ ተደንግጓል። በዚሁ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለውም ለወንጀሉ ማቋቋሚያ መሆናቸውንና መክንያቶቹም ወንጀሉን ለማቋቋም በአንድነት ተጣምረው መገኘት ሣያስፈልጋቸው በራሣቸው ቁመው የወንጀሉ ማቋቋሚያ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑን ነው። በመሆኑም ቅድመ ዝግጅት እና የክፋትና የጭካኔ ስሜት ተጣምረው የመገኘት ሁኔታ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ድንጋጌ ብቸኛ የወንጀሉ መቋቋሚያ ነጥቦች አይደሉም። ይልቁንም በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሣቸው መቆም የሚችሉ ናቸው።

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ባለቤቱን ለግደል የ1ኛዋ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ስድብ እንደምክንያት የማይወሰድ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ያመነበት ጉዳየ ሆኖ የምስክሯ አድራጐት ግን የተጠሪን የክፋትና የጭካኔ ስሜት የሚያሣይ ሁኔታ እራሱን በማዘጋጀትና በማነሣሣት በመሆኑ አያሣይም በሚል ተደምድሟል። ይሁን እንጂ ይኸው ድምዳሜ ፍ/ቤቱ የምስክሯ አድራጐት ባለቤትን ለመግደል ምክንያት ሊሆን አይችልም ብሎ ከተነሣበት ነጥብ ጋር የሚጋጭ ነው ከመባሉ በተጨማሪ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሣቸው ሊቆሙ የሚችሉ መሆናቸውን ያላገናዘበ ነው። ሚች በወቅቱ ወልዳ የተኙች አራስ ከመሆኗም በተጨማሪ በወቅቱ ያደረገችው ምንም አድራጐት የሌለ ሆኖ ተጠሪ ለሕልፈት የዳረጋት ግንባሯ ላይ በሁለት ጥይት በመምታት መሆኑ ሲታይ የተጠሪን የጭካኔ እና የክፋት ስሜት በግልጽ የሚያሣይ ነው።

ድርጊቱ የተፈፀመው በውድቅት ሌሊት የጦር መሣሪያን በመጠቀም በወቅቱ አራስ በመሆኗ ልዩ ድጋፍ በሚያስፈልጋትና እንስት መሆኗ ሲታይም አድራጐቱ በቁጥር 81(1) (ሐ) እና (ሠ) ስር እንደተመለከተው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522 (1) (ሀ) ስር የሚሸፈን መሆኑን የሚያሣይ ነው ተጠሪ አድራጐቱን የፈፀመው ማንነቱን ተቀብላ አብራው በመኖር ሁለት ልጅ በወለደችለት ባለቤቱ ላይ መሆኑ ከወ/መ/ሕ/ቁ.83 አኳያ ሲታይ አክባጅ ምክንያት መኖሩን የሚያሣይና በግፍ ሰው የመግደል አድራጐትን የሚያቋቁም ነው። በ1ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ተነገረ የተባለው ስድብ በማናቸውም መመዘኛ አራስ የሆነችን የትዳር አጋር በክፋትና በጨካኝነት መንፈስ ለሕልፈተ-ሕይወት ለመዳረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ሊባል አይችልም። በመሆኑም ተጠሪ በባለቤቱ ላይ የፈጸመው ግድያ ከቁጥር 81 (1) (ሐ እና) እና በቁጥር 83 ድንጋጌ አኳያ ሲታይም በግፍ መግደሉ ተረጋግጦ እያለ ለዚህ አድራጐት አግባብ ተብሎ በወ/መ/ሕ/ቁ.523 ስር ጥፋተኛ መባሉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል በ2ኛው ክስ ለተጠቀሰው አድራጐት አግባብነት አለው የተባለው የወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 524/ለ/ ሲታይ የምስክሯ አድራጐትና ከነባራዊው ሁኔታ አኳያ ሲመዘን ባግባቡ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም። በዚህም መሠረት ተጠሪ በባለቤቱ ላይ ለፈፀመው የግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ሲሆን በ2ኛው ክስ በተጠቀሱት የግል ተበዳዮች ላይ ለፈፀመው አድራጐት ደግሞ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተለወጠው ድንጋጌ መሠረት ሆኖ አግኝተናል። ይህ የሚያስገነዝበው ደግሞ ተጠሪ በዚህ ችሎት ጥፋተኛ የተባለው የበታች ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሣኔ የሰጡባቸው ድንጋጌዎች መሻሻላቸውን ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለባቸው ድንጋጌዎች መሠረት ነው። በአጥፊ ላይ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወ/መ/ሕ/ቁ. 86 ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው። ችሎቱም እነዚህን ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም። ተጠሪ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ብዙም ባለመማሩ የዕውቀት ማነስና የመንፈስ ልልነት ያለበት መሆኑ እና የኋላ ታሪኩ ሲታይም መልካም የነበረ መሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዙለት የሚገቡ መሆኑን ከወ/መ/ሕ/ቁ. 86 እና 79 (1) (ሀ) ድንጋጌዎች ተገንዝበናል። እነዚህን 258 259 ምክንያቶች መሠረት ስናደርግ ደግሞ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የመጀመሪያው ክስ ድንጋጌ ያስቀጣው የነበረው እድሜ ልኩን ሁኖ በወ/መ/ሕ/ቁ. 184 /ለ/ መሠረት መጠኑ መቅለል ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል።

ሲጠቃለልም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባለቤቱን በመግደሉ ሊጠየቅ የሚገባው ድንጋጌ ተራ የሰው ግድያ ወንጀለ በሚያስጠይቅበት ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የተጠሪ አድራጎት በግፍ ሰው መግደለ የሚሸፈንና የቅጣቱ መጠንም ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል.....ይላል

3. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539 (1-ሐ) መሠረት አንድ ሰው ሌላ ወንጀልን ለመፈፀም እንዲመቸው ወይም የተፈፀመ ወንጀል እንዳይገለጽ ለማድረግ ሲል ሰው የገደለ እንደሆነ በከባድ ሰው መግደል ወንጀለ ልጠየቅ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው የውንብድና ወንጀል ለመፈፀም የኃይል ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት የሰው ህይወት ካለፈ የወንጀሉ አድራጊ በከባድ የውንብድና ወንጀል የሚጠየቅ መሆኑ በአንቀጽ 671 (2) ላይ ተደንግጓል፡፡ በሁለቱ አንቀፆች መካከል የሚኖረው ልዩነት ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው በዝርፍያ ተግባር ላይ እያለ ሰው ቢገድል ከሁለቱ በየትኛው አንቀጽ ነው የሚከሰሰው? ተወያዩበት፡፡

4. አንድ የሙያ ግዴታ ያለበት ሰው በቸልተኝነት ሰው ከገደለ ተጠያቂ የሚሆነው በወንጀለ ህጉ አንቀጽ 543 (2) መሠረት ነው፡፡ ይህም ማለት የሞቱት ሰዎች ቁጥር ከሁለት በላይ ከሆነ ግለሰቡ ተጠያቂ የሚሆነው በአንቀጽ 543 (3) መሠረት መሆኑ ስለተደነገገ በአንቀጽ 543 (2) መሠረት አጥፊው ተጠያቂ የሚሆነው የሞተው ሰው ቁጥር አንድ ብቻ ሲሆን ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሞተው ሰው ቁጥር አንድ ብቻ ቢሆንም አጥፊው ጥፋቱን የፈፀመው ግልፅ የሆነ መመሪያ ወይም ደንብ በመጣስ ከሆነ ጥፋተኛ የሚሆነው በአንቀጽ 543 (3) መሠረት መሆኑን ድንጋጌው ያስረዳል፡፡ በመሆኑም፡-

   ሀ ግልፅ የሆነ መመሪያ ወይም ደንብ የሚባለው የትኛው ነው? ለምሳሌ በመንገድ ላይ የሚታዩትን የትራፊክ ምልክቶችን በመተላለፍ ወይም ትርፍ ጭኖ እያለ አንድ ሰው ገጭቶ የገደለ አሽከርካሪ የሚጠየቀው በአንቀጽ 543 (2) ነው ወይስ በአንቀጽ 543 (3)? እነዚህ እንደ ግልፅ መመሪያ ወይም ደንብ ልቆጠሩ ይችላሉን?

   ለ ግልጽ የሆነ መመሪያ ወይም ደንብ መሠረት በማድረግ በአጥፊው ኃላፊነት ውሳኔ ላይ ለመድረስ የግልጽ መመሪያዎቹ መጣስ ለአደጋው መንስኤ መሆናቸው በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት ወይስ ለአደጋው መንስኤ መሆን አለመሆናቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ የመመሪያ ወይም የደንቡ መጣስ መረጋገጡ ብቻ በቂ ነው?

ሐ ከዚሁ ጋ በተያያዘ ግልፅ የሆነ መመሪያ ወይም ደንብ የሚባለው ምን ዓይነት ደንብ ወይም መመሪያ ይመስላችኋል? አንዳንድ የህግ ባለሙያዎች ግልጽ መመሪያ ወይም ደንብ ማለት ከባለሙያዉ ዉጪ ለማንኛዉም ሰዉ ግልጽ የሆኑና የደንቦቹን ወይም የመመሪያዎቹን አስገዳጅነት ከባለሙያዉ ዉጪ ማንኛዉም ሰዉ ሊያዉቃቸዉ የሚችላቸዉ መመሪያዎች ወይም ደንቦች ናቸዉ ይላሉ፡፡ በዚህ ሃሳብ ትስማማላችሁ? የሚትስማሙ ከሆኔ ከዚህ ሃሳብ አንፃር ከሹፍርና ሙያ ጋር በተያያዜ ግልጽ መመሪያ ወይም ደንብ ልሆኑ ይችላሉ የሚትሏቸዉን ነጥቦች እንደ ምሳሌ በማንሳት ተወያዩ፡፡

5. ማናቸውም የመኪና አሽከርካሪ በተለዬ ሕይወትን፤ ጤንነትን ወይም ደህንነትን የመጠበቅ የሙያ ግዴታ አለበት ተብሎ ሊወሰድና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 (2) ተጠያቂ ሊሆን ይችላል? ወይስ ሹፌርነት በሙያነት ይዘው የሚሰሩበትን ነው ድንጋጌው የሚሸፈነው?

6. አንድ ሹፌር በጫናቸው ሰዎች ላይ ወይስ በሌሎች ሰዎች ላይ በቸልተኝነት ሞትን ሲያስከትል ከዚህ በላየ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው ከዚህ አኳያ የሚከተለውን የፍርድ ቤት ውሳኔ ሀተታ አግባብነት መርምሩ፡፡

7. "... ይህ አንቀጽ ኃላፊነቱን በሐኪሞችና በነርሶች ላይ ብቻ አይወስነውም፡፡ ሙያተኛ የሚለው ቃል... የሰውነታቸው ደህንነት ጥበቃ በእነርሱ ስር የሚገኙትን ሰዎች ህይወትና ጤና በተለይ እነዲጠብቁ የሥራ ተግባራቸው የሚያስገድዳቸውን ሰዎች ይመለከታል፡፡ ሙያተኛ የሚለው ቃል የአውሮፕላን ነጂዎችን የአውቶቡስና ሌሎች የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች ሾፌሮችን ይጨምራል፡፡ ሆኖም የእነዚህ ሰዎች ግዴታ በአጠቃላይ ሰዎችን ሁሉ የሚመለከት ሳይሆን በተለይ እነሱ ኃላፊነቱን ለወሰዱባቸው ሰዎች ማለትም በአውሮፕላን ውስጥ ላሉ ተሳፋሪዎችና የአውቶቡስ ተሳፋሪዎች ሲሆን እነዚህ ሙያተኞች ለእግረኞች ወይም በማመላለሻው ውስጥ በሌሉ ሰወች ከሚኖባቸው ጠቅላላ ግዴታ በቀር ልዩ ግዴታ የለባቸውም፡፡" በማለት ከመኪና ውጭ ላለ ሰው ሹፌሩ የሚጠየቀው እንደማንኛውም በቸልተኝነት ሰው የገደለ ግለሰብ ነው የሚል አቋም በመያዝ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት - <u>በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል</u>

በአካል ላይ ጉዳት የማድረስ ተግባር የወንጀልም የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊያስከትል የሚችል ተግባር ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 16 ላይ እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በአካሉ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ይዜንን መሠረታዊ

የሰው ልጆች መብት ጥበቃ ለማድረግ የወንጀል ድንጋጌዎችን አስቀምጧል። ለወንጀል ድንጋጌዎቹ በመርህነት የተቀመጠው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 553 እንደሚያስረዳው ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በሌላ ሰው አካል፣ አዕምሮ ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በሰዎች አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ተግባሮች ታስቦ ወይም በቸልተኝነት በማናቸውም ዓይነት ዘዴ ቢፈፀሙመት ለቅጣት ይዳርጋሉ።

አስቦ በሰዉ አካል ወይም ጤና ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀልን ህጉ ቀላልና ከባድ የአካላት ጉዳት በማለት በተነፃፃሪነት ያስቀምጣል። የወንጀል ህጉ አንቀጽ 555 ስለ ከባድ የአካል ጉዳት የሚደነግግ ሲሆን በህጉ አንቀጽ 556 ደግሞ ቀላል የአካል ጉዳት ተደንግጎ እናገኛለን።

የህጉ አንቀጽ 555 አስቦ ከባድ የአካል ጉዳት የመፈፀም ወንጀልን የሚያቋቁሙ ሦስት ምክንያቶችን በአማራጭ መልክ ያስቀምጣል። በዚህም መሠረት፤ አንድ ሰው ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ከሦስቱ ምክንያቶቹ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ መሆኑ ከህጉ መረዳት ይቻላል። የመጀመሪያው በአንቀጽ 555(ሀ) የተመለከቱ ሲሆን፤ የደረሰው ጉዳት ለተጐጂውን ሕይወት በሚያሰጋ ወይም በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ጉዳት ከሆነ ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት በ555 (ለ) ስር የተመለከቱ ስሆን የመጀመሪያው ምክንያት (ውጤት) ባይከተል እንኳን በጉዳቱ ምክንያት ለሰውየው አስፈላጊ ከሆኑት ብልቶች ወይም ህዋሳቶቹ አንዱ ከጐደለ፤ እንዳያገለግሉት የሆኑ እንደሆኔ ወይም በሚያሳቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ እንደሆነ የደረሰዉ ጉዳት ከባድ የአካል ጉዳት መሆኑ ነዉ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ሁኔታዎች (ውጤቶች) ባይኖሩም እንኳ የደረሰው ጉዳት ከባድ የአካል ጉዳት የሚባለውና ጉዳት አድራሹም በከባድ ጉዳት በማድረስ ወንጀል የሚጠየቀው በማናቸውም መንገድ የደረሰው ጉዳት ከባድ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ። ስለሆነም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 555 (ሀ፤ለ) ሥር የተቀመጡት ውጤቶች ባይኖሩም እንኳ በማንኛውም መንገድ ታይቶ በተጐጂው ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳት አድራሹ በ555 (ሐ) ሥር ሊጠየቅ የሚችል መሆኑ ነው።

ቀላል የአካል ጉዳት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 556 ሥር የተደነገገ ሲሆን የደረሰው ጉዳት ቀላል የአካል ጉዳት የሚባለው በጉዳቱ ምክንያት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 555 (ከባድ የአካል ጉዳትን የሚያቋቁሙ) ስር የተመለከቱትን ዉጤቶች ያላስከተለ እንደሆኔ ነዉ። (የህጉ አንቀጽ 556 /1/

ይመለከተዋል)፡፡ ቀላል የአካል ጉዳት በራሱ በሁለት ተከፍሎ የሚታይ መሆኑን ከአንቀጹ መረዳት ይቻላል፡፡ በአንቀጽ 556/2/ ከተመለከተው መረዳት እንደሚቻለው በአንቀጽ 556/1/ ሥር የደረሰው ጉዳት ቀላል ቢሆንም ጉዳት አድራሹ የተጠቀመበትን መሣሪያ፤ የሙያ ሁኔታንና የተጐጂውን ማንነት ግምት ውስጥ በማስገባት በተከሳሹ ላይ ሊጣል የሚችል ቅጣት የሚከብድ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአንቀጽ 556/1/ ስር ጥፋተኛ የሚሆን ሰው ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጫ የሚቀጣ ሲሆን በአንቀጽ 556/2/ ስር ጥፋተኛ የሚሆን ሰው ደግሞ የሚቀጣው ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት የሚቀጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በአንቀጽ 556/2/ ሥር ቅጣት እንድከብድ ተደርጎ የተቀመጠበትም ምክንያት የደረሰውን ጉዳት ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት ሳይሆን ጥፋተኛው ጉዳት ያደረሰው በመርዝ ወይም በገዳይ መሣሪያ ወይም የአካል ጉዳት ለማድረስ በሚችል በማናቸውም ሌላ መሣሪያ በመጠቀም እንደሆነ፤ ወይም ጥፋተኛው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታን በመተላለፍ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ወይም ተጐጂው ደካማ በሽተኛ ወይም ራሱን ለመከላከል የማይችል ሰዉ መሆኑ ከተረጋገጠ ሆኖ የእነዚህ ሁኔታዎች መኖር በአንዳራዊ መልኩ ሲታይ የአድራጊዉን አደገኛነት፤ ጨካኝነትና ነውረኛነት ያሳያል ተብሎ ታስቦ እንደሆኔ መገመት አያዳግትም፡፡ ስለሆነም ተከሳሹ ከሁለቱ ንዑስ አንቀጾች (556፤1 556፤2) አድራጊዉ በየትኛው ስር እንደሚወድቅ ለመወሰን ግምት ውስጥ መግባት ያለበት የደረሰው የአካል ጉዳት ደረጃ (ከባድና ቀላል መሆን) ሳይሆን በህጉ በዝርዝር የተቀመጡና ከላይ ያየናቸው ምክንያቶች መኖራቸውና አለመኖራቸውን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የደረሰው ቀላል የአካል ጉዳት ሆኖ ጉዳቱ የደረሰው በአንቀጽ 556/2/ ሥር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጪ ከሆነ ግለሰቡ ጥፋተኛ የሚሆነው በአንቀጽ 556/1/ ሥር ነዉ፡፡

ለማጠቃለልም በዋናነት በከባድ የአካል ጉዳትና በቀላል የአካል ጉዳት መካከል ቅጣትን በተመለከተ የሰፉ ልዩነት መኖሩን እንዲሁም ቀላል የአካል ጉዳት ሆኖ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መካከል በእራሱ ሰፋ ያሉ የቅጣት ልዩነቶች ስላሉ በእያንዳንዱ አንቀጽ መካከል ያለውን ድንበር ማበጀቱ የወንጀል ህግን (ቅጣትን በተለከተ) አጠቃላይ ዓላማ ከማሳካት አንፃር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 555 ስር የተደነገገ ሲሆን ለወንጀሉ ግልፅ የሆነ ትርጉም ባይሰጠውም በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ቋሚ የሆነ ጠንቅ

የሚፈጥር ቁስል፣ አካል ማጉደል፣ በአሰቃቂ ሁኔታ መልክን ማበላሸት እና በተመሳሳይ ደረጃ የሚመደቡ ከባድ ጉዳት ወይም አደገኛ በሽታ የመሳሰሉትን የሚያካትት ስለመሆኑ ግን ተመልክቷል። በድንጋጌው እና በተመሳሳይ ጉዳዮች ዙሪያ ለመወሰን ስለጉዳቱ መጠንና ተፈጥሮ አጠራጣሪ ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ አግባብነት ባለው ባለሙያ ጉዳዩ እንዲመረመር ማድረግ እንሚቻል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 554 ላይ ተደንግጓል።

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 556 ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀልን ይመለከታል። የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 559 በቸልተኝነት ስለሚፈፀሙ ቀላል ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀሎች ይደነግጋል። አንቀጽ 560 ደግሞ እንደነገሩ አካባቢ ሁኔታ እስከ ሦስት ወር ቀላል እስራት ሊያስቀጡ የሚችሉ የአካል ጉዳት ወይም በጤንነት ላይ ጉድለትን ሳያደርስ በሌላ ሰው ላይ የሚፈፀምን የእጅ እልፊት ወይም የመጋፋት ድርጊት ይመለከታል። በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ፓራግራፍ ሦስት ላይ እንደተመለከተው ቀላል የሆኑ ሰንበሮች፣ የደም መቋጠር ምልክቶች ወይም በቶሎ የሚያልፍ ሕመም ወይ ሥቃየረ እንደ አካል ጉዳት ወይም እንደ ጤና ጉድለት አይቆጠሩም ተብሎ ተመልክቶ እናገኘማለን።

በዚህ ላይ ብዙ ጊዜ የሚስተዋለው ችግር በአንደኛው እና በሌላኛው አንቀጽ በተመለከተው ያለው ድንበር የሚወሰነው እንዴት ነው የሚለው ነው። ማለትም የደረሰው ጉዳት ከባድ የአካል ጉዳት፣ ቀላል የአካል ጉዳት ወይም የእጅ እልፊትን በሚመለከተው ድንጋጌ ስር የሚወድቅ መሆኑን ለመለየት የተለያዩ ወገኖች የተለያዩ መስፈርት ሲከተሉ ይስተዋላል። ለምሳል አንድ ሰው አፍንጫውን ተመትቶ ከደማ ቀላል የአካል ጉዳት ካልደማ ግን የእጅ እልፊት ነው የሚሉ አሉ።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች፣</u>

1. አንድ ሰው በቦክስ ፊቱ ላይ ተመትቶ ያበጠ ቢሆንም ደም የቋጠረ ከመሆኑ በቀር የመድማት ሁኔታ ሳይታይበት ቢቀር ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የሚጠየቀው በየትኛው ድንጋጌ ነው?
2. የግል ተበዳይ በተከሣሽ በዱላ እጁን ተመትቶ አጥንቶ ተሰብሮ ነበር። ሕክምና አድርጎ ስብራቱ ተጠግኗል (ድኗል)። ተከሣሹ መጠየቅ ያለበት በከባድ ወይስ በቀላል አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ይመስልዎታል?

3. ጥርስ በማውለቅ ደረጃ ጉዳት ማድረስ በየትኛው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ የሚሸፈን ይመስልዎታል?
4. የሚከተለውን የዐቃቤ ሕግ ውሳኔ አግባብነት መርምሩ፤

"... ተከሣሽ ብረት የግል ተበዳይን አፍና አፍንጫ በመምታት በፈፀመው ተግባር የግል ተበዳይ ጥርስ የተንቀሳቀሰ እንዲሁም ሁለት የፊት ጥርሶች የተሸረፉ ቢሆኑም ጥርሶቹ እንዳያገለግሉ የማድረግ ውጤት ስለሌለው፣ በሚያሰቅቅና ጉልህ በሆነ ሁኔታ የግል ተበዳይን መልክ የሚያበላሽ ባለመሆኑ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ በሰው ሰራሽ ጥርስ መተካት የሚቻል ስለሆነ በተከሣሹ ላይ ታስቦ በሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ቀርቦ የነበረው ክስ በቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተሻሽሎ የወንጀል ክሱ እንዲቀርብ እንዲደረግ... ተወስኗል።

ንዑስ ክፍል ሦስት - <u>የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት</u>

ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል፣ በባንክ ተቀማጭ ያለው ሰው ገንዘብ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሀተታ የሌለው ትእዛዝ የሚሰጥበት ሰነድ ነው። ከኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል፣ በባንክ ተቀማጭ ያለው ሰው ገንዘብ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሀተታ የሌለው ትእዛዝ የሚሰጥበት፣ ገንዘብን ተክቶ ክፍያን የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ሰነድ ነው። ምን ያህል ስፋት እንዳለው በጥናት መደገፍ ያለበት በመሆኑ ምክንያት ደፍሮ ለመናገር ቢያስቸግርም ቼክን አስመልክቶ ከሚስተዋሉት ነባራዊ ሁኔታዎች አንደኛው ቼክን በዋስትና ወይም በመያዣነት የመስጠት ጉዳይ ነው። ከሌሎች የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች (negotiable instruments) በተለዬ ቼክ ካለው ልዩ ባህሪ አንጻር ቼክን በዋስትና ወይም በመያዣነት መስጠት እንዴት ነው ሊደረግ የሚችለው የሚለው በተለይም ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል ከመሆኑ ጋር ያለውን ልዩ ባህሪውን ተከትሎ የሕግ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ሆኖ በተግባር ግን ሰዎች በተለይም በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት ቼክን ለዋስትና (ለመያዣ) የሚሰጡበት ሁኔታ እንዳለ ነው። ከዚህም አኳያ በተግባር ቼክ በዋስትና/በመያዣነት እያገለገለ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል።

በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ በቼክ ለመጠቀም ከሁሉ አስቀድሞ መታወቅ ያለበት ቼክ ቆርጦ የሚሰጠው ሰው (አውጭው) በባንክ የተቀመጠ እርሱ የሚያዝበት ገንዘብ ሊኖረው ይገባል።

አውጭው ባንክ ያለው የሚያዝበት ሂሳብ በቼኩ ላይ እንዲከፈል ካዘዘው ገንዘብ በላይ ወይም ቢያንስ ቢያንስ በቼኩ ላይ እንዲከፈል ካዘዘው ገንዘብ ጋር እኩል የሆነ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለዉ ቼክ ቆርጦ ለሌላ ሰዉ የሚሰጥ ሰዉ አስቀድሞ ያለበት ማረጋገጥ ያለበት በቼኩ ሊያዝበት የሚችል ገንዘብ መኖሩን ወይም ከባንኩ ያለዉ ገንዘብ በቼኩ ከሚያዝበት የገንዘብ መጠን ጋር ቢያንስ የሚመጣጠን መሆኑን ነዉ፡፡

ቼክ ለባንክ እንደቀረበ የሚከፈል ሰነድ እንደመሆኑ መጠን የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ፈርሞ መስጠት የወንጀል ተጠያቂነትንም የሚያስከትል ድርጊት ነው፡፡ በመሆኑም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 ላይ “ማንም ሰው ቼክ በሚወጣት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ (የሰጠ) እንደሆነ በቀላል እስራት ወይም እንደነገሩ ከባድነት ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል” ተብሎ ተመልክቷል፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ እንደተመለከተው ደግሞ አንድ ሰው ቼክ በሚያወጣት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን ባያውቅም በቸልተኛነት በቂ ገንዘብ አለ ብሎ በመገመት ወይም ባለማመዛዘን ቼክ ያወጣ (የሰጠ) እንደሆነ በመቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል ተብሎ ተመልክቷል፡፡

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አንቀጽ በወንጀል ሕጉ “ማታለልን ያካተቱ ወንጀሎች” በሚለው ክፍል ሥር የተመለከተ ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ በአጠቃላይ 14 አንቀጾች ተደንግገው እናገኛቸዋልን፡፡ በዚህ ከፍል ከተደነገጉት ጉዳዮች ውስጥ አንቀጽ 692 አታላይነትን የሚመለከት ሲሆን አንቀጽ 694 “በተጭበረበረ ሁኔታ የአክሲዮን ገበያን ንግድ ማካሄድ”፣ አንቀጽ 695 “በአክሲዮኖች ወይም በሸቀጦች መቆመር”፣ አንቀጽ 698 “ኢንሹራንስ በሚመለከት የሚፈፀም የአታላይነት ድርጊት” እና አንቀጽ 700 ላይ ደግሞ “በሕዝብ እምነት በመጠቀም ማታለል” በሚሉ ርእሶች እና ሌሎች መሰል ተግባሮች በወንጀልነት ተቆጥረው እንደሚያስቀጡ የተፈረጁ ጉዳዮች ስለመሆናቸው ተመልክቶ እናገኛለን፡፡

በ1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥም በሕጉ ቁጥር 657 ላይ ከ1997 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 ላይ ከተመለከተው ጋር ተቀራራቢነት ያለው ድንጋጌ ተደንግጎ የነበረ ሲሆን ምናልባት እንደልዩነት ከተጠቀሰ የቀድሞው ሕግ ቁጥር 657ን የተላለፈ ሰው ስለ አታላይነት በተመለከተው ድንጋጌ (በቁጥር 656) ላይ በተመለከተው ቅጣት መሠረት ይቀጣል በማለት ለሁለቱ ድንጋጌዎች ተመሳሳይነት ያለው ቅጣት ያስቀምጥ የነበረ ሲሆን በ1997 የወጣው የወንጀል ሕግ ግን በአንቀጽ 692 ስለ አታላይነት ከተመለከተው ቅጣት በተለዬ የቅጣቱን ጣራ ከፍ በማድረግ ለአንቀጽ 693 ቅጣት አስቀምጧል። ከዚህ ውጭ በሁለቱ የወንጀል ሕጎች ቼክን አስመልክቶ የተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረታዊ ልዩነት ያላቸው ሆነው አይታዩም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በቂ ገንዘብ ሳይኖራቸው ቼክ ቆርጠው የሰጡ ሰዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693 ላይ የተመለከተውን ተላልፋችኋል ተብለው ክስ ሲቀርብባቸው ከሚያነሱት ክርክር አንደኛውና ዋነኛው ቼኩን ቆርጠን የሰጠነው በዋስትና ወይም በመያዣነት መልክ ነው እንጅ ተቆርጦ የተሰጠው ሰው በቀጥታ ከሚመለከተው ባንክ ሄዶ ገንዘቡን ጠይቆ እንዲወስድ አይደለም፣ ይህንንም አሁን በግል ተበዳይነት የቀረበው ሰው በደንብ ያውቃል። ለዚህም ምስክሮችን ማቅረብ እንችላለን ወይም ሌላ ማስረጃ ማቅረብ እንችላለን የሚሉ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ይገኙበታል። እንዲሁም ቼኩን ቆርጦ የሰጠው ሰው በባንክ ሂሳቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቁ ሁሉ ሰዎች ባላቸው ግንኙነት መነሻ ቼኩን የሚቀበሉበት ሁኔታም ይታያል።

በመሆኑም በሥራ ላይ ከሚስተዋሉት የትርጉም ልዩነት ከሚታዩባቸው ጉዳዮች አንደኛው ከዚህ በላይ በተጠቀሰውና መሰል ሁኔታዎች ዙሪያ ቼክን አስመልክቶ ያለው የወንጀል ተጠያቂነት እንዴት ሊታይ ይገባል የሚለው ጉዳይ ነው። ቼኩ ለክፍያ በሚቀርብበት ጊዜ የሚከፈል በባንክ ሂሳቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ ቼክ ቆርጦ መስጠት በፍትሐብሔር ከሚያስከትለው ተጠያቂነት ባሻገር የወንጀል ተጠያቂነትን እንዲያስከትል የተደረገበት ምክንያት ለምንድነው? የሚሉት ክርክሮችም ሲነሱ ይስተዋላል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አንቀጽ “ማታለልን ያካተቱ ወንጀሎች” በሚለው ክፍል ሥር የተመለከተ በመሆኑ በድንጋጌው አተረጓጎም ላይ አንዳንድ ጊዜ ልዩነቶች ይስተዋላሉ።

አንዳንዶቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693 መሠረት ወንጀል አንድ ሰው ወንጀል መፈፀሙን ለማረጋገጥ በአንቀጽ 692 ስለ አታላይነት የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፤ ስለሆነም አንድ ቼክ ተፈርሞ የተሰጠው በዋስትና ወይም በመያዣነት መሆኑ ከተረጋገጠ የማታለልን ወንጀል የሚያቋቁሙት ነጥቦች ስለማይሟሉ በአንቀጽ 693 መሠረት ወንጀል የለም ይላሉ፡፡

አንዳንዶቹ ደግሞ ቼክ በዋስታነም ሆነ በመያዣነት እንዲሰጥ የተሰራ አይደለም፤የአንቀጽ 693 ድንጋጌ ዓላማም በቼክ የሚገለገሉ ሰዎች በባንክ ውስጥ ገንዘብ ያላቸው መሆኑን ሳይረጋግጡ ቼክ ፈርመው እንዳይሰጡ ለመከላከል ነው፤ ስለሆነም በቼክ ላይ የሚፈፀም አግባብነት የሌለው ተግባርን ለመቋቋም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693 ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጡ ብቻውን በቂ ነው ይላሉ፡፡

ይህን የአተረጓጎም ችግር (በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 657 ድንጋጌ ላይ የነበረውን) መነሻ በማድረግ በ1982 ዓ.ም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ባወጣው መመሪያ አንቀጹ "...ራሱን የቻለና የተሟላ በመሆኑ የአታላይነት ወንጀልን የሚያቋቁሙትን ነጥቦች ከሚደነግገው ከቁጥር 656 (ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንጻር አንቀጽ 692 ማለት ነው) ጋር መያያዝ የለበትም፤ ስለዚህም አንድ ቼክ በዋስትና ወይም በመያዣነት የተሰጠ ከሆነና ይህንንም ሰጭና ተቀባይ ካወቁ የማታለል ወንጀል ተፈጽሟል ለማት አይቻልም በማለት ለሕጉ የሚሰጠው ትርጉም ከሕጉ ዓላማና መንፈስ ውጭ በመሆኑ ይህን ሕግ በመተላለፍ የሚከሰስን ሰው ጥፋተኛ ለማድረግ የሚያዝዝበት ገንዘብ አለመኖሩን ወይም የሚያዝዝበት ገንዘብ ማለቁን እያወቀ ወይም ቼኩ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያገበት የሚበቃ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ መፈረሙን ብቻ ማረጋገጥ በቂ ነው" በማለት በዚሁ መሠረት ተመሳሳይ የሆነ አተረጓጎም እንዲኖር ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንድ የወንጀል መዝገብ በሰጠው ውሳኔ በድንጋጌው ጥፋተኛ ለማለት በቼኩ ላይ የሚፈርመው ሰው ሌላውን ሰው ለማታለል ያደረገው መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት፤ ሌላውን ሰው ለማታለል እና ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት እስካልሆነ ድረስ የሕጉ አፈጻፀም ትርጉም የለሽ ስለሚሆን የሕጉ አንቀጽ መንፈስ ማታለል መሆን ይኖርበታል፡፡ የወንጀል ሕጉ የሚጠብቀው ቼክ ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ አገልግሎት

ላይ እንዳይውል ሳይሆን በቼኩ አማካኝነት መታለል የሚችለውን ሰው ነው። ከዚህም አንጻር የወንጀል ድርጊቱ አፈጻፀም የአንድ ሰው የሆነውን መብት አላግባብ ለማግኘት በሚል መታየት ይኖርበታል። ቼክ ላይ ተፈርሞ የሚሰጥበት ሁኔታ በተለያዩ ምክንያት በመሆኑ በቼክ ላይ ፈርሞ መገኘት ብቻ ወንጀሉን ለማቋቋም በቂ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ስለሆነም ቼኩ የተፈረመው ሌላውን ሰው ለማታለል ሲባል መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል በማለት ተመልክቷል።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

(1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693ን በመተላለፍ በቼክ ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ተሟልተው መገኘት ያለባቸው ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ ተወያዩበት።

(2) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 ድናጌዎች ዓላማ ምን ይመስለዎታል?

(3) አንዳንድ ሰዎች ቼክ ቆርጠው ከሰጡ በኋላ ክፍያውን የሚፈፅመው ባንክ ቆርጠው ለሰጡት ቼክ ክፍያ እንዳይፈፅም ያግዳሉ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ የባንክ ሂሳባቸውን የሚዘጉ ሰዎችም አሉ። እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትሉ እንደሆነ ተወያዩበት።

(4) የአንድ መንግስት መ/ቤት ኃላፊ በመሥሪያ ቤቱ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ካለው ገንዘብ በላይ የሆነ ቼክ ፈርሞ ቢሰጥ የወንጀል ተጠያቂነት ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ መርምሩ።

(5) በአንድ ጉዳይ የአመልካች አቤቱታ የሚመለከተው ተከሣሽ በመጀመሪያ ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ብር 307500.00 (ሦስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር) ተከፋይ እንዲሆን ቼክ ቆርጠው ሰጥተዋቸው ባንክ ሲሄዱ ተጨማሪ ሌላ ፊርማ ያስፈልጋል በማለት ተመላሽ እንደተደረገባቸው፣ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ በ15/1997 ዓ.ም ተከፋይ እንዲሆን ተከሣሽ ቼክ ቆርጠው ሰጥተዋቸው የነበረ ቢሆንም ባንክ ሲሄዱ በ1997 ዓ.ም ቼክ አልሰጠንም እንዲሁም በቂ ገንዘብ በተከሣሽ የባንክ ሂሣብ ውስጥ የለም ተብለው የተመለሱ መሆናቸውን በመግለፅ ባቀረቡት ክስ መነሻ ምርመራው በፖሊስ ተጣርቶ በዐቃቤ ሕግ አማካኝነት በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶ የነበረ ቢሆንም በአመልካችና

በተከሣሽ መካከል የነበረው የፍትሐብሔር ክስ በቂ ማስረጃ ተብሎ ክሳቸው ውድቅ የተደረገ በመሆኑ እንዲሁም በምስክርነት የተቆጠሩት ግለሰብ በሰጡት ቃል ቼኩ በተከሳሽ ብቻ ሳይሆን በራሱ በምስክሩ ጭምር በጣምራ መፈረም ይገባው እንደነበር፣ ቼኩን ሳይፈርሙ የቀሩት አመልካች ከተከሳሹ ጋር ያደረጉትን ስምምነት ተግባራዊ ሳያደርጉ በመቅረታቸው ምክንያት መሆኑን፣ ከአመልካች ለተከሣሽ የተሰጠ ምንም ገንዘብ እንደሌለና ይልቁንም ቼኩ ለአመልካች ተቆርጦ የተሰጠው ወደፊት ለሚያደርጉት የሥራ ግንኙነት ከተከሳሽና ከምስክሩ የጋራ ሂሳብ ብር አውጥተው በብድር መልክ መውሰድ እንዲችሉ መሆኑን የገለፁ በመሆኑ ጉዳዩ ከፍትሐብሔር ችሎቱ ውሳኔ እና ከዚህ ከምስክሩ ቃል አንጻር ሲታይ ተከሣሹን ጥፋተኛ ለማስባል በቂ አይደለም በሚል ዐቃቤ ሕግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ አግባብነት ላይ ተወያዩበት፡፡

(6) በወንጀል ህጉ አንቀጽ 693 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች ከተሟሉ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ቼክ ፈርሞ ከሰጠዉና ክፍያዉ ከታዘዘለት ሰዉ መካከል የዉል ስምምነት መኖሩ ቢረጋገጥ ቼኩን ፈርሞ በሰጠዉ ላይ ልደርስ የሚችለዉ የወንጀል ኃላፊነት ሊቀር ይችላል ብለዉ ያምናሉ? ለምሳሌ አቶ 'ሀ' በሚያዚያ 30 2003 ዓ.ም ገንዘብ ባንክ የሚያስገባ መሆኑንና አቶ 'ለ' ደግሞ በግንቦት 1 2003 ዓ. ም ገንዘቡን ማዉጣት እንድችል ተስማምተዉ አቶ 'ሀ' በሚያዝያ 15/2003 ቼክ ፈርሞ ለአቶ 'ለ' ቢሰጥና አቶ 'ለ' በሚያዝያ 29/2003 ቼኩን ይዞ ባንክ ሄዶ አቶ 'ሀ' ከአካዉንቱ ገንዘብ እንደለሌዉ ለአቶ 'ለ' ተነገረዉ እንበል፡፡ ይህንኑን መሠረት በማድረግ አቃቤ ህግ በአቶ 'ሀ' ላይ በአንቀጽ 693 መሠረት ክስ ቢመሠርት አቶ 'ሀ' የተባለዉን ገንዘብ በሚያዝያ 30/2003 ገንዘቡን ባንክ የሚያስገባ መሆኑንና በዉላቸዉ መሠረት አቶ 'ለ' ገንዘቡን ባንክ ሄዶ ማዉጣት የሚችለዉ በስምምነቱ መሠረት ግንቦት 1/2003 መሆኑን ገልጾ ቢከራከር ክርክሩ ተቀባይነት ይኖረዋልን? ተወያዩበት፡፡

ምዕራፍ አራት - <u>ልዩ ትኩረት የሚሹ አንዳንድ ወንጀሎች</u>

በዚህ ምዕራፍ የሚሰጠው ሥልጠና ዓላማ ሰልጣኞች በባህሪያቸው ለየት ባሉ ወንጀሎች ማለትም ዓለም አቀዎ ባሕርብ ባቨዙ በመኑ፣ በውኑ ው በአ ር በሕዝብ ላብ ጾዎተቾ ፡ ፔ ባሚቨተርሱ ባታትበር ተሻ ሪትፔ ባሕርብ ባላ ው ባአሸባሪትፔ፣ ባሙስ ፣ ሕገ ወጥ

የሰዎች ዝወውር እና በመሳሰሉት ወት ሎኖ ላቭ ትዛቤ ለማስ በኅ ትው፡፡ በሥልኅ ው መ ረሻ ላቭ ሰልኃ ኣ ኖ ፡-

1. በሕገ መንግሥቱና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች እንዲሁም ስለሽብርተፖቼ፣ ሙስ እና የመሳሰሉት ወንጀሎች ምትትፔ ትዛቤ ቭ ብኃ ሉ፣

2. ስለ ትዚህ ወት ሎኖ ልብ ባህሪቨፔ ቭ ትዘባሉ፣ በሕ ኖ ውስኅ ስለተካተቱፔ ባወት ል ታት ጋዎኖ በቂ ዕውቀፔ ቨ ቾሉ፣

3. የወት ሎኖት ውስብስብትፔ በመረ ፔ በማስረ አሰባሰብ ፣በክስ ዝ ፔ በዎርታ ሂተፔ በባተረ ው በሚቨጾ ው ው ተ ባሮኖ ላቭ ኅ ራፔ ብቃፔ ቨለው ሥራ ለማጾ ወት ባሚቨስኖላ ውት ክህሎፔ ቭ ብኃ ሉ፣

4. በሕገ መንግሥቱና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች እንዲሁም ባሙስ ፣ባሽብርተፖቼ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወት ሎኖ በአ ር በህዝብ ላቭ ባሚቨስጾፔሉፔት አተ ስዌፔ በመረ ፔ፣ በባህሪቨ ው ለባፔ ቨሉ ወት ሎኖት ባወኸሙ ወት ለኣ ኖ ተ ቢውት ቅኃ ፔ ት ቭ ዠ ባማታረ አመለካጾፔ (Attitude) ቨ ብራሉ፤

ተብሎ ቭኅ በቃል፡፡

ክፍል አንድ - <u>በሕገ መንግሥቱ እና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ሕገ መንግሥቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የጋራ ጥቅማቸውን፣ መብታቸውንና ነጻነታቸውን በጋራና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ እና አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመገንባት ያስችላቸው ዘንድ ያፀደቁት የቃል ኪዳን ሰነድ ነው፡፡ የዚህ ሕገ መንግሥትም ሆነ የማናቸውም ሕገ መንግሥት አንደኛው መለያ ባህሪ የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ (supreme) መሆን ሲሆን ከዚህ መለያ ባህሪ የሚመነጨው ሌላው የሕገ መንግሥቱ መገለጫው (feature) ደግሞ ማናቸውም የመንግሥት ሥልጣን የሚመነጨው ወይም የሚቀዳው ከዚሁ ከሕገ መንግሥቱ እና ሕገ መንግሥቱ ውስጥ በተመለከተው መንገድ ብቻ መሆኑ ነው፡፡

ከወንጀል አንጻር የእነዚህ የሕገ መንግሥቱ መገለጫ የሆኑትን ባህሪያት ውጤት ተደርጎ የሚወሰደው አንደኛው ጉዳይ ደግሞ ሕገ መንግሥቱን ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ፣ ለመለወጥ ወይም ለማገድ የሚፈፀም ማናቸውም ድርጊት በወንጀልነት የሚያስጠይቅ ተግባር ነው፡፡ የወንጀል ድርጊቱ እንደተፈፀመ የሚቆጠረው ደግሞ ሕገ መንግሥቱን ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመለወጥ የተደረገው ተግባር የተፈፀመው በሕገ መንግስቱ ከተቀመጠውና ከተፈቀደው ውጭ የተፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ የተመለከተውንና የተፈቀደውን መንገድ ተከትሎ የሚፈፀም ተግባር የመጨረሻ ውጤቱ ሕገ መንግሥቱን መለወጥን ዓላማ ያደረገ ቢሆን እንኳን በወንጀልነት የሚፈረጅና የሚያስጠይቅ አይሆንም፡፡

የፍትህ አካላት እንደማንኛውም የመንግስት አካል የኢ.ፌ.ዲ.ሪን ሕገ መንግስት የበላይነት በማረጋገጥ ረገድ የበኩላቸው ሚና እና ድርሻ አላቸው፡፡ የህገ መንግስቱን የበላይነት የሚያረጋግጡበት የመጀመሪያው መንገድ የህገ መንግስቱን መርሆዎች እና ድንጋጌዎች በማክበር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የፍትህ አካላቱ እና በተቋማቱ ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻቸው የሚሰጧቸው ውሣኔዎችና የሚፈፅሟቸው ተግባራት ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን በጥንቃቄ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ የፍትህ አካላቱ እና በተቋማቱ ተመድበው የሚሰሩ ሰዎች የሚወስኑት ውሣኔና የሚያከናውኑት ተግባር ከህገ መንግስቱ ጋር የማይቃረን መሆኑን ማረጋገጣቸው ብቻ የህገ መንግስቱን የበላይነት ሙሉ በሙሉ አያረጋግጥም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍትህ አካላቱ በሕግ በተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ሕገ መንግሥቱን ወይም ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በመጣስ የሚፈፀሙ ማናቸውንም ዓይነት የወንጀል ድርጊቶች መቆጣጠርና ተፈፅመውም ሲገኙ ለድርጊቶቹ ኃላፊ የሆኑትን ሰዎች በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት ደግሞ በሕገ መንግስቱና በሕገ መንገስታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እና እነዚህ ወንጀሎች ምን ምን ዓይነት መሠረታዊ ባህሪያት እንዳላቸው መረዳት አግባብነት ይኖረዋል፡፡

ንዑስ ክፍል አንድ - <u>በሕገ መንግሥቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

“በሕገ መንግስትና በሕገ መንገስት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ወንጀል” በሚል ርዕስ ስር በአዲሱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የተጠቀሱት እነዚህ የወንጀል ድረጊቶች የተመለከቱት በሕገ መንግስቱና በመንግስት ላይ ስለሚደረጉ ወንጀሎች በሚደግገው የወንጀል ሕጉ ንዑስ ክፍል ስር ነው፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል ስር ከአንቀጽ 238-243 የተዘረዘሩት ስድስት የሚሆኑት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱና በመንግስት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በመሆናቸው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ሕገ መንግስቱንና በሕገ መንግስቱ የተቋቋመውን ሥርዓት የሚጻረሩ ተግባሮች ቢሆኑም ለርዕሰ ጉዳያችን ፍጹም በሆነ ሁኔታ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያለው ድንጋጌ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 ላይ “በሕገ መንግስትና በሕገ መንግሥት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ወንጀል” በሚል ርዕስ ስር የተመለከተው ነው፡፡

በመሆኑም በዚሁ ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ላይ በዋናነት በማተኮር አንዳንድ ነጥቦችን ቀጥለን ለማንሳት እንሞክራለን፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 ድንጋጌ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

አንቀጽ 238 በሕገ መንግሥትና በሕገ መንግሥት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ወንጀል

(1) ማንም ሰው በኃይል፣ በዛቻ፣ በአድማ ወይም ሕገ ወጥ በሆነ በማናቸውም መንገድ አስቦ፡-

(ሀ) የፌዴራሉን ወይም የክልልን ሕገ መንግሥት ያፈረሰ፣ የለወጠ ወይም ያገደ እንደሆነ፣ ወይም

(ለ) በፌዴራሉ ወይም በክልል ሕገ መንግሥት የተቋቋመውን ሥርዓት ያፈረሰ ወይም የለወጠ እንደሆነ፣

ከሦስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

(2) ወንጀሉ ሲፈፀም በሕዝብ ደህንነት ወይም ኑሮ ላይ ከፍተኛ ቀውስ ደርሶ እንደሆነ፣ አድራጊው በዕድሜ ልክ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል፡፡

በአንቀጽ 238 (1)(ሀ) ላይ የተደነገገው ሕገ መንግስቱን (የፌዴራሉን ወይም የክልልን ሊሆን ይችላል) በማናቸውም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የማፍረስ፣ የመለወጥ ወይም አፈጻፀሙን የማገድ ተግባርን የሚመለከት ሲሆን በአንቀጽ 238 (1)(ለ) ላይ የተመለከተው ደግሞ ሕገ መንግስቱ (አሁንም የፌዴራል ወይም የክልል ሊሆን ይችላል) ያቋቋመውን ሥርዓት ወይም

መንግሥት የማፍረስ ወይም የመለወጥ ተግባርን የሚመለከት ነው። በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተው ደግሞ እንዲህ ዓይነት በሕገ መንግሥቱና በሕገ መንግሥቱ ሥርዓት ላይ የሚፈፀም የወንጀል ድርጊት በራሱ ከባድነት ያለውና የሚያስከትለውም ቅጣት እንዲሁ ከፍተኛ ቢሆንም የበለጠ ከባድ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን እና የእነዚህ ሁኔታዎች መገኘትም የሚያስከትለውን ቅጣት ከፍ በማድረግ በአብዛኛው በተለምዶ (normally) የመጨረሻ ከፍተኛ ተብሎ የሚወሰደውን የሞት ቅጣት ሊያስፈርድ እንደሚችል የሚደነግግ ነው።

ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 (1)(ሀ) ላይ የተመለከተው በማናቸውም ሕገ ወጥ መንገድ ሕገ መንግሥቱን (የፌዴራሉን ወይም የየትኛውንም ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ሊሆን ይችላል) ማፍረስን፣ መለወጥን ወይም ማገድን በሚመለከት ነው። በድንጋጌው መሠረት እንዲህ ዓይነት ተግባር በወንጀልነት የተፈረጀ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያስቀጣ ተግባር ነው።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ በግልፅ እንደሰፈረው የሕገ መንግሥቱ ባለቤቶች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ናቸው። የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 8 ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ሥለመሆናቸው፣ ሕገ መንግሥቱ ሉዓላዊነታቸው መገለጫ መሆኑን፣ እንዲሁም ይህ ሉዓላዊነታቸው የሚገለፀው በሕገ መንግሥቱ መሠረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት መሆኑን ይደነግጋል። ይህ መርህ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት ከሚመራባቸው መሠረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው።

ሥለዚህ ሕገ መንግሥቱን ማፍረስ፣ መለወጥ ወይም ማገድ የሚችሉት ሕገ መንግሥቱ ራሱ ያስቀመጠውን ሥርዓት ተከትለው የሕገ መንግሥቱ ባለቤቶች ራሳቸው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ወይም በሕገ መንግሥቱ መሠረት የመረጧቸው ተወካዮቻቸው ናቸው እንጅ ማንም እንዲህ ዓይነት መብት የለውም፣ ሊኖረውም አይችልም። በመሆኑም ሕገ ወጥ ድርጊት ነው። ሥለዚህ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 (1)(ሀ) እንዲህ ዓይነት ድርጊቶችን በወንጀልነት መፈረጁ ትክክል ነው ብቻ ሳይሆን የግድ አስፈላጊም ነው።

ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ ምን ዓይነት ተግባሮች ናቸው ሕገ መንግሥቱን ማፍረስ፣ መለወጥ ወይም ማገድ ተደርገው የሚወሰዱት የሚለው ነጥብ ነው። በግልፅ እንደሚታወቀው እንዲህ ዓይነት ድርጊቶችን ወይም ማናቸውንም የወንጀል ድርጊት ለመፈፀም አንድ ሰው ማሰቡ ብቻውን በራሱ በወንጀልነት አያስጠይቀውም። ማለተም ምንም እንኳን ድረጊት የሃሳብ ውጤት ቢሆንም ወንጀል ለመፈፀም ማስብ ብቻውን የወንጀል ኃላፊነት አያስከትልም። ወንጀል የመፈፀም ሀሳቡ በድርጊት እስካልተገለፀ ድረስ ቅጣትን አያስከትልም። ሕጉ በተግባር ያልተገለፀ ሀሳብን ሁሉ ያጠቃልላል ቢባል አፈጻፀሙ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ የወንጀል ሕግ ዓላማን አያሳካም። አንድ ሰው ምን እንደሚያስብ ማረጋገጥ አስቸጋሪ ከመሆኑም ባሻገር በሀሳብና በሀሳቡ ውጤት በሆነው በድርጊቱ መካከል ርቀት ያለ በመሆኑ ወንጀል ለመፈፀም ያሰበ ሁሉ ሀሳቡን በድረጊት ይገልጻል ተብሎ አይገመትም። ስለዚህም ከማሰብ ያለፈ ነገርን የወንጀል ሕግ በአጠቃላይ ይጠይቃል። የታሰበው ነገር ከሃሳብነት አልፎ ወደ ውጭ ወጥቶ በድርጊት (ቢያንስ በቃላት ደረጃ) ከአሰበው ሰው አልፎ መገለፅ አለበት።

በምን መንገድ ሲገለፅ ነው በወንጀልነት ተፈርጆ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት በወንጀል የሚያስጠይቀው የሚለውን በተመለከተ የወንጀል ሕጉ አመላካች ነገሮችን አስቀምጧል። ሕገ መንግሥቱን ለማፍረስ፣ ለመለወጥ ወይም ለማገድ የሚደረገው እንቅስቃሴ በኃይል፣ በዛቻ፣ በአድማ ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገ ወጥ የሆነ መንገድ ሊሆን እንደሚችል ተመልክቷል።

በመሆኑም የሕገ መንግሥቱን በእርግጥ መኖር ባለመቀበል ወይም መኖሩን ተቀብሎ ማናቸውንም ጉዳይ በምክንያትነት በመውሰድ ሕገ መንግሥቱ እንዳይኖር ለማድረግ ወይም በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ከተመለከተው ሕገ መንግሥታዊ ከሆነው መንገድ ውጭ ለመቀየር በመፈለግ ወይም የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ ተደናቅፎ (suspend ሆኖ) እንዲቆይ በመፈለግ ይህ ዓላማው እንዲሣካ ለማድረግ የኃይል ሥራን፣ ዛቻን፣ አድማን ወይም ማናቸውም ሌላ ይህን ሕገ መንግሥቱን የማፍረስ፣ የመለወጥ ወይም የማገድ ዓላማን ለማሳካት ተብሎ የሚወሰድ ተግባርን መፈፀም በድንጋጌው መሠረት በወንጀል ተጠያቂነትን ያስከለትላል።

ይህን ሕገ ወጥ ዓላማ ለማሳካት ተብሎ የሚፈፀመው ተግባር በድርጊት (by deeds) ወይም በቃላት (by words) ማለትም በንግግር ወይም በጽሑፍ ሊሆን ይችላል ወይም

በምልክት ወይም በሌላ መንገድ ህብረተሰቡ ወይም የህብረተሰቡ የተወሰነው ክፍል እንዲነሳሳ በማድረግ ሕገ መንግሥቱ እንዳይኖር ወይም ሕገ መንግሥቱ ካስቀመጠው መንገድ ውጭ እንዲቀየር ወይም አፈጻፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ የሚፈፀም ድርጊት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻርም መገናኛ ብዙኃን የሆኑትን እንደ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ሬድዮ እና የመሳሰሉትን በመሣሪያነት በመጠቀም ወይም በመገልገል ሊፈፀም ይችላል፡፡

በድርጊት (by deeds) ለምሳሌ ኃይልን በመጠቀም ወይም ዛቻና አድማን እንደ መሣሪያ በመገልገል ሕገ መንግሥቱ እንዲለወጥ የሚደረጉ ተግባሮች በባህሪያቸው የቀጥታ ዓላማቸውና አፈጻፀማቸው በግልፅ የሚታይና የሚታወቅ በመሆኑ ማለትም የወንጀልነት ባህሪያቸው ፊት ለፊት የሚታይ በመሆኑ በወንጀል የሚያስጠይቁ መሆናቸው የሚያከራክር ወይም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ ከእነዚህ ይልቅ የወንጀልነት ባህሪያቸው በግልፅ ለማንኛውም ወገን የማይታየው እናም ጥንቃቄ የሚጠይቁት ቃላትን (by words) በመሣሪያነት በመጠቀም የሚፈፀሙት ናቸው፡፡ እነዚህ በቃላት የሚፈፀሙት ድርጊቶች አንዳንድ ጊዜ ማንኛውም ሰው ካለው እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29 ከተረጋገጠለት በማንኛውም ጉዳይ ዙሪያ አመለካከትንና ሀሳብን በነጻ የመያዝ እና የመግለፅ መብት ጋር ሊቀላቀሉ ወይም ሊምታቱ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ስለዚህ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተተ ማናቸውንም ጉዳይ አንስቶ አስተያየት መስጠትን፣ በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ የህበረተሰቡ አስተሳሳብ በመቀየሩ ምክንያት ሊሆን ይችላል ይህን በሕገ መንግሥቱ የተካተተው ጉዳይ የህበረተሰቡን ፍላጎት አያንፀባርቅም ስለዚህም ይህ ድንጋጌ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል ይገባል ብሎ መከራከርን ራሱን የወንጀል ድርጊት አድርጎ የወንጀል ሕጉ አይፈርጀውም፡፡ እንዲህ ዓይነት ተግባሮች የወንጀል ድርጊት የሚሆኑት ተግባሮቹ የተፈፀሙት ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌውን ሕገ መንግሥታዊ ባልሆነ መንገድ (procedure) ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ዓላማ በማድረግ የተፈፀሙ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎቹ ዘለዓለማዊ ሆነው ሳይቀየሩ ወይም ሳይሻሻሉ እንዲኖሩ የማድረግ ግብ ሕገ መንግሥቱ ራሱም ሆነ የወንጀል ሕጉ የላቸውም፡፡

በወንጀል ጉዳይ አንዳንድ ጊዜ የድርጊቶች ውጤት በራሱ ወንጀል የሚሆንበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የድርጊቶቹ ውጤት በራሱ ሕገ ወጥ ባይሆንም ድርጊቶቹ የተፈፀሙበት መንገድ ሕገ ወጥ በመሆኑ (a legal act by illegal means እንደሚባለው ማለት ነው) ድርጊቶቹን ራሳቸውን በወንጀልነት እንዲፈረጁ ያደርጋቸዋል፡፡

ሕገ መንግሥትን ለመለወጥ መንቀሳቀስ በራሱ ሕገ ወጥ አይደለም፡፡ ሕገ መንግሥቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለመለወጥ መንቀሳቀስ ግን ሕገ ወጥ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ የተመለከተ ማንኛውም ድንጋጌ ለመለወጥ ሕጋዊው መንገድ በራሱ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተመለከተው ወይም የተካተተው መንገድ ነው፡፡ ሥለዚህ ሕጋዊው መንገድ ሕገ መንግሥታዊው መንገድ ነው ማለት ነው፡፡

ሌላው ከላይ ከተጠቀሰው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ አንጻር ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ ወንጀሉ ተፈፅሟል ለማለት ተሟልቶ መገኘት ያለበትን የሀሳብ ክፍል (moral or mental element) ወይም የድርጊት ፈጻሚውን mens rea የሚመለከት ነው፡፡ በሕጉ በግልፅ እንደሰፈረው አንድን ሰው የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 238 ድንጋጌን በመተላለፉ በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ድርጊቱን የፈፀመው አስቦ (intentionally) መሆን አለበት፡፡ በዚህም መሠረት ምንም እንኳን ከውጤት እንጻር ድርጊቱ ያስከተለው ጉዳት ተመሣሣይ ቢሆንም በግለሰቡ ድርጊቱ የተፈፀመው ተግባሩ ሕገ መንግሥቱን የማፍረስ፣ የመለወጥ ወይም የማገድ ውጤት ይኖረዋል ብሎ አስቦ ያደረገው ሳይሆን በቸልተኝነት የተፈፀመ ከሆነ የተጠቀሰውን የወንጀል ድንጋጌ እንደተላለፈ አይቆጠርም፡፡

ሌላው ምንም እንኳን በግልፅ የሚታወቅ ቢሆንም ምናልባት ሳይጠቀስ መታለፉ አግባብነት ስለማይኖረው ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ወንጀል ፈጻሚው ለማድረስ የፈለገው በህገ ወጥ መንገድ ሕገ መንግሥቱን የማፍረስ፣ የመለወጥ ወይም የማገድ ዓላማ ግብ ላይ ባይደርስም (ባይሳካም) ማለትም ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ ላይ ቢቀርም የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስቀር መሆኑ ነው፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት - <u>በሕገ መንግሥት በተቋቋመው ሥርዓት ላይ የሚፈፀም ወንጀል</u>

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 238 (1)(ለ) ላይ እንደተደነገገው በሕገ መንግሥቱን (በፌዴራሉ ወይም በየትኛውንም ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ሊሆን ይችላል) የተቋቋመውን ሥርዓት በማናቸውም ሕገ ወጥ መንገድ ማፍረስ ወይም መለወጥ በወንጀል ያስጠይቃል፡፡

ከዚህ በላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት ከሚመራባቸው መሠረታዊ መርሆዎች አንዱ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ስለመሆናቸው፣ ሕገ መንግሥቱ ሉዓላዊነታቸው መገለጫ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ይህ ሉዓላዊነታቸው የሚገለፀው በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው ወይም በራሳቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት መሆኑ ነው፡፡ ሥለዚህ ማንኛውም አካል በመንግሥትነት ማስተዳደርና መምራት የሚችለው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሉዓላዊነት መገለጫ ከሆነው ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት ሥልጣኑ የሚመነጭ ወይም የሚቀዳ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተቋቋመ ሥርዓት ወይም መንግሥት የሚፈርሰው ወይም የሚለወጠው የሥልጣኑ ምንጭ በሆነው በሕገ መንግሥቱ መሠረት በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውሳኔ ወይም ምርጫ ነው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ የሚቋቋመውና ህልውናው የሚቀጥለው በእነዚህ ወገኖች ይሁንታ እና አመኔታ መቀጠል እንደሆነ ሁሉ የሚቀየረው ወይም የሚፈርሰውም እነዚህ ወገኖች ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ አሌላ እንዲለወጥ በሚሰጡት ውሳኔ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሚደረግ ማናቸውም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን የማፍረስ ወይም የመቀየር ተግባር ሕገ ወጥ ነው፡፡ ሕገ ወጥ ብቻ ሳይሆን በወንጀልነት ተፈርጆ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 (1)(ለ) መሠረት የሚያሥጠይቅ ተግባር ነው፡፡

የሥልጣኑ ምንጭ የሆኑት ወገኖች አመኔታ አጥተውበት እስካልቀየሩት ድረስ በሕግ መሠረት የተቋቋመ መንግሥት (ሥርዓት) ማስተዳደሩን ወይም መምራን መቀጠል ይገባዋል፤ ይህ ሁኔታ ካልተፈጠረ በሕግ የተቋቋመው ሥርዓት ብቻ ሳይሆን አገሪቱ ራሷ (the state itself) እንደ አገር መቀጠሏ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአንድ መጽሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው፡-

Government established by law is the visible symbol of the state. The very existence of the state will be in jeopardy if the

government established by law is subverted. Hence, the continued existence of the government established by law is an essential condition of the stability of the state.

በመሆኑም የተረጋጋ አስተዳደር እንዲኖር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሉዓላዊነትና ፍላጎት መገለጫ በሆነው በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተቋቋመው ሥርዓት መፍረስ ወይም መለወጥ የሥልጣኑ ምንጭ በሆነው በሕገ መንግሥቱና በእነዚህ ወገኖች ፍላጎት የሚጸረር ተግባር ነው።

ምን ዓይነት ድርጊቶች ናቸው ይህን ወንጀል የሚያቋቋሙት የሚለውን ስንመለከት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 ስር እንደተመለከተው ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ ወይም ለመለወጥ በማሰብ የሚፈፀሙ የኃይል፣ የዛቻ፣ የአድማ ወይም ማናቸውም ሕገ ወጥ ተግባር በድንጋጌው ስር ይወድቃል። በመሆኑም በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተቋቋመውን መንግሥት በመንግሥትነት ባለመቀጠር (recognize ባለማድረግ) ወይም ይህ መንግስት፣ የመንግስት አካላቱ ወይም ባለሥልጣናቱ የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች በማጣጣል ህብረተሰቡ ወይም የህብረተሰቡ የተወሰነው ክፍል መንግስት የለም ብሎ እንዲያምንና በዚሁ እምነቱ መሠረት እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ ወይም መንግሥት መኖሩን ተቀብሎ ውሳኔዎቹን ግን ሕጋዊ ወይም ተቀባይነት የላቸውም ብሎ ከውሳኔው እንዲያፈነግጥ ወይም መንግሥት፣ አካላቱ ወይም ባላሥልጣናቱ በሚሰጡት ውሳኔ መሠረት እንዳይተዳደር ወይም እንዳይመራ የሚደረግ ማናቸውም ድርጊት በወንጀልነት ያስተይቃል።

ሕገ ወጥ ተግባሩ በድርጊት (by deeds) ወይም በቃላት (by words) ሊገለጽ የሚችል ሲሆን ዓላማ ያደረገው በሕገ ወጥ መንገድ በሕግ መሠረት የተቋቋመውን መንግሥት ማፍረስን ወይም መለወጥን ሊሆን ይገባል።

እዚህ ላይ አሁንም ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ በመንግሥት ወይም በአስተዳደር አካላቱ ወይም ባለሥልጣናቱ አማካኝነት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ወይም ሌሎች ውሳኔዎችን ትክክል አይደሉም ወይም አግባብነት የላቸውም በሚል አስተያየት መስጠት ወይም መተቸት ብቻውን በራሱ የተከለከለ ተግባር አይደለም፤ የወንጀል ድርጊት ተደርጎም አይቆጠርም። እንዲህ ዓይነት

ተግባሮች የወንጀልነት ባህሪ የሚኖራቸው ድርጊቶቹ የተፈፀሙት በህብረሰተቡ ውስጥ ጥላቻን (hatred or enmity) በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ ለመፍጠር ወይም ህብረተሰቡ መንግስትን ዝቅ አድርጎ (with contempt) እንዲመለከተው በማድረግ በሕገ ወጥ መንገድ ይህ በሕግ መሠረት የተቋቋመ መንግሥት እንዲፈርስ ወይም እንዲለወጥ የማድረግ ዓላማን በመያዝ ድርጊቶቹ የተፈፀሙ ሲሆን ነው።

ሆኖም እነዚህ ድርጊቶች የተፈፀሙት መንግሥት ወይም አካላቱ ወይም ባለሥልጣናቱ የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ወይም የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች በሕጋዊ መንገድ በትክክል ህብረተሰቡ በሚፈልገው ዓይነት እንዲያደርግ ለማረም በማሰብ (with a view to obtain their alteration by lawful means) ወይም ይህን ለማድረግ ህብረተሰቡ ሕገ መንግስታዊ መንገድን ተከትሎ ያለውን መንግሥት በሌላ መንግሥት እንዲተካው ለማድረግ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች በወንጀልነት ያልተፈረጁ እናም የማያስቀጡ ድርጊቶች ናቸው።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ሕገ መንግሥቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የጋራ ጥቅማቸውን፣ መብታቸውንና ነጻነታቸውን በጋራና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ እና አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመገንባት ያስችላቸው ዘንድ ያፀደቁት የቃል ኪዳን ሰነድ ነው። የዚህ ሕገ መንግሥትም ሆነ የማናቸውም ሕገ መንግሥት አንደኛው መለያ ባህሪ የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ (supreme) መሆን ሲሆን ከዚህ መለያ ባህሪ የሚመነጨው ሌላው የሕገ መንግሥቱ መገለጫው (feature) ደግሞ ማናቸውም የመንግሥት ሥልጣን የሚመነጨው ወይም የሚቀዳው ከዚሁ ከሕገ መንግሥቱ እና ሕገ መንግሥቱ ውስጥ በተመለከተው መንገድ ብቻ መሆኑ ነው።

ከወንጀል አንጻር የእነዚህ የሕገ መንግሥቱ መገለጫ የሆኑትን ባህሪያት ውጤት ተደርጎ የሚወሰደው አንደኛው ጉዳይ ደግሞ ሕገ መንግሥቱን ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ፣ ለመለወጥ ወይም ለማገድ የሚፈፀም ማናቸውም ድርጊት በወንጀልነት የሚያስጠይቅ ተግባር ነው። የወንጀል ድርጊቱ እንደተፈፀመ የሚቆጠረው ደግሞ ሕገ መንግሥቱን ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመለወጥ የተደረገው ተግባር የተፈፀመው በሕገ መንግስቱ ከተቀመጠውና ከተፈቀደው ውጭ የተፈፀመ እንደሆነ ነው። በሕገ መንግሥቱ

የተመለከተውንና የተፈቀደውን መንገድ ተከትሎ የሚፈፀም ተግባር የመጨረሻ ውጤቱ ሕገ መንግሥቱን መለወጥን ዓላማ ያደረገ ቢሆን እንኳን በወንጀልነት የሚፈረጅና የሚያስጠይቅ አይሆንም።

የሕገ መንግሥቱን የበላይነትና ተፈጻሚነት ማረጋገጥ የማናቸውም ዜጋ ኃላፊነት ቢሆንም የፍትሕ አካላት በተለይም ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ እና ዳኞች ደግሞ ድርብ የሆነ ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ አንጻር በሕገ መንግሥቱ ወይም በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ምንነት በአግባቡ ተገንዝቦ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ማንኛውም በተለይም የግል አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልግ ክስ ሊቀርብባቸው የሚችሉት የወንጀል ዓይነቶች በቀጥታ ፊት ለፊት የሚታይ ተጠቂ (victim) ቢኖራቸው እንኳን በሕዝብና በመንግሥት ላይ እንደተፈፀሙ ተደርጎ ይወሰዳል። በሌላ በኩል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 በሕገ መንግሥቱና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በማለት የተወሰኑ ድርጊቶችን ለይቶ በማውጣት በወንጀልነት ፈርጆ አስቀምጧል። ይህ ሁኔታ ማንኛውም ወንጀል በመንግሥት መብትና ጥቅም ላይ እንደተፈፀመ ከሚቆጠርበት ሁኔታ አንጻር እንዴት ይታያል?
2. በአንድ ክልል ሕገ መንግሥት ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት የሚፈፀም ወንጀል በአጠቃላይ በአገሪቱ ሕገ መንግሥት ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ እንደተፈፀመ ወንጀል ይቆጠራል ወይ? እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የፌዴራል ወይስ የክልል ፍ/ቤት ነው?
3. "ሀ" የተባለው ቡድን በዋናነት በግል ንብረት ባለቤትነት ላይ የተመሰረተውን (ካፒታሊዝም ተብሎ የሚጠራውን) ሥርዓት በመገርሰስ ንብረት በጋራ የሚያዝበትን ሥርዓት ለመመስረት፣ እንዲሁም የአንድ ፓርቲ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግን በዓላማነት በመያዝ ይንቀሳቀሳል። ለዚህም ህ/ሰቡን የግል ንብረት ባለቤትነት መጥፎ ጎኖችን በማንሳት በማስተማር ህብረተሰቡ ቡድኑን እንዲመርጥና የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ለማስገባት ይንቀሳቀሳል። የዚህ ቡድን እንቅስቃሴ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 238 ድንጋጌዎች አንጻር እንዴት ይታያል?

ክፍል ሁለት - <u>የሙስና ወንጀል፣</u>

በመዝ በ ቃላፔ በተለቨብ ኮሀዐ ኖ ባተሰን፡ ፔር ሞኖ እንደሚያስረዱት ሙስና ሥልኃትት ለ ል ኀ ቅም ማ ቾ፣ ተ ቢ ባልሆት መት ታ መን ቀም፣ ለራስ ወቨም ለቡታት ተ ቢ ቨልሆት ኀ ቅም ለማ ገቼ ሲባል በ ልኮ ባተተት ፡ ሕ ኖናት ወቨም በአን ቃላቨ ተቀባቨቸፔ ቨላ ውት ልም ኖ (norms) መመሪቨዎኖ፣ ሥነሥርዓ ኖ መርሆዎኖት ባሚቃረት በማትቾ ውም ባመት ሥፔ ባለሥልኃት ወቨም ሠራተቾ ወቨም ለሰብ (Private individual) ወቨም ቡታት ባሚወ ም ታር ፔ ሲሆት ተ ባሩም በማታረ (by commission) ወቨም ባለማታረ (by omission) ሊወ ም ቨኖላል::

በሕግ መ፡ያ ዙሪያ የምንጠቀምባቸውን ቃላት እና ሀረጎች ወይም ፅንሰ ሀሳቦች ለመተርጎም ብዙ ጊዜ የምንጠቀምበት ብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት ሙስና /corruption/ የሚለውን ቃል እንደሚከተለው ተርጉሞታል

> corruption is “the act of doing something with an intent to give some advantage inconsistent with official duty and the rights of others; a fiduciary’s or official’s use of a station or office to procure some benefit either personally or for someone else, contrary to the rights of others.”

በግርድፉ ወደ አማርኛ ሲመለስም ሙስና ጥቅም በመፈለግ ከሥልጣን ኃላፊነት ውጭ በሆነ ሁኔታ አንዱን ለመጥቀምና የሌላውን መብት ለመጉዳት የሚደረግ ተግባር፣ ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ሲባል የያዘውን ሥልጣንና ኃላፊነት ሕገ ወጥና ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ የመጠቀም ወይም ከሥራ ኃላፊነት ውጭ በመሥራት የሌሎች ሰዎችን መብት መንካት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በተሻረው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ለሙስና ወንጀል ቀጥሎ በተመለከተው መልኩ ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

“የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግሥት ወይም ከሕዝብ አገልግሎት ወይም ከሕዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈፀም ማናቸውም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግሥት ወይም የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ወይም ለቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላውን ሰው መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣ በሥልጣን መነገድን፣ በሥልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግሥት ሥራን ወይም የሕዝብ አገልግሎት ሥራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በሥራ ተግባር ላይ የሚፈፀም መውሰድና መሠወርን፣ በመንግሥት ሥራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን እና ምስጢር ማባከንን እና የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮችን ይጨምራል፡፡”

የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 “የሙስና ወንጀል “ ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች ናቸው በማለት በአዋጁ ውስጥ ትርጓሜዎችን ባስቀመጠው አንቀጽ ስር የደነገገ ሲሆን በወንጀል ሕጉ ውስጥ የሙስና ወንጀል ምን ማለት እንደሆነ በቀጥታ በመተርጎም ደረጃ የተቀመጠበት ቦታ የለም፡፡ የሙስና ወንጀል ምን ምን ዓይነት ድርጊቶችን እንደሚያካትት ግን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 404 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር እንደሚከተለው ተመልክቷል፡-

- “ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባው እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ፣ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የሕዝብ አደራ ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤” ወይም
- “ማንኛውም ሰው ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፣ ለመንግሥት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ፣ ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ፣” ወይም

- “በአግባቡ ለተፈፀመ ወይም በአግባቡ ለወደፊቱ ለሚፈፀም የመንግሥት ሥራ የማይገባ ጥቅምን ማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የተቀበለ እንደሆነ፤

በዚህ ርዕስ የተመለከቱትን የሙስና ወንጀሎች አድርጓል ተብሎ”.... ይቀጣል፡፡

በዚህም መሠረት አዋጅ ቁጥር 236//93ትን በሻረው አዋጅ ቁጥር 434/97ትም ሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ ላይ የሙስና ወንጀል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ቀጥተኛ ትርጉም ባያስቀምጡም የወንጀል ሕጉ የሙስና ወንጀሎች ተብለው የሚቆጠሩትን ድርጊቶች አጠቃላይ ባህሪና የወንጀል ዓይነቶችን ግን አስቀምጧል፡፡ በሕጉ ልዩ ክፍል የተመለከቱትን እነዚህን ወንጀል የሚያቋቁሙ ድንጋጌዎች በመተላለፍ አንድ ሰው የወንጀል ድርጊት ከፈፀመ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የሚወሰድ ሲሆን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶችን ለመመርመር እና/ወይም ለመክሰስ ሥልጣን ያለው አካልም (በፌዴራል ደረጃ ከሆነ) በተሻሻለው የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በመርህ ደረጃ የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በኢትዮጵያ ሕግ የሙስና ወንጀሎች ናቸው ተብለው የተወሰዱት የወንጀል ድርጊቶች በወንጀል ሕጉ በዋናነት በአንድ ተጠቃለው የሚገኙ ሲሆን በወንጀል ሕጉ ከአንቀጽ 407 እስከ አንቀጽ 419 እንዲሁም ከአንቀጽ 427 እስከ 431 ያሉትን ድንጋጌዎችን ያካትታል፡፡ ከነዚህም የሙስና ወንጀሎች ውስጥ በሥልጣን ያለ አግባብ መገልገል፣ በሌለው ሥልጣን መጠቀም፣ ጉቦ መቀበል እና መስጠት፣ የማይገባ ጥቅም መቀበል፣ ማቀባበል፣ የመንግሥት ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት፣ አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ፣ በሥራ ተግባር ላይ የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል፣ በሥልጣን መነገድ፣ በሕገወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ፣ ያለ አግባብ ጉዳይን ማጓተት፣ ዋጋ ያለውን ነገር ያለ ክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት፣ ያለ አግባብ ፈቃድ መስጠት እና ማፅደቅ፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በእጁ ይዞ መገኘት ወይም ኑሮውን በዚሁ ዓይነት ባልታወቀ ገቢ መምራት፣ በግል ተሰሚነት መነገድ ይገኙበታል፡፡ ነገር ግን ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የወንጀል ድንጋጌዎች በተጨማሪ የሙስና ወንጀሎች ሌሎች ወንጀሎችን ሊያጠቃልል እንደሚችል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 404 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ተመልክቷል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዓይነቶች የሙስና ወንጀሎች ሊፈፀሙ የሚችሉት በመንግሥት ሠራተኞች አማካኝነት ሲሆን "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት ደግሞ በመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም በመንግሥት ልማት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተሹሞ፣ ተመድቦ፣ ወይም በሕዝብ ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናውን ማንኛውንም ሰው የሚመለከት ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 402(2) ላይ ተመልክቷል።

በመሆኑም በመርህ ደረጃ የሙስና ወንጀሎች የሚመለከቷቸው የመንግሥት ሠራተኞችን ነው። ነገር ግን ስለ ወንጀሎችና ወንጀል አድራጊዎች በማስመልከት በሚደነግገው በወንጀል ሕጉ ጠቅላላው ክፍል ውስጥ አንቀጽ 33 ላይ እንደተመለከተው አንዳንድ ወንጀሎች በጠባያቸው የተነሳ በሁሉም ሰዎች የማይፈፀሙ ዓይነት ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ቢሆንም እንዲሁም አንድ ሰው እነዚህን የተለዩ ጠባይ ያላቸውን ወንጀሎች ለመፈፀም የሚያስችለው ሁኔታ ባይኖረውም በመላ አሳቡና ድርጊቱ እነዚህን ወንጀሎች ለመፈፀም የተለዬ ሁኔታ ካላቸው ሰው ጋር ከተባበረ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተጠያቂ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የመንግሥት ሠራተኛ ያልሆነ ሰውም በእነዚህ ወንጀሎች ውስጥ ተካፋይ ከሆነ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት ይኖራል ማለት ነው።

ከሙስና ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ሌላው ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ነጥብ ማንም ሰው በሙስና ወንጀል ተካፋይ ከሆነ በኋላ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ድርጊትና ስለተካፋዮች ሚና ጠቃሚ መረጃ ከሰጠ ከክስ ነጻ ሊሆን እንዲችል የወንጀል ሕጉ የፈቀደ መሆኑ ነው (አንቀጽ 406)። በተመሳሳይም የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 43 ላይ በሙስና ወንጀል ተሳታፊ የሆነ ሰው ከክስ ነጻ ስለሚደረግበት ሁኔታ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ላይ እንደተመለከተው እንዲህ ዓይነት ከክስ ነጻ የማድረግ ውሳኔ የሚሰጠው በፌዴራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይም አግባብ ባለው አካል የበላይ ኃላፊ አማካኝነት ነው።

እንዲህ ዓይነት አሰራር ለምን ተፈቀደ የሚለውን በምናይበት ጊዜ በመሰረቱ ሙስና በባህሪው (በተለይም ግራንድ ኮራብሽን የሚባለው) በትምህርትና በሙያ የተለዬ ችሎታና ዕውቀት ባላቸው፣ መንግሥታዊ ሥልጣን በያዙ፣ በሥልጣናቸው ተፅዕኖ ሊያደርጉ በሚችሉ

ሰዎች የሚፈፀም ድብቅ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ወንጀል ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ራሳቸው ማስረጃ እንዲሰጡ በማድረግ ሌሎችን ተጠያቂ ከማድረግ ውጭ አንዳንድ ጊዜ ምንም ዓይነት ማስረጃ ማግኘት አይቻልም ወይም ቢያንስ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም ተጨባጭ የሆኑ ለጉዳዩ ጠቀሜታ ያላቸው ማስረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎችን ከክስ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስና በፈፀሙ ሌሎች ሰዎች ላይ ተገቢው ቅጣት እንዲጣል ማድረግ ጠቀሜታው የሰፋ ነው፡፡ ስለዚህም በተፈፀመው ሙስና የሚጠየቅ ሳይኖር ከሚቀር አንድ ሰው ነጻ ተደርጎ እርሱ በሚሰጠው ጠቃሚ መረጃ በመንተራስ ሌሎች እንዲጠየቁ ማድረግ የተሻለ ነው ተብሎ በሕጋችን ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ይመስላል፡፡

<u>ባመወሸሸ ጎ ሸቄዎኖ</u>

1. የሙስ ወት ልን ከሌሎች ወንጀሎች ለየት የሚያደርጉት ባህሪያት ምን ምን እንደሆኑ ተወያዩበት፡፡

2. በተሻሻለው የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 9 ባሙስ ወት ል ጸባታ ቀላል ተብሎ በሁለፔ ተጸዎሏል፡፡ ከባታ ባሙስ ወት ል ማለት ጸዎተቾ ስፔራ ፣ሸዊ ጎ ቀሜ ባላ ው ባመት ሥፔ መ/ቤ ኖ ባመት ሥፔ ባልማፔ ታር ኖ ላቭ ባሚወኸሙ ከዎተቾ ባ ትዘብ መጎ ትት ሸካተቱ ወቭም ባመት ሥፔ ባለሥልታ ትት ባሚመለጸቱ ወቭም በአ ር ሉዓላዊትፔ፣ ኢኮ ሚ፣ ኸነ ት ፣ሁም በሕብረተሰቡ ትሮ ላቭ ጸዎተቾ ጎ ፔ ባሚሸተርሱ ወቭም ሊሸተርሱ ባሚኖሱ ባሙስ ወት ሎኖ ትዘየት ተተር ሞ ተተር ጎሚል፡፡ ከዚህ ፔር ጎም አትኹ ጸዎተቾ ስፔራ ፣ካዊ ጎ ቀሜ ሸላ ው ባመት ሥፔ መ/ቤ ኖ ባመት ሥፔ ባልማፔ ታር ኖ ባፔኣ ቷ ው? ከዎተቾ ባ ትዘብ መጎ ት ማለፔስ ስከ ስትፔ ታረስ ሸለ ችው?

3. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (money laundering) በእራሱ በወንጀልነት እንደሚፈረጅ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 404(4) እና

ከአንቀጽ 684 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (money laundering) እራሱን የቻለ ወንጀል ነው? የድንጋጌዎቹን አግባብነት እና እንድምታ ተወያዩበት።

ክፍል ሦስት - <u>የዘር ማጥፋት ወንጀል</u>

የዘር ማጥፋት ወንጀል በሰው ልጆች ከሚፈጸሙ ወንጀሎች ጋር ያለው ግንኙነት እና ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

የዘር ማጥፋት ወንጀል በሰው ልጆች ላይ ከሚፈፀሙት ወንጀሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ጥሬ ቃሉ ሲተረጎምም ሰዎችን በጅምላ መግደል (ማጥፋት) ነው። ሆኖም የጅምላ ማጥፋት ተግባር መሠረታዊ የሆኑ መለያ ባህሪያት አሉት።

የሰው ዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቅጣት በ1948 እ.ኤ.አ በተባበሩት መንግሥታት ተቀባይነት ያገኘው ዓለም ዓቀፍ ስምምነት (Convention to Prevent and Punish the Crime of Genocide) አንቀጽ 2 Genocide የሚለውን ቃል በሚከተለው መልኩ ይተረጉመዋል፤

"… genocide means any of the following acts committed with intent to destroy, in whole or in part, a national, ethnical, racial or religious group, as such (a) killing member of the group; (b) causing serious bodily or mental harm to members of the group; (c) deliberately inflicting on the group conditions of life calculated to bring about its physical destruction in whole or in part; (d) imposing measures intended to prevent births within the group; (e) forcibly transferring children of the group to another group."

ወደ አማርኛ በግርድፉ ሲመለስም ዘርን ማጥፋት ማለት በሚከተሉት ድርጊቶች አማካኝነት ሆን ብሎ በከፊልም ሆነ በሙሉ የአንድን ብሔር፣ ብሔረሰብ (ጎሣ)፣ ዘር ወይም የሐይማኖት

ቡድን ለማጥፋት የሚፈፀም ተግባር ነው፤ (ሀ) የዚያን ወገን አባላት መግደል፤ (ለ) በዚያ ወገን አባላት ላይ ከፍተኛ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ማድረስ፤ (ሐ) በከፊልም ሆነ በሙሉ የዚያን ወገን ህልውና የሚደመስስ አስከፊ ኑሮ ሆን ብሎ መጫን፤ (መ) የዚያን ወገን አባላት እንዳይዋለዱ የሚያደርጉ እርምጃዎችን መውሰድ፣ (ሠ) ከዚያ ወገን የተወለዱ ህጻናትን በኃይል አስገድዶ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ናቸው።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 269 ላይ ደግሞ ስለ ዘር የማጥፋት ወንጀል በሚከተለው መልክ ተመልክቷል፤

“ ማንም ሰው በሠላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጐሣ፣ በዘር፣ በዜግነት፣ በቀለም፣ በሃይማኖት ወይም በፖለቲካ አንድ የሆነን ቡድን በመላ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የጥፋቱን ድርጊት በማደራጀት፣ ትዕዛዝ በመስጠት ወይም ድርጊቱን በመፈፀም፡-

ሀ. በማናቸውም ሁኔታ የማጎበረሰቡን አባላት የገደለ፣ አካላዊ ወይም ሕሊናዊ ጤንነት የጐዳ፣ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤ ወይም

ለ. የማጎበረሰብቡ አባላት በዘር እንዳይራቡ ወይም በሕይወት እንዳይኖሩ ለማድረግ ማናቸውንም ዘዴ በሥራ ላይ ያዋለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ. በማህበረሰቡን አባላት ወይም ሕፃናት በግዴታ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ያዛወረ ወይም የበተነ ወይም ሊሞቱ ወይም ሊጠፉ በሚችሉበት የኑሮ ሁኔታ እንዲኖሩ ያደረገ እንደሆነ፤

ከአመስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት፤ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እሰራት ወይም በሞት ይቀጣል።”

ከዚህ በላይ ከተሰጡት ትርጉሞች ለመረዳት እንደሚቻለው፤

- የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈፀመ ለማለት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድርጊቶች የተፈፀሙት አንድን ቡድን በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ መሆን አለበት። ስለዚህም ድርጊቱ ሳይሆን ውጤቱ ታስቦ የተፈፀመ መሆኑ ወንጀሉ መፈፀሙን ለማረጋገጥ አንደኛው መሠረታዊ ነጥብ ነው ማለት ነው።

- የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈፀመ ለማለት ማናቸውም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድርጊቶች የተፈፀሙት አንድን ቡድን በጅምላ ለማጥፋት በመፈለግ የተቃጣ መሆን

አለበት፤ የተጠቀሱት ቡድኖች (ወገኖች) አባል የሆኑ አንድ ወይም ሁለት ግለሰቦች ለማጥፋት በማሰብ የተፈጸመ ድርጊት የዘር ማጥፋት ወንጀል ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። ማለትም ድርጊቱን የዘር ማጥፋት ነው ለማለት የተፈፀመበት አሳብ አንድን ቡድን በሙሉ ወይም በከፊል የማጥፋት ዓላማን መሠረት ባደረገ ሁኔታ መሆን አለበት።

- እንዲጠፋ የተፈለገው ቡድን በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በዘር፣ ወይም በሀይማኖት የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ ነጥብ አንጻር የኢትዮጵያን ሕግ ስንመለከት ሌሎች ቡድኖችንም አካትቶ እናገኘዋለን። ለምሳሌ በፖለቲካ አስተሳሰብ የተቆራኘ ቡድንን በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የሚፈፀም ተግባር የዘር ማጥፋት ወንጀል ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ላይ ግን ይህ ጉዳይ በትርጉሙ ውስጥ ተካትቶ አናገኘውም።

- የዘር ማጥፋት ወንጀል ሆን ብሎ አንድን ድርጊት ከማድርግ በመቆጠብ (by omission) የሚፈፀም ድርጊትንም ይጨምራል። ከዚህ አንጻር ለምሳሌ አንድ ቡድን በርሀብ ወይም በተላላፊ በሽታ ተጠቅቶ እያለ ሆን ብሎ በዚሁ ተጋላጭነቱ ቀጥሎ ቡድኑ እንዲጠፋ ማድረግ በወንጀሉ ተጠያቂነትን ያስከትላል ማለት ነው።

- የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አስገድዶ የአንድን ቡድን አባላትን ወደ ሌላ ቦታ ማዛወርን በተመለከተ በህጻናት ሲፈፀም ብቻ ሳይሆን በማናቸውም የቡድኑ አባላት ላይ ሲፈፀም የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሆነ አድርጎ ይወስደዋ። ከዚህ አንጻርም ለዘር ማጥፋት ወንጀል የሰጠው ትርጓሜ ሰፋ ያለ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል።

ሌላው መነሳት ያለበት ነጥብ የዘር ማጥፋት ወንጀል በይርጋ ቀሪ የማይሆን መሆኑ ነው። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ላይ እንደተመለከተው የሰው ዘር ማጥፋት ወንጀል በይርጋ አይታገድም፤የተጣለው ቅጣትም በምህረት ወይም በይቅርታ ቀሪ ሊሆን አይችልም። የሞት ፍርድ ከሆነ ብቻ በይቅርታ ወደ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሊቀየር ይችላል።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የሰው ዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቅጣት በወጣው ዓለም ዓቀፍ ስምምነት (ብዙ ጊዜ በአጭሩ Genocide Convention ተብሎ ይጠቀሳል) መሠረት በፖለቲካ አስተሳሰብ ምክንያት የተቆራኘን ቡድን በከፊል ወይ በሙሉ ለማጥፋት መንቀሳቀስ በዘር ማጥፋት ወንጀልነት አልተፈረጀም። ይህ ለምን ይመስላችኋል? ኢትዮጵያ የዚህ ስምምነት አንዲ ፈራሚ አገር ሆና እያለች የተለዩ ሕግ ማውጣቷ የሚኖረው እንድምታ ምንድን ነው?
2. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የGenocide Convention ድርጊቶችን በዘር ማጥፋት ወንጀልነት የሚፈርጅ ቢሆንም የሚያስከትለውን ቅጣት አያስቀምጥም፤ ከዚህ አንጻር የስምምነቱን ፋይዳ መርምሩ።
3. የዘር ማጥፋት ወንጀልን የማነሳሳት ወይም የማሰናዳት ተግባር በራሱ ወንጀሉ ባይሞከርም እንኳን በወንጀል ያስጠይቃሉ? ካላስጠየቀ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር የወንጀል ሕጋችንን አቋም እንዴት ያዩታል?
4. ለዘር ማጥፋት ወንጀል በይርጋ ቀሪ መሆን ተፈጻሚነት የተባለበት ምክንያት ለምን ይመስላችኋል? የይርጋ ሕግን መደንገግ ካስፈለገበት ምክንያት ጋር አይጋጭም ወይ?

ክፍል አራት - <u>የአሸባሪነት ወንጀል፣</u>

ሽብርተኝነት በእንግሊዝኛው terrorism የሚለውን ቃል የሚተካ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን terrorism ደግሞ terrere ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ነው፤ በጥሬው ወይም በግርድፉ ሲተረጎምም ማስፈራራት (to frighten) ማለት ነው።

ብላክስ ሎው ባሕ መዝ በ ቃላፔ ሽብርተፖቼት ባ ቭል ኅ ቃፔት በመኅ ቀም ሽብርት ዎርሃፔት መዎነ ር ወቭም በተለቭም በዠለቲካ አመራር ላቭ ተኮ ዕ ማሳተር በሚል ቭተረ ሙመዋል፡፡ ክሊቭ ዎጾር ባተባሉ ፀኃፊ ደግሞ the prevention of terrorizm in Biritsh law በሚለው መኮ ሀዌ ው ውስኅ ሽብርተፖቼ ማለፔ ለዠለቲካ ብ ሲባል ሀቭል መኅ ቀም ሲሆት ሕብረተሰቡት ወቭም ማትቾውትም ባሕብረተሰብ ክዎል ለማስወራራፔ ሀቭል መኅ ቀምት ቭካፔ ል በሚል ል ው ል፡፡

በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ወጥ የሆነ ለሽብርተኝነት እና ሽብርተተኛ ማነው ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ በትርጉሙ ላይ ስላለው ልዩነት ለማሳየት አንዳንዶች በሚከተለው መልኩ ይገልፁታል “one man’s terrorist is another man’s freedom fighter”- ለአንደኛው አሸባሪ ለሌላኛው የነጻነት ታጋይ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል እስካሁን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ስለ ሽብርተኝነት ወንጀል ስምምነት መፈራረም አስቸጋሪ የሆነው፡፡

ወደ አገራችን ስንመለስ እስከ ቅርብ ጊዜ ሽብርተኝነትን የሚመለከቱ ድርጊቶች ለማየት የሚያስችሉ የወንጀል ድንጋጌዎች ቢኖሩም የወንጀል ሕጋችን ግን ቃሉን በቀጥታ አይጠቀምበትም ነበር፡፡ አሁን ግን ከ------ ጀምሮ ሥራ ላይ በዋለው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3 ላይ የሽብርተኝነት ድርጊቶች ተብለው የሚወሰዱት ምን ዓይነት ድርጊቶች እንደሆኑ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር፣ ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት ወይም የሃገሪቱን መሠረታዊ ፖለቲካዊ፣ ሕገ መንግሥታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፍረስ፡-

(1) ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤
(2) የህበረተሰቡን ወይም የህበረተሰቡን ክፍል ደህንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤
(3) እገታ ወይም ጠለፋ የፈፀመ እንደሆነ፤
(4) በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤
(5) በተፈጥሮ ሀብት፣ በአካባቢ፣ በታሪካዊ ወይም የባህል ቅርስ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

(6) ማናቸውም የሕዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆነ፣ ወይም

(7) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6 ከተመለከቱት ድርጊቶች መካከል ማናቸውንም ለመፈፀም የዛተ እንደሆነ፤ ከ15 ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ በሚደርስ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል።

ከዚህ በላይ ከተመለከተው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው፡-

- የሽብርተኝነት ድርጊት በግለሰብ ወይም በቡድን ደረጃ ሊፈፀም ይችላል።
- ግለሰቡ ወይም ቡድን የፈጸማቸውን ድርጊቶች በሽብርተኝነት ለመፈረጅ የተፈፀመበት ዓላማ ግምት ውስጥ መግባት አለበት - ምንም እንኳን ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድርጊቶች የተለያዩ ዓላማዎችን ለማሳካት ሊፈፀሙ የሚችሉ ቢሆንም ሽብርተኝነት ነው ለማለት ድርጊቶቹ የተፈፀሙት በተዕዕኖ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ መሆን ይኖርበታል።
- ድርጊቶቹን መፈፀም ብቻ ሳይሆን እፈጽማለሁ በማለት መዛትም በሽብርተኝነት ወንጀል ውስጥ ይካተታል።
- በእርግጥ ድርጊቶችን በመፈፀም ወይም በማዛት የተፈለገው ተዕዕኖ የማድረግ ሁኔታ ባይሳካም ተዕዕኖ ለማድረግ መሞከሩ በወንጀሉ ተጠያቂነትን ያስከትላል።
- ድርጊቶቹ በዋናነት መገለጫቸው የመንግሥትን የፖሊሲ አቅጣጫ፣ አሠራር ለማስቀየር ወይም የህብረተሰቡ የተለመደ መሠረታዊ የሆነ አካሄድ በዚያው መልኩ እንዳይቀጥል ወይም እንዲዛባ ለማድረግ ኃይል መጠቀም ወይም ኃይል ለመጠቀም መዛት ነው፤ ኃይል የመጠቀሙ ወይም የዛቻው የቅርብ ዓላማም (immediate objective) የሥነ ልቦና ጫና ወይም ፍራቻን ማንገስ ነው። የሥነ ልቦና ጫና ወይም ፍራቻ የማስከተሉ የመጨረሻ ዓላማ (ultimate goal) ደግሞ ይህን እንደ አንድ ሥልት ወይም ታክቲክ በመጠቀም ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የሚፈልጉትን የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማ መጫን ነው። ቫህት ብ ለማሳካፔ በ ቭል በዛኖ ባሚፈፀመው ጎ ቃት በሕ መት ሥቱ መሠረፔ በተቋቋመው መት ሥፔ፣ ባመት ሥፔ አካላፔ ባኢኮ ሚ ተቋማፔ ት ሁም በሕዝቡ ላቭ ሊሰዝር ይችላል።
- ወት ሎቹ የ ቭል ጥቃቶችን በማድረግ ወይም ለማድረግ በመዛት ሊከናወኑ የሚችሉ ሲሆን፣ አወክ ሙም ሆትተብሎ ስቦበፔ የሚፈፀም ነው።

ከዚህመ፣ አንጻር አንድ የሆነ አመለካከት ወይም እምነት እንዲስፋፋ ወይም እምነቱ የሚያስቀምጣቸው ሕጎች ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ለማስገደድ የሽብርተኝነት ወንጀል ሊፈፀም ይችላል ማለት ነው።

ባመወሸሸ ጎ ሸቁዎኖ

1. የካፒታሊዝም ሥርዓት ሀብታሞች ድሆችን በመበዝበዝ የሚኖሩበት ሥርዓት በመሆኑ ሥርዓቱ መቀየር አለበት ብሎ የሚያምን አንድ ግለሰብ የካፒታሊዝም ሥርዓቱ መለያ ናቸው ብሎ በሚያያቸው ትላልቅ የግል የኢኮኖሚ ተቋማት ላይ አደጋ ቢያደርስ ድርጊቱ በሽብርተኝነት ወንጀል ሊፈረጅ ይችላል? ለምት?

2. የሽብርተኝነት ወንጀል በሕግ የሰውነት በተሰጣቸው ድርጅቶች አማካኝነት ሊፈፀም ይችላል? በመንግስታት አማካኝነትስ? ሽብርተኝነት አለ ለማለት ከፈጻሚው ወይስ ከተፈፀመው ድርጊት አንጻር ነው የሚታየው (የሽብርተኝነት ወንጀል አለ ለማለት ድርጊቱን ወይስ ፈጻሚውን ነው የምናየው)? ለምት?

3. አገሪቱ ይህን መንገድ ካልተከተለች ትበጠበጣለች፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል መከበሩ አገሪቱን ይበታትናታል በማለት "ማስፈራራት" በሽብርተኝነት ወንጀል ውስጥ ይካተታል ትላላችሁ? ለምት?

4. ምንም ዓይነት ይህ ነው የሚባል ዓላማ የሌለው ወይም "ለመታወቅ" ብቻ ተብሎ በፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ላይ ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱ ወይም ሁሉም ቢፈፀሙ የሽብርተኝነት ወንጀል ተብሎ ሊፈረጅ አይችልም?

5. የሆነ ቡድን አባላት በፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ ከተመለከቱት ዓላማዎች ውስጥ አንዱን በተዕዕኖ ለማሳካት በማሰብ ራሳችንን እናጠፋለን (እንገድላለን) በማለት ለማስፈራራት ቢሞክሩ የሽብርተኝነት ወንጀል ተብሎ ሊፈረጅ አይችልም? (የእንግሊዝ Terrorism Act (2000) እንዲህ ዓይነት ተግባር በወንጀሉ እንደማይፈረጅ በግልፅ አስፍሯል)።

6. በቸልተኛነት የሽብርተኝነት ወንጀል ሊፈፀም አይችልም ትላላችሁ? ለምት?

ክፍል አምስት - <u>የሰዎች ህገወጥ ዝውውር፣</u>

ሰዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማዘዋወር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እና ዓለም አቀፋዊ ይዘት እየያዘ የመጣ ወንጀል ሲሆን ይህ ወንጀል በተለይ በሴቶችና በህጻናት ላይ የሚያስከትለው ችግርና አስከፊነቱ እየተባባሰ መጥቷል።

በሰዎች መነገድ (human trafficking) የሰዎችን የተለያዩ መብቶች በእጅጉ የሚጻረር ከአገራዊነት ዓለም አቀፋዊ ባህሪ ያለው ተግባር ነው። በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (conventions) እና መግለጫዎች (declarations) ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሰዎች ያለምንም አድልዎ የሰብዓዊ መብቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚገባ፣ በተለይም ደግሞ የግዴታ ሥራ እንዲሰሩ ከመገደድ የመጠበቅ መብት እንዳላቸው፣ ጾታን መሠረት በማድረግም ሆነ በሕጻናት ላይ የሚደርስን የፆታና የጉልበት ብዝበዛ የዓለም ሕብረተሰብ በጋራ የመዋጋት ግዴታ እንዳለባቸው ያስቀምጣሉ።

በሴቶች እና በህጻናጽ ላይ የሚፈፀሙ ሕገ ወጥ ዝውውሮችንና ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ በደሎች በወንጀል የሚስጠይቁ ስለመሆናቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በተለያዩ አንቀጾች ደንግጓል። በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 597 ላይ እንደተደነገገው ሴትን ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የግዳጅ ሥራ ለማሰራት በማሰብ በሃይል፣ በዛቻ፣ በተንኮል፣ በማታለል፣ በመጥለፍ ወይም በሴቲቱ ወይም በልጁ ላይ ኃለፊነት ላለው ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም በመስጠት ተበዳይዋን (ተበዳዩን) የሚመለምል፣ ከቦታ ቦታ የሚያዘዋውር፣ ከሀገር ያስወጣም ሆነ ወደ ሃገር ያስገባ እንዲሁም የደበቀ ማንም ሰው በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን፤ ይህንን የወንጀል ድርጊት ለማስፈፀም ተበዳዮችን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወይም በውጭ አገር በጉዞ መጨረሻ ሲደርሱ ለማስረከብ በማሰብ (በማቀድ) በየብስ፣ በባህር ወይም በአየር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ ዝውውሩን የመራ ወይም የረዳ ሰው በተመሳሳይ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል።

ሌላው ድንጋጌ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክን አስመልክቶ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 598 ላይ የተደነገገው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገ ወጥ መንገድ የኢትዮጵያ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከ ማንኛውም ሰው የወንጀል ተጠያቂነት አለበት፣ ቅጣቱም ከአምስት ዓመት እስከ 10 ዓመት ሊደርስ የሚችል ፅኑ እስራትና ከሃያ አምስት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ነው። በዚህ መልኩ የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብዓዊ መብቷ፣ በሕይወቷና በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ፅኑ እስራትና ሃምሳ ሺህ ብር መቀጮ ሊደርስ ይችላል። መሠል ድርጊቶች በሴቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ሰው ላይ በሚፈፀሙበት ጊዜም ተመሳሳይ ቅጣት የሚያስከትሉ ይሆናሉ።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ለአካለ መጠን የደረሰ ወንድን የግዳጅ ሥራ ለማሰራት በማሰብ በሃይል፣ በዛቻ፣ በተንኮል፣ በማታለል፣ በመጥለፍ ተበዳዩን የሚመለምል፣ ከቦታ ቦታ የሚያዘዋውር፣ ከሀገር ያስወጣም ሆነ ወደ ሃገር ያስገባ ማንም ሰው ስለሚኖርበት የወንጀል ተጠያቂነት ተወያዩበት።

2. ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ሰዎችን ወደ ውጭ አገር ልከው የተላኩት ሰዎች በአካላቸው፣ በሰብዓዊ መብታቸው ወይም በሕይወታቸው ላይ ጉዳት ቢደርስባቸው በላኪዎች ላይ የወንጀል ተጠያቂነት ይኖር እንደሆነ መርምሩ።

3. የሚከተሉትን ጉዳዮች ተወያዩባቸው፡-

(ሀ) ወ/ሪት ሶፊያ ሀምዛ የተባለች ኢትዮጵያዊት በአንድ ፈቃድ ባለው ሠራተኛና አሠሪ አገናኝ ኤጀንሲ አማካኝነት ወደ ቤሩት ተልካ በአንድ ግለሰብ መኖሪያ ቤት ውስጥ በቤት ሠራተኛነት ስታገለግል ቆይታ በግለሰቡ መፀዳጃ ቤት ውስጥ በገመድ ታንቃ በመስኮት ተንጠልጥላ፣ የግራ እጅዋና የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቿ በኤሌክትሪክ እንዲሁም በፈላ ውሃ ተቃጥሎ ሕይወቷ ስለማለፉ ከፊደራል ፖሊስ የተላከው የወንጀል ምርመራ መዝገብ ያስረዳል፤ በተጨማሪም መዝገቡ ላይ በቤሩት ፖሊስ በተደረገው ምርመራ

በግለሰቧ ላይ ለደረሰው ሁኔታ ተጠያቂ ሊሆን የሚችል ሰው ስላለመገኘቱ የተገለፀ መሆኑን ያሳያል፡፡

(ለ) ወ/ሪት ሰብለ አባይ የተባለች ኢትዮጵያት በአንድ ፈቃድ ባለው ሠራተኛና አሠሪ አገናኝ ኤጀንሲ አማካኝነት ወደ ሶሪያ አገር ተልካ ሁለት ወር ከሀያ ቀን ሰዎች በነጻ አሰርተዋት፣ በሴትነቷ ተጫውተውባት እንዲሁም በአሰቃቂ ሁኔታ የውስጥ እግሯን በመደብደብ አሰቃይተው ወደ ኢትዮጵያ የመለሷት ስለመሆኑ በምርመራ መዝገቡ ላይ ተመልክቷል፡፡

(ሐ) ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላሳ ዓመታት በላይ የኖሩ ዜግነታቸው ሕንድ የሆኑ ባልና ሚስት ልጅ (ልጃቸውም ዜግነቱ ሕንድ ነው) ሕጋዊ ፍቃድ በሌለው ግለሰብ አማካኝነት ለሥራ ወደ ውጭ አገር ተልኮ ከፍተኛ በደል ደርሶበት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል፡፡ የላከው ሰው የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል?

ክፍል ስድስት - <u>የአስገድዶ መድፈር ወንጀል፣</u>

በአዲሱ የወንጀል ሕግ የአስገድዶ መድፈር ወንጀልን ጨምሮ ሌሎች በግብረ ሥጋ ነፃነትና ንፅህና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች የተደነገገው ከአንቀጽ 620 ጀምሮ እስከ አንቀጽ 628 ባሉት ድንጋጌዎች ሲሆን የአንቀጽ 620 ንዑስ ቁጥር 1 ድንጋጌ "ማንም ሰው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ሕሊናዋን እንድትስት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ከጋብቻ ውጪ አስገድዶ ከአንዲት ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል" ይላል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት የአስገድዶ መድፈር ተግባር ተፈፅሟል ለማለት፡-

1. ተጠቂዋ ሴት መሆን አለባት፣ (አንዲት ሴት ወንድን አስገድዳ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከእርሷ ጋር እንዲፈፀም ያደረገች እንደሆነ በወንጀል የምትጠየቅ ሲሆን እንዲህ ዓይነት የወንጀል ድርጊት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 621 ነው)፡፡

2. በማናቸውም መንገድ የሚደርስባትን ጥቃት መከላከል እንዳትችል የተደረገች መሆን አለባት፡፡ ማለትም በሴቷ ላይ ድርጊቱ የተፈፀመው ኃይልና ዛቻን በመጠቀም፣ ወይም ሕሊናዋን በማሳት እና በመሳሰለው መንገድ የመከላከል አቅሟን በማሳጣት ተደግፎ መሆን አለበት፡፡

3. የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም አለበት (ወይም ቢያንስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈፀም መሞከር ይኖርበታል)፣

4. ድርጊቱ የተፈፀመው የጋብቻ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል መሆን አለበት፡፡ በዚህም መሠረት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በጋብቻ ተሳስረው የሚገኙ ሰዎችን አይመለከትም ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 621 መሠረት አንዲት ሴት ወንድን አስገድዳ ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈፅም ያደረገች እንደሆነ በወንጀል የምትጠየቅ ቢሆንም ሕጉ ይህን የወንጀል ድርጊት “አስገድዶ የመድፈር” (rape) በሚለው ሀረግ (ቃል) አይጠራውም፡፡

አዲሱ የወንጀል ሕግ አስገድዶ መድፈርን በተመለከተ ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ከቀድሞው የሚለዩባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ለመደበኛው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ተቀምጦ የነበረውን እስከ አሥር ዓመት የሚደርስ የፅኑ እስራት ቅጣት መነሻውን ከአምስት ዓመት እንዳያንስ ያደረገው ሲሆን የቅጣቱን ጣራ ደግሞ ወደ አሥራ አምስት ዓመት ከፍ አድርጐታል፡፡ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ሲኖር ደግሞ በቀድሞው ሕግ እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ብቻ ያስቀጣ የነበረው በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ወደ ሀያ ዓመት ፅኑ እስራት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዕድሜዋ ከ15 ዓመት እስከ 18 ዓመት በሆነ ሴት ላይ የተፈፀመ አስገድዶ መድፈር የሚያስቀጣው በመደበኛው የአስገድዶ መድፈር ድንጋጌ መሠረት የነበረ ሲሆን (እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ የፅኑ እሥራት ብቻ ነበር የሚያስቀጣው) በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620(2) መሠረት ዕድሜዋ አስራ ሦስት ዓመት ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላት ሴት ልጅ ላይ የሚፈፀመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የሚያስቀጣው ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ነው፡፡

አስገድዶ የመድፈር ድርጊት ከባድ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ ወንጀለኛው በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንደሚቀጣና ከአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ ጋር ተያይዞ የመጥለፍ ተግባር ወይም በሽታ የማስተላለፍ ተግባር ሲፈፀም ስለተደራራቢ ወንጀሎች በተደነገጉት አንቀፆች መሠረት ቅጣት በወንጀለኛው ላይ እንደሚፈፀምበት በማስቀመጥ በቀድሞው ሕግ ያልነበሩ ድንጋጌዎችን አዲሱ የወንጀል ሕግ ጨምሯል፡፡

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች አዲሱ የወንጀል ሕግ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ሲፈፀም የሚጣለውን የቅጣት ወለልም ሆነ ጣራውን ከፍ ያደረገ ሲሆን አንዲት ሴት ለአካለ መጠን ወይም ለጋብቻ የምትደርስበትን ዕድሜ (18 ዓመት) ጠብቆ ከዚህ ዕድሜ በታች ላይ የምትገኝን ሴት ልጅ አስገድዶ መድፈር ከፍ ባለ ቅጣት የሚያስቀጣ እንዲሆን አድርጓል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ዕድሜዋ ከ18 ዓመት ለከሆነች ሴት ጋር የሚደረግ ግብረ ሥጋ ግንኙነት የሴቷ ፍቃደኝነት ቢኖርበትም እንኳን በወንጀል ያስጠይቃል፡፡ በአባባሉ ትክክለኛነት ላይ ተወያዩበት፡፡

2. ለዐቃቤ ህግ የደረሰው በአንድ የምርመራ መዝገብ ላይ ተከሣሽ ዕድሜው 15 ዓመቱ እንደሆነና የግል ተበዳይ ደግሞ ዕድሜዋ 14 ዓመት ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡ ተከሣሽ

ምርመራው የተጣራበት የግል ተበዳይዋን ደፍሯል በሚል ሲሆን ተከሣሽ ከግል ተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረጋቸውን አምኖ ነገር ግን ተበዳይ ነች የተባለችው ፈቃደኛ ሆና ድርጊቱ ስለመፈፀሙ የገለፀ ሲሆን ልጅቱም ተከሣሽ ምንም ዓይነት የማስገደድ ተግባር ሳይፈፀም በፈቃደኝነት የተፈፀመ ስለመሆኑ ገልጻለች፡፡ እናንተ በዐቃቤ ሕጉ ቦታ ብትሆኑ ምን ዓይነት ውሳኔ ትሰጣላችሁ?